*1ጴጥ. 1፡7 በዚህም እጅግ ደስ ይላችኋል ነገር ግን በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለምስጋናና ለክብር ለውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል።*

2ጴጥ. 1፡16 *የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ።*

1ዮሐ 2፡28 *አሁንም ልጆች ሆይ በሚገለጥበት ጊዜ እምነት እንዲሆንልን በመምጣቱም በእርሱ ፊት እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ።*

መምጣቱ ምክንያታዊ ነው፤ ከምክንያቶች ውስጥ ዋንኞቹን በቀዳሚነት መናበብ ተገቢ ነው።

ኢየሱስ ድነትን ለማምጣት እና ሰዎች ይድኑ ዘንድ መፍትሔን ለማቀበል አይመጣም፦ ይልቅስ ከፉውን ዓለም ሊፈርድበት፣ የጠላት ስራን ፍፃሜ ሊሰጥ ይመለሳል፤ የኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ አመጣጥ በትህትና፣ በየዋህነትና በፍቅር እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የድነት ስራ ለመስራት አስከ መስቀል ሞት ድረስ መታዘዝ ነበር። ይህም ዮሐ 3፡17፣ 12፡47 ላይ በአግባቡ ሰፍሯል።

«እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው» ዮሐ 3፡17 ሁለተኛ ሲመጣ ግን መምጣቱ ከትንሳኤ ጋር፣ ከመታደግ ጋር እና ከፍርድ ጋር ይተሳሰራል **«ድኑናል፤ እየዳንነው፤ እንድናለን።»** የሚለው ሂደታዊ ጉዘትም ያጠናቀቃል።

> *«ወንድሞች ሆይ አንቀላፍተው ስላሉ ሰዎች ሳታውቁ እንዳትቀሩ አንፈልግም ደግሞም ተስፋ እንደሌላቸው እንደሌሎች ሰዎች እንድታዝኑ አንሻም ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሳ ካመንን በኢየሱስ ሆነው ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደዚሁ ያመጣቸዋል፤ በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህን ነው እኛ በሕይወት ያለንና ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉትን አንቀድምም።»*
> 1ተሰ. 4፡13-15

በዚህ ጊዜንስህ ግቡ የስብከት ዋንኛ ቃል አይሆንም፤ ይልቅስ የኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅነት ከቀደመው በበለጠ ገኖ ይገለፃል።

> *በ2ጴጥ 3፡9 «...አንዳንድ ሰዎች የዘገየ እንደሚመስላቸው የተስፋ ጌታ ቃሉን ለመፈፀም አይዘገይም ነገር ግን ማንም እንዳይጠፋ ሁሉ ለንስሀ እንዲበቃ ስለ እናንተ ይታገሳል»*





ይህ መሰረታዊ ምክንያት የሚያበስረው የንስሀ ጥሪ ቁሞ የእግዚአብሔር ፍርድ ከክርስቶስ ዳግም ምፅአት ጋር ተያይዞ እንዳለ ማረጋገጥ ነው

***

ኢየሱስ ክርስቶስ የተልዕኮውን የመነሻ እና የመድረሻ ክልልን ያሳወቀው ወደ አባቱ ለመዝለቅ በሚዘጋጅበት ጊዜ ነበር፤ ይህን በማቴ. 28፡20 ሰፍሯል *«...ስልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤ ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ... ደቀመዝሙር አድርጓቸው እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ...»* ማለቱ አይዘነጋም፤ ይህ የተሰጠው ስልጣን በስራ ላይ ውሎ እያገለገለ አለ፤ የዚህ ስልጣን የመነሻ ፍፃሜ ግን በ1ኛ ቆሮ 15፡24-26 ላይ ተበስሯል። *«በኃላም መንግስቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉና ስልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ ፍፃሜ ይሆናል፤ ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድረስ ሊነግስ ይገባዋልና»* በዚህም ሞት ተሸናፊ በመሆን ክርስቶስ ደግሞ ሲመለስ በእርሱ የሆኑ ሙታን ተነስተው የመንግስቱ የፍፃሜ ተካፋይ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

***

በተያያዥ በፍጥረት ላይ ያለ የሀጢአት ውጤት እና ሰቆቃም መፍትሄ የሚያገኙት ከኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ ጋር ተያይዞ ነው፤ ሮሜ 8፡19-23 የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና። ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቶአልና በተስፋ ስላስገዛው ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም። ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ከቡር ነፃነት እንዲደርስ ነው። ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ መቃተትንና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና እርሱም ብቻ አይደለም ነገር ግን የመንፈስ በኩራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን። ይህም ከሰው የመነሻ ታሪክ ጋር ተሳሳሪ በመሆን ከዘፍ 3፡17-19 ጋር ይጋመዳል *«አዳምን አለው የሚስትህን ቃል ሰምተሀልና ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሳ የተረገመች ትሁን በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ እሾህንና አሜኬላን ታበቅልብሀለች የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህና።»* ዳግም መመለሱ የፍጥረት መታደስ መሰረታዊ መገለጫ ነው።

***

ትንሳኤ ሙታን ከክርስቶስ ዳግም መምጣት ጋር ሊያያዝ መቻሉ ጥንት በዳንኤል ኋላም

በኢየሱስ የተብራራ ትምህርት ነው «በምድር አፈር ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፣ አንዳንዶቹ ለዘላለም ሕይወት ሌሎቹም ለውርደትና ለዘላለም ጉስቁልና ይነሳሉ» ዳን 12፡2 በማለት ሲተነብይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ *«በዚህ አትደነቁ መቃብር ውስጥ ያሉ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል መልካም የሰሩ ለሕይወት ትንሳኤ ክፉ የሰሩ ለፍርድ ትንሳኤ ይወጣሉ...»* (ዮሐ 5፡28-29) በማለት መሰረት ጣለልን በዚህም የጌታ የሆኑትና ያልሆኑት እንደሚነሱ አረጋገጠበት ይህም በአንድ ጊዜ እንደሚፈፀም ያስተምራል ያሳውቃል።

***

*ይህ የአነሳስ ሁኔታ ግን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማብራሪያ በአግባቡ ሊተነተን ይገባዋል፤*

በሉቃ 24፡39 ላይ ኢየሱስ «እጆቼንና እግሮቼን ተመልከቱ እኔው ራሴ ነኝ ደግሞም ንኩኝና እዩ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ስጋና አጥንት የለውምና» በማለት ራሱን የገለፀበት መንገድ የእያንዳንዳችንም የትንሳኤ መገለጫ መሆኑ አይቀሬ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ 28፡9 «...እነርሱም ወደ ኢየሱስ ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት» በማለቱ የትንሳኤው አካል በእርግጠኝነት የሚዳሰስ የሚጨበጥ ነበር። በዮሐ 20፡11 መሰረትም ከትንሳኤው በኋላ አካሉ በመቃብሩ አልነበረም፤ ጳውሎስ መንፈሳዊ አካል እያለ ያስተማረው እንግዲያስ እነዚህን ሁሉ ያጠቃለለ አካልን እንጂ የማይጨበጥ የማይታይ መሆኑን አያመለክትም። እንግዲያስ በ1ቆሮ 15፡44 «ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ» ያለበት መለያውም መለኪያውም ይኸው ነው፤ አማኞች በአካል በተገለጠ ማንነት ይኖሩ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ ይህም ከትንሳኤው ጋር በቀጥታ ይያያዛል።

***

*መያያዙ ከዚህ ከያዝነው የመነሻ አካላችን ጋር ተገጣጣሚ መሆኑ ነው።* 1ቆሮ 15ም የዚህ ትምህርት *መደምደሚያ* ነው። በትንሳኤው ተነስቶ የታየውበዮሴፍ መቃብር ውስጥ የነበረው የኢየሱስ በድን ነው፤ ይህን ግንዛቤ ብዙዎች ሊሆን የማይችል ብለው ይሞግቱታል። ግን በአካላችን ላይ የሚካሄዱትን ዘላቂ ለውጦች ከግምት ማስገባት ያንንም በቀጣይነትና በዘላቂነት ማየት ግራመጋባቱን ይመልሰዋል።

በማህፀን ያለ ህፃን በውልደት ጊዜና ኋላ በልጅነት እና በወጣትነት ዕድሜ ያለ ያው አንድ ሰው ነው። ይህ አንድ ሰው ግን የአካሉ መዋቅር በለውጥ ሂደት ውስጥ ይኖራል፤ ይህ ለውጥ ግን ሰውየውን ወደ ሌላ ሰውነት አይቀይረውም ከመነሻ እስከ መድረሻ በሚጠራበት ስም እየተጠራ ይሄዳል። ይዘልቃልም።





በመሰረቱ ይህ የትንሳኤው አካል ከቀደመው አካል የተሻለ ነው፤ የበለጠ እና የከበረም ነው፤ ኢየሱስ ከትንሳኤም በኋላ በተዘጋ ቤት ውስጥ ተገኘ ። (ዮሐ 20፡26) «በሮቹ ተቆልፈው ነበር ኢየሱስ ግን መጥቶ በመካከላቸው ቆመና ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው፤ የትንሳኤው አካል በቦታ የመገደብ ይዞታን ጣሰ። ገደብ ሳይኖርበት ቀረ። ይህን አካል ነው ጳውሎስ የትንሳኤው አካል ያለው 1ቆሮ 15፡50 ያለ ክርስቶስ ስለሆኑት ግን ትንሳኤያቸው እንዴት እንዴት ሊሆን እንደሚችል መናገር ይከብዳል። በተያያዥ ትንሳኤ ሙታን አልሆነም በማለት በ1ኛው ክፍለ ዘመን ይሞግቱ ስለነበሩት ጥቂት ማብራሪያ በመስጠት ጭብጡን ከማቴ 24፡1 ጋር እናያይዘው

15 *እንደማያፍርና የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ የተመሰከረለት ሰራተኛ ሆነህ ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ ትጋ፤*

16. *እግዚአብሔርን ከማያስከብር ከንቱ ልፍለፋ ራቅ፤ በዚህ ነገር የተጠመዱ ሰዎች ከእግዚአብሔር እየራቁ ይሄዳሉና፤*

17. *ትምህርታቸው እንደማይሽር ቁስል ይሰራጫል፤ ከእነዚህም መካከል ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ይገኛሉ፤*

18. *እነዚህም ከእውነት ርቀው የሚባዝኑ ናቸው፤ እነርሱም ትንሳኤ ሙታን ከዚህ በፊት ሆኗል እያሉ የአንዳንዶቹን እምነት ይገለብጣሉ...* 1ኛጢሞ.1፤15-20

እነዚህ ሁለቱ ተጠቃሽ መምህራን በኤፌሶን ኑፋቃዊ ትምህርት የሚሰጡ ሰዎች ነበሩ።

ሄሜኒዮስ በ1ጢሞ 1፡19-20 ጳውሎስ ከእስክንድሮስ ጋር አያይዞ በማቅረብ «...ለሰይጣን አሳልፌ ሰጠኋቸው...» ብሎ ነበር፤ አሁን ደግሞ ይህ ሰው ከፊልጦስ ጋር ተነስቷል 2ጢሞ 2፡16-18፤ 1ጢሞ 1፡6 እና 6፡21 ላይ እናያቸዋለን።

1፡6 «አንዳንዶች ከእነዚህ ነገሮች ዘወር ብለው ወደ ከንቱ ንግግር ተመልሰዋል»

6፡21 «...እውቀት አለን ሲሉ የነበሩ አንዳንዶች ይህን በማድረጋቸው ከእምነት መንገድ ስተው ሄደዋል...»

«እነዚህ ሰዎች... ትንሳኤ ሙታን ከዚህ በፊት ሆኖአል» አሉ፤ እርግጥ ነው፡- ጳውሎስ መንፈሳዊ ትንሳኤ እንዳለ አስተምሯል። በመንፈስ ሙት የሆኑትን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሕያው ይሆናል። ብሷል ለዚህም ሮሜ. 6፡3-4 ኤፌ 2፡6 ፊሊ. 3፡11 ቆላ 2፡12፤ 3፡1 እንዲሁም ሉቃ 15፡24 ያስተምራል፤ ልክ እንዲሁ ግን የአካል ትንሳኤ የክርስትና ዋና መሆኑንም አስተምሯል። 1ቆሮ 15 ፊል 3፡21 ዮሀ 5፡28 ይልቅኑ 1ቆሮ 15፡13,14,17 ይነበባሉ።

13 የሙታን ትንሳኤ ከሌለማ ክርስቶስ አልተነሳም ማለት ነዋ!

14 ክርስቶስም ካልተነሳ ስብከታችን ዋጋ ቢስ ነው እምነታችሁም ከንቱ ነው፣

17 ክርስቶስም ካልተነሳ እምነታችሁ ከንቱ ነው እናንተም እስከ አሁን ድረስ ከነኃጢአታችሁ አላችሁ ማለት ነው፣

ይህን መሰረታዊ እውነት ይዘው የነበሩት ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ውለው አድረው ይህን ፅኑ እውነት ሻሩ በመሻራቸውም በእርምተ ጥቅም ውስጥ ተከተቱ (Excommunicated)።

በመሰረቱ ትንሳኤ የለም ማለት ያስቻላቸው በወቅቱ የነበረው የአረማውያን እምነት ስለገዘፈባቸው ነው ኖስቲዝምና መሰል ትምህርቶች መንፈስ «ቅዱስ» ነው፤ ቁስ «እርኩስ» ነው፤ በማለት ኢየሱስ በስጋ መጣ የሚለው ትምህርት ለእነርሱ ቀልድ ሆነ።

መንፈሳዊነት ተገቢ ይሆን ዘንድ በክርስቶስ የሆኑ ክርስቲያኖች ከቁስ ምንነት ተለይተው መንፈሳዊ ማንነት መያዝ እንጂ እንደገና የእርኩሰት መገለጫ ከሆነው ቁስ አካል ጋር በመገናኘት ስለ ትንሳኤ አካል መነጋገርና ማመን የለባቸውም አሉ።

1ጢሞ 4፡3 «*...ሰዎች ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት የማይቀበሉበት ጊዜ ይመጣል። ከዚህ ይልቅ ለገዛ ምኞቶቻቸው የሚስማማውን የሚያሳክክ ጆሮአቸው ሊሰማ የሚፈልገውን እንዲነግሩአቸው ብዙ አስተማሪዎችን ይሰበስባሉ...*» ይላል

«ቁስ እርኩስ ነው። አካላችን እርኩስ ነው። ከዚህም የተነሳ ከፈረሰ ሊነሳ አይገባውም...» በማለት ሰው ያለ አካል ትንሳኤ ከሀጢአተኝነት ወደ ፍፁምነት፣ ከስህተተኝነት ወደ ሙሉ ሕያውነት ይመጣልና ከዚህ ማለፍ ጥፋት ነው ብለው ያስተምሩ ነበር። ይህን ትምህርት ጳውሎስ፡-

- እግዚአብሔርን የማያስከብር ትምህርት፤-

- ከእግዚአብሔር የሚያርቅ ትምህርት፤

- የማይሽር ቁስል...በማለት ጠራው።

ቁጥር 19 «ይሁን እንጂ «*ጌታ የእርሱ የሆኑትን ያውቃል ደግሞም የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከክፋት ይራቅ የሚል ማኅተም ያለበት የማይነቃነቅ መሰረት ቆሞአል...*» በማለት፤ አገላለፁን ከማቴ 24፡11 እና 24 ጋር ያስተሳስራል።





11 «...ብዙዎች ሐሰተኛ ነብያት ይነሳሉ ብዙዎችን ያስታሉ...

24 ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት ይነሳሉና ቢቻል የተመረጡትን ለማሳት ሲሉ ትላልቅ ምልክቶችንና ታምራትን ያደርጋሉ... እንዲህም ቢሆን ግን መልካሙ እረኛ የገዛ በጎቹን ይጠብቃል። ያውቃል፤ ከእጁ የሚነጥቃቸው የለም። መንግስቱም ፅኑ ናት ዮሐ. 10,14-28 ዕብ 12፡28 ይላል።

በ1ጴጥ 5፡9 ዕብ 5፡12 ክርስቶስ ዋንኛው መሰረት 1ቆሮ 3፡10-12 የማዕዘን ድንጋይነቱ ክርስቶስ ከሞት በመነሳት ቀዳሚ እንደሆነ ሁሉ አማኞም እንዲሁ ይከተላሉ።

***

መጽሐፍ ቅዱስ ፍርድንና ቅጣትን ገላጭ መጽሐፍ ነው፤ የውሃ ጥፋት፣ የሰዶምና ጎመራ መጥፋት፣ የእስራኤል ከግብፅ የመውጣት ሂደት ላይ ተደጋጋሚ ፍርዶች (በግብፅ ላይ) ባቢሎናውያን እንዲሁም በአይሁዶች ላይ መምጣቱን እናውቃለን። የ70 ዓ.ም የኢየሩሳሌም እና የቤተመቅደሱ መፍረስ ሁሉ ከፍርድና ከቅጣት ጋር የተያያዘ ነው። ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር ይፈርዳል፤ይህ አዲስ ትምህርት አይደለም። በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ የፍፃሜውን ፍርድ መጠባበቅም ተገቢና ምክንያታዊ ነው።

በመሰረቱ ፍርድ ጥቅም አለው፡- ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል የመፈጠራቸው ተፈላጊነት በተለይም ስነምግባራዊ አቅምን በዘመናቸው በአግባቡ አለመጠቀማቸውን በማመላከት የሰው ልጅ ታሪክ ማጠቃለያ ማግኘቱን፣ ያመላክትበታል። ራዕ 20፡12-13 «*...ሙታንን ታላላቆችንም ታናናሾችን በዙፋን ፊት ቆመው አየሁ መፅሐፍቱም ሌላም መፅሐፍት ተከፈተ ሙታንም በመጽሐፍቱ ተፅፎ በተገኘው መሰረት እንደ ስራቸው መጠን ተፈረደባቸው። ባህርም በውስጡ የነበሩትን ሙታን ሰጡ እያንዳንዱም እንደ ስራው መጠን ተፈረደበት*» ይህ የሚያበስረን እግዚብሔር በየዕለት ስራችን ሁሉ ውስጥ ዋንኛ መሆኑን ያፀናል። በሐዋ 17፡27-28 «*...ይህም ቢሆን እርሱ ከእያንዳንዳችን የራቀ ሆኖ አይደለም። የምኖረውና የምንቀሳቀሰው ያለነውም በእርሱ ነውና*» የሚለው ቃል እግዚአብሔር ለፍርዱ መሰረት እንዳለው ያረጋግጣል። እንግዲያስ በዚህ ሁሉ ክርስቶስ የሁሉ ነገር ማዕከል ነው።

«*...በመረጠው ሰው አማካኝነት በዓለም ላይ በፅድቅ የሚፈርድበትን ቀን ወስኖአልና እርሱንም ከሙታን በማስነሳቱ ለሰዎች ሁሉ ይህን አረጋግጧል...*» *ሐዋ 17፡31 ሉቃስ በዚህ ቃል እንዳብራራው ጳውሎስም «በወንጌል እንደሚያስተምረው እግዚአብሔር በሰው ልብ የተሰወረውን በክርስቶስ በኩል በሚፈርድበት ዕለት ግልፅ ያደርገዋል»* (ሮሜ 2፡16 አመት) በማለት ክርስቶስ የዓለም ታሪክ ዋንኛው ማዕከል መሆኑን ያሳውቃል።

ስነ ፍፃሜ ተያያዥ ሆኖ ከሚያነሳቸው አስተምህሮዎች አንዱ ለደህንነት የተዘጋጁ የዘላለም መኖሪያቸው በየት እንደሆነና ለደህንነት ያልበቁ ፍፃሜያቸውና ኑሮአቸው እንዴትና በየት እንደሆነ ማወቅን ያካትታል። ለዚህ ደግሞ መነሻው ሞት እንቅልፍ ነው ብሎ ከማመን ባለፈ ሰው ሲሞት ያለ ዕውቀት በሆነ ዓለም ውስጥ ራሱን ማግኘቱ ሳይሆን ወዲያው እንደ ሞተ ሊረዳው ወደ ሚችለው ቀጣይ ሕይወት መሻገሩ ነው።

ይህ ደግሞ ኢየሱስ ከሞት በኋላ ስላለው ኑሮ የገለፀበት የአላዛር እና የሌላው ሰው ማንነት ይገልጠዋል፤ ይህም በሉቃ 16 ከ19 ጀምሮ ተተንትኗል «ሐምራዊና ቀጭን በፍታ የለበሰ በየቀኑም በተድላ በደስታ የሚኖር አንድ ሀብታም ሰው ነበር። በእንፃሩም መላ ሰውነቱ በቁስል የተወረረ አንድ አልአዛር የሚባል ድሀ በዚህ ሀብታም ሰው ደጃፍ ይተኛ ነበር። ከሀብታሙ ሰው ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ እንኳ ሊመገብ ይመኝ ነበር። ውሾችም ሳይቀሩ መጥተው ቁስሉን ይልሱት ነበር።

ይህም ድሀ ሞተ መላዕክቱም ወደ አብርሀም እቅፍ ወሰዱት ሀብታሙም ሰው ደግሞ ሞቶ ተቀበረ በሲኦልም እየተሰቃየ ሳለ ቀና ብሎ ከሩቅ አብርሀምን አየ አልዓዛርንም በእቅፉ ይዞት አየ...» በማለት ገለፃውን ያሳድጋል።

በዚህ ትምህርቱ ከስጋ ሞት ቀጥሎ ወዲያው በሟቹ ህልወና ላይ የሚቀጥለውን ይዞታ አስረድቷል፤ ሐዋሪያው ጳውሎስ ከኢየሱስ ትምህርት ጋር ስምም ስለሆነ ነው በፊሊጵስዩስ 1:23-24 ላይ «ከእነዚህ በሁለቱ እጨነቃለሁ ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልሆን እናፍቃለሁ ይህ እጅግ የተሻለ ነውና ነገር ግን በስጋ መኖሬ ለእናንተ ይበልጥ አስፈላጊ ነው...» በማለት ያስተያየው በዚህም አማኝ ሲሞት ወዲያው ከአዳነው ጌታ ጋር ሊሆን መቻሉን ያም የሚያስደስት እንደሆነ ተረጋግጧልም፤ ይህ ደግሞ በምድር ከሚኖረው ኑሮ የተሻለ እና የበለጠ ነው። ይህም እስከ ትንሳኤ ጊዜ የሚሆነው ይዞታ ነው።

***

መንግስተ ሰማይ ስፍራ ወይም ቦታ ነው ብሎ ማመን አስቸጋሪ ነው፤ ይልቅስ ከሀጢአት በፀዳ ኑሮ መኖር፣ ከእግዚአብሔር ጋር ዘላቂ (ዘላለማዊ) ግንኙነት መመስረት የሚገለፅበት ይዞታ ነው። ስፍራ ሳይሆን የፍፅምና ባህርይ የሰፈነበት ማኅበር ነው፤ መንግስተ ሰማይ። እርግጥ አካባቢው ተሀድሶ፤ የባህርይ ፍፅም ለውጥ የመኖሩን አስፈላጊነት ሮሜ 8:19-22 እንዲህ በማለት ይገልፀዋል *«የአሁኑ ዘመን ስቃያችን ወደ ፊት ሊገለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር ሲነፃፀር ምንም እንዳይደለ እቆጥራለሁ። ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ በናፍቆት ይጠባበቃል። ፍጥረት ሁሉ ለከንቱ ተዳርጓል። ይኸውም በራሱ ምርጫ ሳይሆን ለተስፋ እንዲገዛ ካደረገው ከፍቃዱ*





*የተነሳ ነው። ይህም ፍጥረት ራሱ ከመበስበስ ባርነት ነፃ ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደ ሆነው ወደ ከበረው ነፃነት እንዲደርስ ነው፤ እስከ አሁን ድረስ ፍጥረት ሁሉ በምጥ ጊዜ እንዳለው ሲቃይ በመቃተት ላይ እንደሚገኝ እናውቃለን...»* መባሉ ከፊታችን ያለው ሁኔታ ምን መሆን እንደሚገባው ያስረዳል።

«...እኛ ግን ፃድቅ የሚኖርበትን አዲስ ሰማይና ምድር በተስፋ ቃሉ መሰረት እንጠባበቃለን...» 2ኛ ጴጥ 3:13 በማለቱ የጌታ የሆኑቱ የሚኖሩበት ስፍራ፡- ይህች ምድር ታድሳ ወደ ፍፅምና በማምጣት ወይም ከአዲስ ሰማይና ምድር ጋር የተዘጋጀ አማራጭን በማዘጋጀት የሚደረጅ መሆኑን በወጉ መናገር ባይቻልም፡- ግን ያኔ አካላችን በትንሳኤ የከበረ ከመሆኑ የተነሳ የቦታ ሁኔታዎች የማይወስኑት መሆኑ እንዲሁም ውድቀት ካመጣው ከየትኛውም ጣጣ ነፃ ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ሕብረት «ዘላለማዊ» መሆኑን ማረጋገጥ የእግዚአብሔር መንግስትን ቀዳሚው መለያ አድርጎታል።

***

ሐዋርያው ዮሐንስ «ወዳጆች ሆይ እኛ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ወደ ፊት ምን እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እናየዋለንና እርሱን እንደምንመስል እናውቃለን።» (1ኛዮሐ 3:2) በሚለው ገለፃ ውስጥ ከፊት ለፊታችን ሊመጣ ያለውን እርግጠኛ ፅኑ መቼት ምን ሊሆን እንደሚችል ያስረዳናል።

እግዚአብሔር አስቀድሞ ከወሰናቸው ቢጋሮቹ ውስጥ አንዱ የልጁን መልክ የመምሰል ይዞታ ነው፤ ሐዋሪያው ጳውሎስ «እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው...» ሮሜ 8:29 በማለቱ ክርስቲያኖች ዛሬ በምድር ኑሮአቸው ባላቸውትግል እንዳይረቱ፣ በሀጢአት ወድቀው በዚያው እንዳይዘልቁ ይልቁኑ ፊታቸውን በማየት ሙሉ ነፃነት፣ ሙሉ መቤዠት በሚቀጥለው ኑሮ ውስጥ መገለጡን ማመን በእርሱም ተስፋ መኖር የክርስትያኖች መፃሒ ሕይወት ነው።

በምድር ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ እና ደቀመዛሙርቱ አብረው ሳሉ ከተገለፁት አሉታዊ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ በእነርሱ ሊገለጥ የፈለገውን ሁሉ በእነርሱ አለማግኘቱ ነው፤ በስልጣን ጉዳይ ላይ ተጨንቀው ማነው በግራ በቀኝ የሚሆን ይላሉ? ለምን ትሞታለህ? በማለት ይደናገጣሉ፤ ከፈቃዱ ጋር ያልተጣጣመን ስራን በመስራት ይኖራሉ። ይህም የሆነው አዳማዊ (ሀጢአታዊ) ባህሪያቸው ከእነርሱ ጋር በመዝለቁ ነው፤ መፃኢው ሕይወት ግን ሐዋሪያው ጳውሎስ በፊል 1:23 ተስፋ እንዳደረገው ከእነዚህ አደናቃፊዎች ሁሉ በመለየት እርሱን የመምሰል ብቃት ማግኘት ነው።

እርግጥ ነው ከመሞት ወይም ከትንሳኤ ባሻገር ባለው ሕብረት ውስጥ ጋብቻ አይኖርም፤ በትንሳኤ ሙታን የማያምኑት ኢየሱስን ለመፈተን «ተጠየቅ» ወይም «ሎጂክ» ይዘው ሊፈትኑት መጡ፤ በፈተናውም የእነርሱን አስተምህሮ ይደግፍ እንደሆነና እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ተነሱ፤ ለዚህ ደግሞ «አንድ ሰው ዘር ሳይተው በመቅረቱ ሌላው የሰውየው ወንድም አገባት፡- በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሰባቱ ወንድማማቾች አግብተዋት ሞቱ» ካሉ በኋላ በትንሳኤ እሷ ለማንኛው ሚስት ትሆናለች?» በማለት ጠየቁ።

እነርሱ ማንም ያግባት አያግባት ጉዳያቸው አይደለም፤ ትንሳኤ ካለ ግን ውስብስብ ችግር ሊፈጠር እንደሚችል የማመናቸው አካሄድ «ትንሳኤ የለም» ስላስባላቸውእምነታቸውን ማረጋገጥ ነበር ምኞታቸው፤ ኢየሱስ ግን እነርሱ የሙሴን ሕግ ጠቅሰው «ዘር እስካልተካ ወንድሙ ያግባት» የሚለውን ቢዘረዝሩም እሱ ግን በቀዳሚነት «የምትስቱት እኮ ቅዱሳት መፅሐፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል ስለማታውቁ ነው። ሙታን በሚነሱበት ጊዜ እንደ ሰማይ መላዕክት ይሆናሉ እንጂ አይጋቡም፤ አያገቡም» አላቸው ማር 12፡18-27

በዚህም በመጪው ሕይወት ሕብረት መኖሩን፤ ግን ጋብቻ አለመኖሩን አበሰረ፤ ከዚህም የተነሳ በቀዳሚነት ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረትን ማድረግ አስከትሎም የእርስ በርስ ህብረት ተያይዞ እንደሚዘልቅ ታወቀ።

***

*ራዕ 7፡17 «በዙፋኑ መካከል ያለው በግ እረኛቸው ይሆናል፤ ወደ ሕይወት ውሃ ምንጭም ይመራቸዋል፤ እግዚአብሔር እንባን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል» ኢሳ 25፡8 ሞትንም ለዘላለም ይውጣል፤ ጌታ እግዚአብሔር ከፊት ሁሉ እንባን ያብሳል፤ የሕዝቡን ውርደት ከምድር ሁሉ ያስወግዳል»*

*ራዕ 21፡4 «ዕንባን ሁሉ ከዐይናቸው ያብሳል፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሞት ወይም ሐዘን ወይም ለቅሶ ወይም ስቃይ አይኖርም፤ የቀድሞው ስርአት አልፎአልና»* እነዚህ ውስን ጥቅሶች አመላካችነታቸው በመፃኢው ሕይወት መከራ፣ ስቃይ፣ ሀዘን፣ ህመም ፈፅሞ አለመኖሩን በድግግም ማፅናት ነው፤ ይልቅስ በእግዚአብሔር ዙሪያ መቦዘን አይኖርም፤ እንቅስቃሴ እና ስራ፣ የተትረፈረፈ ሕይወት በዚያ ይበረክታል፤ መሰልቸት የለም፤ ድግግሞሽ በዚያ የለም፤ ይልቅኑ የሕያውነት መገለጫ ንፁህ አምልኮ ለእግዚአብሔር በዚያ ይሆናል «...የእግዚአብሔርና የበጉ ዙፋን በከተማይቱ ውስጥ ይሆናል፤ አገልጋዮቹም ያመልኩታል» ራዕ 22፡3ም እውን ይሆንበታል፤





የቅዱሳን የኑሮ ሁኔታ ፍፁም ነው፤ ፍፁም ማለት ግን ዕድገት የሌለውንና ባለበት የመቆም ኑሮን ፈፅሞ አያመለክትም፤ ይልቅስ ዘላለማዊ ዕድገትን ያፀናል፤ ሰውን ሊገድቡት በሚችሉ ሁኔታዎች እየኖረ በምድር በኖረው ሕይወቱ ለውጦች የኑሮው መገለጫ ነበሩ ይልቅኑ እንቅፋቶቹ በተወገደበት ባህርይና ስፍራም ዕድገት ቀጣይነት ኖሮት መታየቱ አይቀሬ ነው፤ ኢየሱስ ሀጢአት የለበትም፤ ፍፁም ነው ግን በምድር ሳለ በሁሉም ዘርፍ ለውጥ ያመጣ ነበር፤ ያድግ ነበር።

1ቆሮ 13፡9-12 ለዚህ ጭብጥ ፍንጭ ሰጪ ነው *«...ነገር ግን ፍፁም የሆነው ሲመጣ በከፊል የነበረው ይሻራል፤ ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ አስብ ነበር እንደ ልጅም አሰላ ነበር፤ ከጎለመስሁ በኋላ ግን የልጅነትን ነገር እርግፍ አድርጌ ትቻለሁ፤ አሁን የምናየው በመስተዋት ውስጥ እንደሚታይ በድንግዝግዝ ነው፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ አሁን የማውቀው በከፊል ነው፤ በዚያንጊዜ እኔ ራሴ ሙሉ በሙሉ የታወቅሁትን ያህል ዐውቃለሁ...»* ማለቱ ለዚህ ቀጣይ ዕድገት መለኪያ ነው።

ያለ ክርስቶስ በሆኑት ላይ መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልፀው ትምህርት ተያያዥ ሆኖ በስነ ፍፃሜ ዝግጅት ላይ አብሮ ይነሳል፤ ይመጣልም፤ መፅሐፍ ቅዱስ ቅጣት ፍርድ መኖሩን በብሉይና በአዲስ ኪዳን በአግባቡ አስተምሯል፤ ይልቁኑ በብሉይ ኪዳን አጥፊዎች፣ አመፀኞች ቅጣታቸውን በምድር በማግኘት ስለሚገለፅ ከምድር ሕይወታቸው ባሻገር ሌላ ፍርድ እንዳለ ለማሰብ አቅም አልፈጠረም፤ አዲስ ኪዳን ግን ከሞት በኋላ ስላለው ቅጣት በግልፅ ይናገራል፤ ይህ ትምህርት ደግሞ በቀዳሚነት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተተንትኗል፤ ኢየሱስ በተደጋጋሚ እግዚአብሔር ነፍስንና ስጋን በሲኦል እንደሚጥል በማቴ 5፡22፣ 29፤10፡28፣ 18፡9 ማርቆስ 9፡43,45 ሉቃ 12፡5 ተናግሯል። ከዚህም የተነሳ «መፍራት የሚገባችሁን አሳያችኋለሁ ከገደለ በኋላ ወደ ገሀነም ለመጣል ስልጣን ያለውን እርሱን ፍሩት» ሉቃ 12፡5 በማለት ተናገረ፤ አስተማረም።

በዚህም ሀጢአት ሊቀጣ እንደሚገባ ሀጢአትን በመስራትና በጌታ የድነት ስራ ላይ በማመፅ መዝለቅም የገሀነም ፍርድ እንዳለበት መረዳት ተገቢ ነው፤ የእግዚአብሔር ፈራጅነት በፅድቅ መንገድ ላይ የተገኙትን ይታደጋል በሀጢአት የፀኑትን ይቀጣል።

ይህ አቀጣጥ የልዩነት ሁነኛ መሰረትን የሚጥለው ኢየሱስን በመታመንና ባለመታመን ሕይወት ወይም ውሳኔ ይለያል።

እግዚአብሔር አብ በዘላለማዊ እቅዱ ያዘጋጀው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሰው ሆኖ መምጣት ነበረበት። በዚህም የሰውን ሀጢአት ተሸከመ፤ በመስቀል ላይ ሞተ፤በሞቱና በትንሳኤው ዲያብሎስን፣ ሞትንና ሀጢአትን አሸነፈ፤ በዚህ ድሉ የተደገፉ እና የታመኑ ከእርሱ ጋር ዕድገታዊ ኑሮን በመንግስቱ ውስጥ በመኖር ይደሰታሉ፤ በትይዩ ያሉት ግን የዘላለም ቅጣት ይገጥማቸዋል።

በርካታ ምሳሌያዊ ገለፃ ገሀነምን በተመለከተ አለን፤ ሀጢአተኞች በእንዴ በእሳት እንደሚጠፉ ወይም እርካታ የለሽ ኑሮን በመኖር በሰቀቀን እንደሚዘልቁ ያስረዳሉ፣ አንዳንዶች ደግሞ ከገሀነም ፍርሀት ለመትረፍ ከሞት በኋላ በሕይወት ያሉ ዘመዶቻቸው በስማቸው በሚያደርጉት ቸርነት ከቅጣት ወደ መንግስተ ሰማይ ከዕለታት በአንዱ ቀን እንደሚጠጉ ወይም እንደሚገቡ ያስተምራሉ።

እነሀ ሁሉ ግን ሰው ሰራሽ ግንዛቤዎች ናቸው። ይልቅኑ ቅጣት በኢየሱስ ላልታመኑ ለሁሉም መኖሩን ማመን የእግዚአብሔር የፅድቅ ፍርድ ነው፤ ሁልጊዜ ውሳኔውን ከእርሱ ፍትህ ጋር በማጣጣም መኖር የክርስቲያኖች ሁነኛ ሐላፊነት ነው። የወንጌል ስራን በመስራት መዝለቁም ተገቢ የሚሆነው እግዚአብሔር ቃሉን አለማጠፉን በማመን የሀዘን ልብንና ፍቅርን በማንገብ ሁነኛ መፍትሄውን ለሰው ሁሉ ማቅረብ ተገቢ በመሆኑ ነው።

ተከታዮቹን ከፍሎች ላለመዘንጋት በመጣር የስነ ፍፃሜን ምንነት በቅጡ እንጠቅልል።

ማቴ 11:22 *ነገር ግን እላችኋለሁ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላቸዋል፤*

ሮሜ 2:14 ሕግ የሌላቸው አህዛብ ከባህርያቸው የህግን ትእዛዝ ሲያደርጉ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤

ሉቃ 16:26 *ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጓል።*

ማቴ 25:46 *እነዚያ ወደ ዘላለም ቅጣት፣ ፃድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ፤*

እርግጥ ነው ኮነር ከ70 ዓመታት በፊት ይህን ምልከታውን በአግባቡ ቢያስተናግድም እርሱን ቀድመውም ሆነ እሱን ተከትለው ያሉ ወገኖች ተቀራራቢ መረዳትን በመያዝ ዘልቀዋል፤ ይህ ደግሞ በመግቢያው ላይ እንዳመለከትኩት ስነ ፍፃሜ ከብዙ የክርስትና መሰረታዊ ትምህርቶች ጋር በመያያዙ ችል የማንለው ትምህርት መሆኑን ያረጋግጣል።

ስነ ፍፃሜ በወንጌል ስርጭት አቅም ላይ እና አማኞች በክርስቶስ የማደግ ብቃት ላይ በቂ ግንዛቤን ስለሚሰጥ በመማር መዝለቃችን የተገቢ ተገቢ ነው፤ በክፍል አንድ ዝግጅት ላይ ሰባውያንን (pretrist) ከመስተዳድራውያን ጋር በማስተያየት በሁለቱም አስተምህሮዎች ላይ ያሉትን ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን ተናበናል፤ በዚያም የተሻለ ግንዛቤን በማግኘት ቤተክርስቲያን የመንፈስ አንድነቷን የምትጠብቅበትን ትምህርትም አይተናል።





በዚህ ዝግጅት ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን የተሰጣት ክርስቶስ ያስተማረውንና በቤተክርስቲያን በአገልግሎት ላይ ሊውሉ የተገባቸውን እውነቶች መግለጥ ስራውና ከብሩ ስለሆነ ይህን በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁሉ ያለልዩነት አንድን እውነት እንደገለጠ ለመረዳት የተዘጋጀ ጥናት ነው።

ከዚህም የተነሳ ሙሉውን ቃለ እግዚአብሔር ለመረዳት ራሱን ለሰጠ ለየትኛውም አማኝ በየትኛውም መንፈሳዊ ትምህርት ላይ አንድና ወጥ እምነት ይዞ የመገኘት አቅም ይኖረዋል።

ይህ ሲባል ደግሞ ለማፍታታት የሚያስቸግሩ አንዳንድ ጭብጦች የሉም ማለት አይደለም፤ የThe Early Days of Christianity ደራሲ F.W Farrar በ1882 በፃፉት መፅሐፋቸው ይህ እንደገጠማቸው ፅፈዋል። ይህንንም በኢየሩሳሌም መውደም The fall of Jerusalem ከገፅ 486-493 ባለው ትንታኔ የታሪክ አቀናባሪው ጆሴፈስም ሆነ ፊሎ በተለያየ አቅጣጫ መዝግበው የተዋቸውን ሰነዶች ላገላበጠ ተመራማሪ መልስ ፈላጊ ሶስት አጨናናቂ ጥያቄዎች ሊገጥሙት እንደሚችሉ አሳውቀዋል፤

**አንዱ** በማቴ 24:34 *«እውነት እላችኋለሁ ይህ ሁሉ እስኪፈፀም ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም» ያለበት ምክንያት በእርግጠኝነት ተፈፃሚ የሆነው በዚያኑ ጊዜ መከረኝነት፣ እልቂትና ውግጂያ ከኢየሩሳሌምና ከቤተመቅደሱ ጋር ተሰልፎ በመጠናቀቁ ይሆንን?*

**ሁለት፡-** በማቴ 16:28 *«እውነት እላችኋለሁ እዚህ ከቆሙት ሰዎች መካከል የሰው ልጅ በመንግስቱ ሲመጣ እስከሚያዩ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አሉ» በማለት ኢየሱስ ያስተማረበት ሁነኛ ጊዜ ከኢየሩሳሌም መፍረስ ጋር በመያያዝ ካልተገለፀ በቀር ለየትኛው ይሆናል? የሚለውና*

**ሶስት፡-** *በማቴ 10:23 «...በአንድ ሰፍራ ሲያሳድዷችሁ ወደ ሌላ ሽሹ እውነት እላችኋለሁ የእስራኤልን ከተሞች ሳታዳርሱ የሰው ልጅ ይመጣል» ያለበት ገለፃ ከ70ው የቤተመቅደስ እና የኢየሩሳሌም መፈራረስ ጋር ካልተያያዘ ከምን ጋር ሊመጣጠን ይችላል? የሚሉት ተሳሳሪ ጥያቄዎች መልስ እንደሚያስፈልጋቸው አልዘነጋም፡ ያሉበትን በዚህም ዝግጅቴ ላመላከት እፈልጋለሁ።*

እርግጥ ነው ከ70 ዓመተ ምህረት ኩነት ጋር ተያያዥ የሆኑ መለኮታዊ አጀንዳዎች ሰፍራቸውን ይዘዋል፤ የቀደመው ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞትና ትንሳኤ ፍፃሜውን ቢያገኝም ያው ኪዳን ግን ዳግመኛ አገልግሎት ላይ ሊውል የሚችልበት ምንም ቀዳዳ አለመኖሩን በማረጋገጥ ለአዲስ ኪዳን ዘላቂነት ዋስትና በመስጠት መሰረትን መጣሉ፣ የእግዚአብሔር ቅጣት ፅኑና አይመለሴ መሆኑ፣ በተለይም ይሁዲነትና እምነት ብሔራዊ መገለጫ አድርገው ለሚያምኑ

እስራኤላውያን ያ ግንዛቤ በክርስቲያናዊ ይዘቶች ሁሉ ውስጥ እየገባ ፍዘትን እንዳይጋብዝ፣ እንዲሁም የሕዝቡ መሪዎች «ፀጋ»ን በመቋቋም ራስነታቸውን በሕዝቡ ላይ ለመጫን በመወሰን «ደሙ በልጅ ልጆቻችን ላይ» ይሁን እስከ ማለት ያደረሳቸው፣ እንዲሁም ቀደም ብሎ ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም በማልቀሱ ኋላም ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ አይቀርም ያለበት ፅኑ ቃል ተፈፃሚነት ያገኘ ዘንድ 70 ዓ.ም መምጣቱ በክርስትና ታሪክ ውስጥ አይረሴ ስፍራ ይይዛል።

በዚህም ኢየሱስ በአማኑኤልነቱ ለብዙዎች መዳን ምክንያት እንደሆነ ለብዙዎች መጥፋትም መንስኤ መሆኑ አይቀሬ ነው፤ የእርሱ በሰዎች መካከል መገኘት ለድነትና ለቅጣት፣ ለበረከትና ለመርገም መሆኑ ከሚገለጥባቸው አንዱ ፅዋው ሲሞላ የሰው ልጅ በቅጣት የሚገለፅ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፤ ይህ ደግሞ ከ70 በፊት ነበረ ከ70 በኋላም ይቀጥላል።

በቀደሙት ገፆች ስለ ትንሳኤ፣ ስለ ፍርድ፣ ስለ መንግስተ ሰማይና ገሀነም እንዲሁም በመጨረሻ ሊሆኑ ስለሚችሉት መጠቅለያዎች የተዘረዘሩት ትምህርቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔያቸው ተገቢ መሆንም በስነ ፍፃሜ ግንዛቤያችን ላይ አዎንታዊ አቅምን ይፈጥርልናል።

## ምዕራፍ 5

## የማጠቃለያ - ድምዳሜ

*በእኛ መልካምን ሥራ የጀመረው እርሱ እስከ ክርስቶስ ኢየሱስ ቀን ድረስ ከፍፃሜ እንደሚያደርሰው እርግጠኛ ነን* (ፊሊ. 1:5) ከዚህም የተነሳ *«...ፍቅራችንም በጥልቅ ዕውቀትና በማስተዋል ሁሉ በዝቶ እንዲትረፈረፍ እፀልያለሁ፤ ይኸውም ከሁሉ የሚሻለውን አይታችሁ እንድታውቁ እስከ ክርስቶስም ቀን ድረስ ንፁና ነቀፋ የሌለባችሁ እንድትሆኑ ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚገኘውን የፅድቅ ፍሬ እንድትሞሉ ነው»* (ፊሊ. 1:9-10) ይህ የፊልጵስዩስ ሰዎች በፍፁም ደስታ ተሞልተው ይኖሩ ዘንድ የተመከሩበት ቃል ነው።

አማኞች በየትኛውም የስነ መለኮት ትምህርት ላይ ቢነጋገሩ፤ ቢመካከሩ እና ቢማማሩ ይህን የማድረጋቸው መነሻው ራሱ እግዚአብሔር ነው። ይህም ድነትን ዳግም በተወለዱት ሁሉ ዘንድ የጀመረው እርሱ ራሱ በመሆኑ የተቀረውን ሁሉ በአግባቡ ይገነዘቡ ዘንድ ሊያግዝ አብሮን አለ፤ በጥልቅ ዕውቀትና ማስተዋል መሞላት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ ይህም ዕውቀት ከእግዚአብሔር የሆነው ሀሳብ ነው፤ ወደ እርሱ ለመድረስ ጥረት ማድረግ፣ ቀርበም ደርሰም መገኘት የዚህ ዝግጅት አካል ነው።

ክርስቶስ ዳግም መጥቷል ወይም ዳግም ይመጣል፤ የማያነጋግር ርዕስ ጉዳይ አይደለም።





ያነጋግራል፤ ያመካክራል፤ በምክሩ ውስጥ ጉዳዩ ሁሉ በቀዳሚነት በቃለ እግዚአብሔር ይመዘናል፤ በነባራዊ ታሪክ እና በሕዝባዊ ትውፊቶች ይፈተሻል፤ እነዚህ ሁሉ አንድ ጉዳይን አጥርቶ ለማየት አስተዋፅኦ አላቸውና ይህ ጥናት ይህንን በግርድፉም ቢሆን አገጣጥሟል።

በመሰረቱ አጠቃላይ ዝግጅታችን ትኩረትን የሰጠው ሙሉ ሰባውያን/Full Preterists ላይ ነው እነርሱ ሁሉም ነገር በ70 ተከናውኗል ስላሉ ተገቢ የሆነ ምጥን ትንታኔ ተሰጥቷል። ከፊል ሰባውያን/Partial Preterists ግን 70 ዓ.ምን የሚወስዱት ኢየሱስ በእስራኤል ሊፈርድ በዚያን ዓመት መጥቷል ግና ትንሳኤ፤ ንጥቀት፤ የጌታ ቀንም ሆነ የመጨረሻ ፍርድ፣ በታሪክ ማጠቃለያ ላይ የጌታ በአካል ዳግም በመመለስ ጊዜ ወደ ፊት መሆኑን በተስፋ ይጠብቃሉ፤ ከእኒህ ጋር ይህ ዝግጅት የከረረ ሙግት የለውም ከፊል መግባባት እንጂ።

ይህ ማጠቃለያ ያስፈለገውም ይህንን ለመጠቆም ነው፤ የጥንት ክርስቲያኖች መለያቸው የነበረው የእግዚአብሔር ቃል ካለው ማለታቸው፤ ካላለው ላለመድፈር ጥንቁቅ ሆነው መኖራቸው ነበር፤ የጥንት ክርስቲያኖች የመንፈሳዊ ሕይወታቸው መለኪያ ድርጊታቸው ነው፤ ይህም «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም ዛሬም ለዘላለሙም ያው ከመሆኑ» የተነሳ ይኖሩበታል (ዕብ 13:6)

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው ልታስብባቸው የሚገቡ በርካታ ጉዳዮች በየጊዜው ይገጥሟታል፤ ያንን የገጠሟትን በአግባቡ ስርታ ለሁሉም በማውረስ መትጋት መለያዋ ነው፤ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ያሉ ክርስቲያኖች በታሪክ ጉዞት ውስጥ አልፈው መጥተዋልና ብዙ የሚጠቅሙ ሀብቶች አሉአቸው፤ እነርሱን በአግባቡ፤ በፍቅር፣ በትህትና እና አንዱ ከሌላው እንደሚሻል በማመን ከያዙት ምንም ነገር በፍፃሜው የሚጠቅምና የሚባርክ ሆኖ ይገኛል።

ቤተ ክርስቲያን ጠቦቶቿን፣ ግልገሎቿን፣ የደረሱ በጎቿን ሁሉ በአቅማቸው ልክ በመድረስ የማሳደግ፣ የመጠበቅም ግዴታ አለባት። ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን በምንም ባለመደናገጧ ትታወቃለች፤ ለምትጠየቀው ብቻ ሳይሆን ላልተጠየቀችበት የነገ ስራዋ ሁሉ ስርታ ትገኛለች። መወያየት መሸናነፍ አይደለም፤ መማማር መደነጋገርም አይደለም፤ ይልቁኑ እንደ ቤሪያ ሰዎች ሁልጊዜ ነገሩ እንዲህ ይሆንን በማለት ቢጋራ የእግዚአብሔርን እውነት ፈላጊ መሆናችን ይታወቅ፤ ይህም ሁል ጊዜ በቀጣይነት ይተግበር።

እንግዲያስ፡- ጌታ ዳግም እስኪመለስ ድረስ ወንጌሉን በመስበክ፣ በቅድስና በመመላለስ፣ የክርስቶስን አካል በመጠበቅ፣ እርስ በርሳችን በትህትና በመተናነፅና እውነትን በፍቅር ለሰው ሁሉ በማድረስ እንበርታ። ይህ ዝግጅት ለበርካቶች ትምህርትን ይሰጣልና በዚህ መፅሐፍ ውስጥ መካተቱ ተፈላጊ ሆኗል።

## አጋዥ የተነበቡ እና ሊነበቡ የሚገባቸው
## የመፀሐፍት ዝርዝሮችና ድረ ገጾች


1. የጥንት እና የመካከለኛ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ - ሰሜ ታደሰ 2002 ዓ.ም
2. የእግዚአብሔር መንግስት ታሪክ በምድር ላይ አንደኛ መፅሐፍ - ዶክተር ምክረ ሥላሴ ገ/አማኑኤል 2000
3. የእረኛው ምርኩዝ - ሰለሞን አሰፋ ቅፅ 1እና2 2000
4. ትምህርተ ክርስቶስ - በቄስ ማንሰል 1997
5. የእግዚአብሔር መንግስት በአፍሪካ - ማርክሾው 2000
6. Understanding Theolgy. R.T.Kendall. V.3.2002 G.C
7. Israel in the New Testament David Powson2009 G.C
8. 2000 Years of Christ's Power N.R.Needham 2004 G.C
9. Judgment Day.Dave Hunt 2005
10. History of the Christian Church.Philip Schaff 4-8 2002 G.C
11. ደቂቀ እስጢፋኖስ - ጌታቸው ኃይሌ 2002
12. መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ለመረዳት - ተከሉ መንገሻ 1993
13. መጽሐፍ ቅዱስ እና እፊታት ስህተቶች - ዘላለም መንግስቱ 2000
14. መጽሐፍ ቅዱስና ዘርኢ ያዕቆብ ኢትዮጵያ 1995
15. The Great Doctrines of The Bible William Evans 1912
16. ትምህርተ መለኮት - ዓሥራት ገብረማሪያም 1983
17. The final Return. David Rushwoth smith 1990 G.C
18. Mathew 24 is fulfilled. John L Pray 2900 G.C
19. A Short introduction to preterism. R.A. Thylor. 2011
20. Christiam History and its preterist presupposition by Chrysostotm Matthew.
   (WWW preteristar chire. Com/preterism
21. A Critique of preterism Henry Hammond
   (WWW.Swad and trower. Org.)







22. The lase Days According to Jesus R.C. Sproul. 1998 G.C
23. Before Jerusalem fell. Kenneth Gentry. 1999 G.C
24. Jewish Antiquities. Flavious Josephus 2006

# ፍልሰት - አፍላሽ እና አሜሪካ

በልሙጡ ለመፃፍ መነሳሳት በአመዛኙ ፀሐፊውን ይጠቅማል፤ ምክንያታዊነቱን አጉልቶ መፃፍ የፈለገ ደግሞ ፀሐፊውንም የመልዕክቱንም ተቀባይ ይብዛም ይነስ ይጠቅማል።

የዛሬ መልዕክቴ መንደርደሪያውን ያመላከተኝ የዳዊት ፀጋዬ **«ማቆሚያ ያለው የማይመስል ፍልሰት»** በማለት በማቴቴስ ቁጥር 19 2004 ያስነበበን ፅሑፍ ነው፤ እሱ በጉዳዩ መክሮበታል፤ አነጋግሮበታል፤ ፀሐፊው የሱን ፈቃድ በስሱ በማኖር እኛን ቀስቅሶናል በተለይም እኔን። መቼም ለመፃፍ የሚጨነቅ ሁሉ ሌላውን ለመጥቀምና ለሌላው ለመኖር እስከሆነ ድረስ የሚነሱ ብዕሮች ሁሉ በልሙጡ ለመፃፍ ቢነሳሱም ውለው አድረው ግን ምክንያታዊ በመሆን አእምሮን በመሰርሰር ለተግባር ሊያበቁ አደራ አለባቸው።

አቅርቦቴ ከማቴቴስ የመነሻ መረጃ በተጨማሪ አራት መፃህፍትን ከዳር ዳር እንድቃኝ አስገድዶኛል፤ይህንን ስል እምነታችንንና የምግባራችንን ሁነኛ መለኪያ መጽሐፍ ቅዱስን ከቁጥሩ ሳላካትት ነው፤ እሱ መነሻም መደምደሚያም መጽሀፍ አይደለም፤ እሱ ሕይወታችንነ ው፤ ኑሮአችን የሚመዘንበት ነው፤ በእኛ ዘንድ ያለውን እርግጠኛ ሐላፊነት አሳውቆናል፤ የሚከተለውንም ተጠያቂነት ገልጦ አሳይቶናል፤ ያሳየናልም ከዚህም የተነሳ በፍልሰት ርዕስ ጉዳይም ሆነ በ«ምንም» ቅዱስ ቃሉን ዋቢ መጥራት ያስፈልጋል። እናም እሱን በአራቱ ውስጥ አላሳለፍኩም የእኔ ምንጭ ሁሉም ስለ «አሜሪካ» የሚተርኩ ናቸው፤ ይህን የመረጥኩትም ማቴቴስ ዝግጅቷ ያዘነበለለት ስለሆነ እና የእኔ ወዳጆች በአመዛኙ ወደ አሜሪካ ስለፈለሱ ነው፤ ሰነዶቹ፡-





1. **የኢትዮጵያውያን ስደትና ኑሮ...በከበደ** ኃይሌ 1996 ዓ.ም
2. **መኖር በአሜሪካ** - ዓለማየሁ ማሞ 1998 ዓ.ም
3. **የእኛ ሰው በአሜሪካ** - ነቢይ መኮንን 2000 ዓ.ም
4. **ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ ማህበራዊና ሥነልቦናዊ ትንተና...** ዶ/ር ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ 2001 ዓ.ም

ከላይ የተዘረዘሩት መፅሐፍት አሜሪካንን በአግባቡ እንድንረዳ መሰረት ጥለዋል፤ ሊፈልሱ ያላቸው፣ የፈለሱ እና ከፍልሰት ለመመለስ የሚያውጠነጥኑ ሁሉ ቢያነቧቸው ይጠቅማሉ፤ እንግዲህ፡-

ገጣሚው ተመስገን አፈወርቅ፤ «የተስፋይቱ ምድር» በማለት የገለፀበትን ሥራውን በቅድሚያ እንብቡ

ጮኾም ለመናገር
ጣጥሮም ለመከበር
ሰድቦም ለማሳፈር
በዲሞክራሲ ፈር
ልክን ለመስፈር
በፈሪ - ደም ሰፈር
ልብን ለመወጋት
በነ «እያውቁ» ሀገር
ወድቆም ለመሰበር
በነ «አዳልጤ» ነገር
ዕድሜም አይጠይቅም
መቅለሉ ይሄ አገር
ዳገትም የለበት
ቁልቁል ለመንደርደር
ሁሉ የቀለለበት
የባረከው መንደር።

(መኖር በአሜሪካ ገፅ 28)

ግጥሙ በርካታ አመላካች ጭብጦችን በውስጡ ይዟል፤ ስለ አሜሪካ በገጣሚው ልክ በማሰብ እኛም ተባባሪ ሆነን «እንዲህ ናት አሜሪካ» ልንል እንችላለን።

አራቱ ፀሐፊያን በአሜሪካ:-

ኪራይ ይወደድ ይሆናል እንጂ የቤት እጦት እንደ ሌለ፣

የሰዓት ክፍያው ይለያይ ይሆናል እንጂ ሥራ አጥ አለመኖሩን፣

ዓለም አቀፋዊ አስተሳሰብ ግር ይለን ይሆናል እንጂ ጠባብነት ስፍራ አለመያዙን፣

የእግዚአብሔርን ለምደን ሴጣን ሲወደስ ይምታታብን ይሆናል እንጂ ሁሉም በዚያ እንዳሉ ይነግሩናል።

ሁሉ በዚያ ካለ ሁሉ ወደዚያ ለመሄድ ቢነሳሳ በቂ ምክንያት አለው ማለት ነው «አሞራዎች ጥንብ ባለበት በዚያ እንደሚሰባሰቡ» ጌታ አስተምሮ የለ።

ግና መሰረታዊ ጭብጥ በዚያ ሁሉ መኖሩ ሳይሆን እነዚያን ሁሉ ተብዬዎች በሙሉ የሰውን ይልቁኑ የኢትዮጵያውያንን መንፈሳዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ስሜታዊም ሆነ አካላዊ ፍላጎቶችን በአግባቡ አሟልተዋል ወይ? የሚለውን ጥያቄ መመለሳቸው ቀዳሚው ሲሆን እርሱን ተለጣቂው ወደዚያ ለመፍለስ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በተለይም በወንጌላውያን አማኞች ዘንድ ትልቁን ሚና የሚጫወተው ማን ነው? ለምንስ? የሚሉትን በግርድፉ ማመላከት ተገቢ ይመስለኛል። ይህን ደግሞ ለመመለስ «በዙሪያ ገቤ» ልብ ያልኳቸውን፣ ለዚህ ዝግጅቴ ስል ጠይቂያቸው ምላሽ በሰጡኝ ሰዎች ላይ እነጣጥራለሁ።

***

ትዳር ከመሰረተ አስራ አራት ዓመቱን ይዟል፤ በላጤነት ዘመኑ ስራን አይንቅም፣ በአገኘው ደስተኛ ነው፤ ራሱን ለማሻሻል ከስራ ስራ ቀያይሯል ከሰርተፍኬት፣ ዲፕሎማ፣ ዲግሪ እያለም በትምህርቱ ከፍ ብሏል፤ በክርስቶስ በመሆኑ ባገኘው ፀጋ ወንድሞችንና እህቶችን አገልግሏል፤ ትዳር መስርቶ የጋብቻ ዕድሜውን እኩሌታ ላይ ሲደርስ ስለ ልጆቹም ሆነ ስለ ባለቤቱ ስለ ስራውም ሆነ ስለነገ ሕይወቱ እያሰላ ውሎ አድሮ ያመጣው መፍትሄ «ወደ ውጭ መሄድ:- አሜሪካ መድረስ ሆነ» ያልታሰበ ነገር መታሰቡ ተቃውሞ ባያደርስም ይህን አስቦት የነበረውን እቅድ ግን ፈጥኖ ተወው፤





የተወውን ደግሞ ባላሰብነው ሰአት አነሳው፤ እኔን በወቅቱ የገረመኝ በስንብት ምሽት ላይ ባለቤቱ «ዛሬ ላይ ባሌ በአሜሪካ የመኖር ሀሳብ አልነበረውም፤ ይህን ማሰብ፣ ማመንም እንደሚገባው ያደረኩት እኔ ነኝ» አለችኝ፤ ይህ ከተገለፀ ከአንድ ሰዓት በኋላ ተቃቅፈን ተለያየን።

***

*የዛሬ ትዳሩን ሳይመሰርት በፊት ዐይኑን ይሆኑኛል ባላቸው ልጃገረዶች ላይ ጥሎ ነበር። እነርሱን ለማፍቀሩ መሰረቱ በየጊዜው መገናኘታቸውና በክርስቶስ መሆናቸው መነሻው ነበር፤ መነሻው መቼም ትውውቅ እና ቅርርብ በኖረ ቁጥር «እኔ እወድሻለሁ አንቺስ» የሚል ጥያቄ ከወንድ ሊቀርብ ይችላል፤ እሱም ለሁለቱ ይህንኑ አቅርቧል፤ አንደኛዋ ያፈቀረውን ሙያውን ለመቀየር ባለ መውደዱ የመቀራረቡ አቅም ሳሰቶ ጉዳዩ በዚያው ቀረ። ሌላኛዋ ደግሞ የፍቅር ጥያቄው ተገቢ ነውርም የሌለበት መሆኑን አረጋገጠችለት አስከትላ ግን አንድ ቀጣይ መርሀ ግብር ኖራት። እሱንም መፈፀም ይኖርባታል። ያም በዙሪያዋ ያሉት የዕድሜ እቻዎቿ ወደ አሜሪካ ዘልቀዋል። እሷም በዚህ ውስጥ መሆን መኖርም እምነቷ ሆኗል። እሷም ይህንኑ አረጋገጠችለት። እሱም ይህን እምነት ተሻግሮ ትዳር መመስረት አልቻለም፤ ይልቅስ እግዚአብሔር ካጣመረው አንድም ካደረገው ጋር ዛሬ አብሮ መኖሩን ተያያዘው።*

***

*መጋቢው ጥሪው ለሀገሩ እንደሆነ፣ ቤተ እምነቱንም እግዚአብሔር የወሰነለት መሆኑን በመግለፅ ለጉባኤው ከአመታት በፊት መስክሮ ነበር። ከዚህም የተነሳ ሕዝቡ ደስተኛ ሆኖ ትምህርቶቹን በትጋት ይከታተላል። በየቤታቸው የተጎበኙ ሁሉም እግዚአብሔር አጥቢያችንን ሙሉ በማድረግ የሚመራን፣ የሚገሰፀን ባይሰጠን ኖሮ በዕድገታችን በቀጨጭን ይላሉ፤ እሱም በሕይወት እስካለ ድረስ በታማኝነቱ እንደሚያግዛቸው በደስታ ይመሰክራል። ልጆቹም አድገው በእሱ እጅ በመጠመቃቸው፣ ወገኖች የሙሴንና የኢያሱን ያድርግለት ይላሉ።*

*በመጋቢው ሌላ ዘመን ውስጥ ግን አንድ ጥሪ ከአሜሪካ ካለች አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቀረበለት «አንተና ቤተሰብህ በዚህ መጥታችሁ ኑሩ አንተም በመጋቢነት አገልግለን» አሉት ምላሹ ፈጣን ነበር። የተጠራሁት በአዲስ*

*አበባ ላለችው ለዚህች አጥቢያ ነው ፈቃደኛ አይደለሁም በማለት አብረውት ለሚያገለግሉ መሪዎች ምላሹን አቀረበ ደስታም ሆነ።*

*ውሎ ሲያድር ግን «ልጆቻችን መማር አለባቸው፣ እስከመቼስ በዚህ ዐይነት ሁኔታ እንቀጥላለን። መጋቢነት በተመቻቸና ባልተመቻቸ ሁኔታ ሲፈፀም ልዩነት አለው» የገዛ ባለቤቱ ጥያቄ ሆነበት ይህን ውዝግብ በቀዳሚነት ለመፍታት የጠሪዋን ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ ፈፀመ፤ በዚያም ራሱን አስገኘ።*

***

*ሦስቱ አባወራዎች ሁለት፣ አራት እና ሶስት ልጆች አሏቸው ሦስቱም ባለቤታቸውንና ልጆቻቸውን ለመጎብኘት በመንፈቅ፣ በሁለት አመት፣ በአራት አመት ወደ ተከፋይ ቤተሰቦቻቸው ወደ አሜሪካ ደርሰው ይመለሳሉ። ሦስቱም በአዲስ አበባ የተሞሸሩ፣ የኖሩ እና ያገለገሉ ቤተሰቦች ናቸው። ከልጆቻቸው ከፊሎቹ በዚሁ ሀገር ተወልደዋል። ከፊሎቹ በአሜሪካ ተወልደዋል ከሦስቱ ቤተሰብ አንዱ በዲቪ ሎተሪ፣ አንዱ በትምህርት፣ ሌላኛው በጉብኝት ስም ተጓጉዘው ኑሮን በአሜሪካ የቀጠሉ ናቸው፤ ሦስቱ አባወራዎች አንደኛቸው በሚስታቸው የመነሻ ምክንያት ሁለቱ በባሎቻቸው የመነሻ ምክንያት በዚያው መቆየትን በመወሰን ለባሎቻቸው ተመላልሰው ቢጎበኟቸው በቂ መሆኑን በማሳወቅ ትዳርን በዚህ መንገዱ ይወጣሉ።*

***

*ውጤታማነት የሁለቱም ተጫጮች የሁል ጊዜ ንግግር ነው፤ የሚጋቡበትን የተቀጠረ አመት ሁለት ጊዜ ቀይረዋል፤ ሶስተኛውን ዘንድሮ ቀጥረውለት በመጠባበቅ ላይ ናቸው፤ ሁለቱም በጋብቻ አማካሪዎቻቸው ፊት ቀርበው ሲወያዩ እሱ 3ኛ ድግሪውን በሀገሩ መስራት ይፈልጋል፤ እሷ በአባቷ የተመቻቸላትን የአሜሪካ ጉዞ ቀዳሚ በማድረግ «ተምረህ እስክትጨርስ ዕድሜ ይሄዳል፤ እንደተጋባን ቀድሜ እሄዳለሁ ለዚያ የሚያስፈልጉትን ሕጋዊ የጋብቻ ሰነዶች ቀድመን እንጨርሳለን፤ የምታፈቅረኝ ከሆነ አመነኝ ልሂድ ከዚያም ትከተለኛለህ» የሚለው ቃል ዛሬም ሳያግባባቸው አለ፤ የምክሩ ማለሳለሻ «ተጋቡ ከዚያ በኋላ የሚሆነውን እግዚአብሔር ያውቃል» መባባሉ አሁን ላይ ጎልቷል፤ እንዲህም አየረገበ ባለበት ለሚስትነት ራሷን ያዘጋጀችው «ስርተን የምናገኝበት፣ ውጤታማ የምንሆንበት፣ በሀገራችን ያሉ አቅም የሌላቸውን አጥቢያዎችን በምናገኘው*





*ገንዘብ ለመደገፍ ስንል ለምን ዋጋ አንከፍልም»ትላለች።*

***

ከላይ ያመለከትኳዋቸው አምስት ያህል ተነባቢዎች ለመነጋገሪያ፣ ለመወያያ እንደሁኔታው ለጥናት መነሻ ይሆናል በሚል እሳቤ የደረጇ ናቸው፤ ሁሉም ውስጥ «ፍልሰት» አለ፤ ሁሉም ውስጥ ሀገርን ለመልቀቅ መነሻ ምክንያት አለ፤ሁሉም ውስጥ ለፍልሰት ዋንኛ ሞጋች ወይም ዋንኛ ወሳኝ አካል አለ፤ እነሱም ሴቶቹ ናቸው፤ ሚስት እና እናት የሆኑት ወይም ገና ሊሆኑ ያላቸው ሴቶች የቀዳሚውን ድርሻ ወስደዋል።

እንዲህ በማስነበቤ ከወንድ አንፃር አይቶት እንጂ ስለ ወንዶችም የምንለው አለ የሚል ምላሽ ሊገጠመኝ ይችላል፤ ይህን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ አልያም መነሻውም መደምደሚያው በቀዳሚነት በዙሪያው ያሉትን ብቻ በመውሰድ ስለሆነ ወንዝ እያሻግርም የሚል ሙግት ሊገጥመኝ ይችላል ይህንንም ለመቋቋም ግትርነት አያጠቃኝም።

ግና ጉዳዩ ከግምት ገብቶ ዙሪያ ገቡ ይፈተሽ ከዚያም ወደልከኛው አቅጣጫ እንምጣ ፍልሰትን ከበርካታ አቅጣጫ ከማየት ዝግጅት ውስጥ እንደ አንዱ ይህንንም በመቁጠር «ይሆንን ብለን» በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ በመፈጠር ላይ ያለውን ቀውስ ወይም በረከት እንቁጠር።

የእኔ አቋም **ቀ[illegible]ስነቱ** ላይ ያደላል፤ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ ሊስተካከሉ የሚገባቸው ተጠኚ ጉዳዮች አሉ። ከበደ ኃይሌ በጥናታቸው ላይ «...አሜሪካን ገብተን ስንኖር አንድም ቀጥ ብለን በመስራት አሊያም ቀጥ ብለን በመማር ላይ ከተሰማራን ዓላማችንን ማሳካት እንችላለን በመስራትና በመማር መካከል ያለው ልዩነት እና ተመሳሳይነት ሲዳሰስ መማር ሞራልን አጎልብቶ በሕዝብ ፊት ተደማጭነትን ያስገኛል። መስራት ገንዘብ ማፍሪያ መሳሪያ ነው። የሁለቱም የመጨረሻ ዓላማቸው ደግሞ ገንዘብ ነው። ከችግር ነፃ ሆነ ምንም ነገር ባይኖርም ከሚያጋጥሙ የዘር፣ የቀለም፣ የአኗኗር ልዩነቶችና የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮች አኳያ ሲታይ አሜሪካን አገር መኖር ብዙ ችግር አለበት...» (ከበደ ገፅ 359) ይህ ድምዳሜ በአሜሪካ ያሉ ወንዶችና ሴቶች በአመዛኙ ገንዘብን ለማግኘት የሚሰሩ የሚኖሩም መሆኑን ያመላክታል። ገንዘብ በአግባቡ ካልተመራ ክርስቲያናዊ እሴቶችን ለማጎልበትም ሆነ ለመፍጠር አይችልም። በአሜሪካም ያሉም ሆኑ በኢትዮጵያ በመኖር የምዕራባውያንን ዓለም በመመኘት የሚኖሩ ሰዎች በየትም የክርስቶስ አምባሳደር በመሆን የመኖር ዓላማን ካነገቡ ፍልሰትን በመነጠል ከገንዘብ እና እሱን ተከትለው ከሚመጡ ዋናቂ ግንዛቤዎች ጋር ያላቸውን አቋም በቅጡ ማጤን አለባቸው።

ዓለማየሁ ማሞ «**መኖር አሜሪካ**» በሚለው መፅሐፍ ላይ «ውሸት ባልነበር ዲቪ ጥሩ ነበር» በሚል ርዕስ ሰዎች ወደ አሜሪካ ለመግባት ሀሰትን በእውነት ልከኝነት በመለወጥ የትኞቹንም እንቅስቃሴዎች ራሳቸውንና የአሜሪካንን መንግስት «ለመሸወድ» በሚያስችል መካሪና አስመካሪ ይመሩታል፤ በማለት የሀሳቡንም አንጓ ከተከታዩ የአዝማሪ ግጥም ጋር አዋድዶታል:-

«ዲቪ አይደርስ መስሎት

የቀበጣጠረው
ይኸው ከተፍ አለ
ምን ጉድጓድ ይዋጠው?
እኔስ መሄዴ ነው
ይብላኝልህ በሉት
በማላገባት ሴት
የጋብቻ ፓስፖርት። (አለማየሁ ገፅ 74)

ይህ ብዙውን ገለፃ ስብስብ አድርጎ የሚይዝ በወንጌላውያኑም ዘንድ ምን ያህሉ ፈላሽ ራሱን በንፅህና አሰናዳ ደግሞም አኖረን ይጠይቃል፤ መፍለስ በክርስቲያኖች ዘንድ በቂ ምክንያታዊነትን መያዝ አለበት፤ እውነትን መሰረት ማድረግ አለበት፤ የመኖርን ትክክለኛ ፍቺም መገንዘብ አለበት።

«**የእኛ ሰው በአሜሪካ**» አዘጋጅ ነቢይ መኮንንም «ይመስለኛል» በማለት በዚያ የስራ ጉብኝቱ የገጠመውንና ያገናዘበውን እንዲህ በማለት ይገልፃል «...ራስን መሸጥ አለመቻል በተለይ የኢትዮጲያውያን ትልቅ ድክመት ይመስለኛል፤ የእኔም ጭምር፤ ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ቱሪዝም ኮሚሽን ድረስ ምን ብዬ ብናገር እራሴንና አገሬን አስተዋውቃለሁ ብሎ ንቃትን ገዝቶ የመራመድ ዘዴ በጣም ያንሰናል የአለመሰልጠን አባዜና በይሉኝታ መያዝ ብቻ ሳይሆን ሀፍረትም ነውርም ያለበት አድርገን እንኖራለን...» (ነብይ ገፅ 85-6) በማለት አቅም የሳሳበትን ክልል ፅፏል፤ ይህ ግንዛቤውን ዶክተር ታደሰ ወልደጊዮርጊስ «**ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ትንታኔ**» መፅሀፍ የበለጠ አጥብቆታል:-

ኢትዮጵያውያን እየፈለሱ ላሉባት አሜሪካ ላለፉት 100 ዓመታት ያመጡት ለውጥ «ምንም» ነው ይላል «...የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ አሜሪካ ውስጥ ገና ራሱን በኅብረተሰብ ደረጃ አላደረጀም፣ የራሱን የሙያም ሆነ የንግድ ዘርፍ ገና አልመሰረተም። ኢትዮጵያና አሜሪካ ባገር ደረጃ የወዳጅነት ግንኙነት ከመሰረቱ ከመቶ ዓመት በላይ ቢሆንም በዚህ በመቶ አመት ግንኙነት ኢትዮጵያ ከአሜሪካ





ያተረፈችው ይኼ ነው የሚባል ከፍተኛ የዕድገትና የስልጣኔ እንቅስቃሴ አልታየም...» (ታደሰ... ገፅ 111-4)

ከዚህም የተነሳ ፍልሰት በማንም ቀስቃሽነት፣ በምንም ዐይነት የጠነከረ ምክንያት ቢከናወን በየትም የፈለሱ «...አሜሪካን መደበቂያ፣ መሸሸጊያ፣ ማኩረፊያ፣ ተራ መከበሪያ ለማድረግ ሳይሆን አዲስ ሀሳብ የምንገበይበት፣ አዲስ አመለካከት የምናዳብርበት፣ ራሳችንን የምንጠይቅበት እና ዕውቀታችንን የምንመረምርበት መድረክ ለማድረግ ካልተሞከረበት ፍልሰቱ ዋጋ የለውም፤ ተፈላጊም አይደለም» (ታደሰ...313)

ከላይ የተዘረዘሩ አመላካች ነጥቦች ሀገርን ለቆ ለመውጣት ወይም ለመሄድ በቂ መሰረታዊ ምክንያት ከመነሻው ሊኖረው ይገባልን እና ለምን እሄዳለሁን? በመመለስ ላይ ያተኩራል።

እኔ ግን ጨምሬ የምለው በክርስቶስ የሆኑ ሰዎች አደራ በላያቸው ላይ አለ፤ እሱም ከተወለዱበት ቀዬ ተነስተው እስከ ዓለም ዳርቻ በደረሱበት ሁሉ ሊሆኑት እና ሊያስተላልፉት የሚገባ መልዕክት አላቸው፤ እሱም የሁሉም ነገር ማዕከል የሆነው ኢየሱስ እና ትምህርቱ ናቸው፤ ኢየሱስ ለዓለም ሀጢአት መፍትሄ የሆነ መድህኒት ነው፤ ኢየሱስ በትምህርቱ ለዓለም አመለካከት፣ እምነት፣ ፍልስፍና እና ስነ ምግባራዊ እሴቶች ሁሉ ላይ ልኩንና ተገቢውን የሰጠ ነው።

አማኞች የትም ይገኙ:- ኑሮአቸውን እያሻሻሉ፣ ሌሎችን እያገዙ በዋናነት ግን ብርሀን ሆነው መገኘታቸውን በየዕለቱ ማረጋገጥ አለባቸው። ብርሀንነት ቤተሰብን በመጠበቅ በመንከባከብ፣ በአንድ በመኖር ይገለጣል። እንኪያስ በፍልሰት የተፋቱ፣ የተራራቁ፣ የተለያዩ ወይም ዳር ዳር ያሉ ፅኑ ምላሽን መስጠት አለባቸው። በእኔ እምነት ለችግሩ መንስኤ የሆኑት ቅድሚያውን በመውሰዱ መፍትሔ ማቀበል አለባቸው።

*ፍልሰት የህይወት ዘይቤ ነው፤ ዘይቤነቱ ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ሲፀና እና በፅድቅ መንገድ ላይ ሲገኙበት ብቻ ነው፤ በተጭበረበረ የሀጢአት ጎዳና ላይ እግዚአብሔር አይተባበርበትም ከዚህም የተነሳ በየአቅጣጫው ንስሀን ዋቢ መጥራት ተገቢ ነው።*

አልያ ክርስቲያን እንዳልሆኑ በመቁጠር፣ ወቃሽ እንደሌለው ሰው በመሆን ያለ እግዚአብሔር እንደሆኑ በመቁጠር መጠራት ይሻል ይሆናል።

ማሳሰቢያዬ አሜሪካንንም ሆነ የምንማልልበትን የትኛውንም ዓለም «ገነት አድርገን የምንቆጥርበት የፈላ ምኞት ኖሮን ቢሆን፣ ስለ ትዳራችንም መስዋዕትነትን ለመክፈል በሚወሰድ ውሳኔ ላይ ተገኝተን ቢሆን፣ ለወጥ ልናመጣበት የሚገባውን ቀዳሚ የማንነት ጥያቄ ባለመመለስ

ዘግይተን ወይም ትተነው ቢሆን፣ «ምን አገባችሁ» በሚል አቋም ለራሳችን ራሳችንን ሸመንለት ቢሆን፣ ቆም እንበል ከዚያም ዛሬውኑ፡- በሕይወት ሳለን ተገቢ የሆነውን አቋም እንውሰድ።

**የመመካከሪያ ነጥቦቹ**

1. *ሀገርን ለመልቀቅ የሚያበቃ ክርስቲያናዊ ምክንያት አለን? ካለ ምን?*
2. *ስለ አሜሪካም ሆነ ስለ ሌሎች ሀገራት ቀድመን ልናውቃቸው የሚገቡ መሰረታዊ ዕውቀቶች ምን ምን ናቸው?*
3. *ለአብዛኛው ፍልሰት የ«ቤቶች» መነሳሳት ቀዳሚ ድርሻውን ወሰዷል? ለምን?*
4. *በተሄደበት ክርስቲያናዊ ተልዕኮን ያልፈፀመ አማኝ ባይሄድስ?*
5. *ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ ላለፉት 100 ዓመታት መሰረታዊ ለውጥ ያላመጡት ከምን የተነሳ ነው? ከዚህ በኋላ መፍለሱስ ለምን?*



# «የአገድ አራሽ ንግግር» ኦሌ ኤሪክሰን 1928አ.ም.

ምጥን መልዕክቴን በሁለት ግጥሞች ብጀምርስ፤ የምታነቧቸውን ግጥሞች ደግሞ የገጠመው ደረጃ በላይነህ ነው፤ እኔም የዘረፍኩት ከ **«እድሜ መንገድ»** መፅሐፍ ነው።

የአፍ ዘመቻ
ለውጥ እናምጣ ዲስኩር
ስብሰባ ተጠርቶ ፋይሉ ተከፍቶ
ሁል ጊዜ ጥሩንባ ሁልጊዜ ቀራርቶ
ጠዋትና ማታ
ስንት ዓመት ቆጠረች
ቅንጣት መሰናከል ደጃችን ተኘታ? (ገፅ 9)

***

ልዩነት
አባቴ በኩራት ታሪኩን ሲነግረኝ
አራት አምስት ጋሻ አገር ቤት ነበረኝ፣
ብሎ ነበር ያለኝ
አሁን ወጣቲቱ ጓደኛዬ...
ስታወራኝ በመኩራራት
አሜሪካ አራት ያህል ዘመድ አላት (ገፅ 17)

***

ዘመቻ በስፋት በየት ይካሄዳል ቢባል በመንግስት ቤት ሳይሆን በቤተክርስቲያን ይመስለኛል፤ ብዙ

«አድርጉዎች» ብዙ «ንስሆ ግቡዎች» ብዙ «ተቀደሱ እና ብዙ «ብርሀንና ጨው ሁኑዎች» ቢያንስ በእሁድ በየሰባኪው ይቀርባል፤ ከዚህም የተነሳ ለዘመቻው የሚያነሳሳው አቅመኛ እግዚአብሔር አብሮ ተነሺ ነውና ሕዝበ ክርስቲያን የተባበረ ሰው በመሆን ለውጥን ማምጣት ይጠበቅበታል፤ ይህ ውጤት ሳይመጣ ከቀረ ግን ዘመቻው «የአፍ ዘመቻ» ተብሎ ቢጠራ ማንም ተቃዋሚ መሆን የለበትም፤ ሰባኪውም ተሰባኪውም «ቅንጣት መሰናከል ከደጃቸው ያላቸውን ሳያነሱ ዕድሜ ዘመናቸውን «እንለወጥ» ብለዋልና ተጠያቂ ናቸው፤ለውጥ ስለተፃፈለትና ስለተደሰኮረለት አይመጣም፤ ንስሀ ግላዊ እና ማህበራዊ የለውጥ አቅምን አስከትሎ ካልመጣ ንስሀው በእግዚአብሔርም በሰውም ዘንድ ዋጋ የለውም፤ ገጣሚው ደረጀ በላይነህ ያየውን አይቷል፤ ለበርካታ አመታት መታረም ያለበት ቀላል ስራ ሳይታረም በዐይናቸው እየታየ ስለተተወው ኮንኗል፤ በአጭሩ መልዕክቱ የአፍ ዘመቻው በብቻው ለውጥ አይሆንም የሚል ነው።

ከዚሁ ጋር ተያያዥ የእኛ ባላደረግነው ባለፈውና በእነርሱ ነገር የእኛ መኩራራት ግብዝነት መሆኑን ነው ያረጋገጠው፤ የ«ልዩነት» ግጥም መሰረት ጣይ ትምህርት አለው፤ ዛሬ በእጃችን ላይ ላለው አኗኗር ምንም አስተዋፅኦ የሌለውን የነበረን እና የነበረኝን ተረት የሚተርትልኝ አባቴ በኩራት መናገሩን ማቆም አለበት፤ ምክንያቱም አላረሰበት፤ ለውጥ አላመጣበት፤ የዛሬዋ ሴትም አፏን መሰብሰብ አለባት፣ ያኩራራት በአሜሪካ ያሉት ዘመዶቿ ዛሬ ላይ ቅዠታዊ ጥገኝነትን ፈጥረውላት ካልሆነ በቀር በአጠገቧ ያለው የሚታየው «አጋሯ» ምን ያህን እንደሚበልጥ? የረገጠቻትም ምድር ምን ያህል ፍሬያማ መሆኗን በማወቅ ለአብሮ መስራት፣ ለአብሮ መኖር፣ ለአብሮ ብርሀን ወደሚኮንበት አቅጣጫ መዞር ግድ ነው፤ አልያ ፍሬያማነት በሰው ዘንድ አይገኝም፤ ሊሆንለት የሚችለው አፈኛነትና አጉል መኩራራት ብቻ ነው።

ከዚህ ግን መውጣት ይቻላል፤ እሱም ትናንትን ጠንቅቆ በመረዳት ዛሬን በውል በመገንዘብ ነገን ለቀጣይ ውጤታማነት በመስራት በርካታ «ውጤትን» በቀናው መንገድ ላይ ማስገኘት ይችላል።

ሰዎች «ካፍ ዘመቻና ከአጉል መኩራራት ወጥተው ራሳቸውን፣ ማህበረሰባቸውን፣ አጥቢያቸውንና ሀገራቸውን በስፋትም አለምን የሚጠቅሙ ሆነው ለማለፍ መዘጋጀት አለብን።

እኔ ደግሞ እንዲህ ሆነው ያለፉ ሰው አውቃለሁ። ስውዲናዊው አሌ ኤሪክሰን፤ ሰውየውለኢትዮጵያ ሸክም ኖሯቸው በኢትዮጵያ ተገኝተዋል። ሰውዬው ለውጥን መደስኮር ሳይሆን ማመንና መኖር ብቻ ያዋጣል በማለት ክርስቶስ በሕይወታቸው የሰራው የድነት ስራ ደንቋቸው ያንን ለማሻገር በዚህች አገር በለጋ ዕድሜያቸው ተገኝተው በመኖር አማርኛን ተካኑ፤ ኖረው ከሕዝቡ ጋር የቀለም ለውጥ ካልሆነ በቀር ሁሉን በመሆን ኖረው በ1928 ዓ.ም የዛሬ 80 ዓመት **«ያንድ አራሽ**





**ንግግር»** በማለት መፅሐፍ ፃፉልን፤ ይኸው መፅሐፍ በምስራች ድምፅ ሥነ ፅሑፍ ክፍል በ1965 በድጋሚ ታትሟል

ሰውየው በገዛ ዘመኑ ለእንግሊዝ ብቻ ሳይሆን ለመላው እንግሊዝኛ ተናጋሪ ሕዝብ የሚጠቅም ስራን ሰርቶ ያለፈውን ስፐርጅንን ይወዱታል። በጎ አቅምን በሕይወታቸው እሱ አኑሯል። እሳቸው ስራውን አንብበው። ከቅዱስ ቃሉ ጋር የተጣጣመውን ለይተው። ተጠቅሜ ዝም ብል ነውረኛው እኔ ነኝ ብለው የተረዱትን የየገዛ መልዕክታቸውን ከታዋቂው ሰባኪ ትምህርቶች ጋር በማሰናሰል በውብ ቋንቋ ፃፉልን። ታዲያ የአሌ ኤሪክሰንን አገላለፅ ባየሁ ቁጥር «አማርኛ ድሮ ቀረ» እስከምል ደርሻለሁ።

ከዚህም የተነሳ እኔ ለምን ከ«አንድ አራሽ ንግግር» ያለምንም ማብራሪያ ከአብዛኞቹ ጥቂቱን ብቻ በመውሰድ ከየርዕስ ነገሩ አንዲት ነጠላ አንቀፅ ብቻ በማስነበብ እናንተን አላስተዋውቅም፤-

<u>**ቤታችን**</u>

*«ቤታችን» የሚል ቃል እንደ ቅኔ ሆኖ ደስ ያሰኛል፤ ልባችንን የሚነካ እንደ ቤተክርስቲያን ደወልና እንደ ሰርግ እልልታ ይመስለኛል፤ ቤታችን በሰንበሌጥ የተከደነ፣ የተዋረደ ጎጆ ቢሆን ቤታችን ስለሆነ ከሌላ ቤት ሁሉ ይልቅ እንወደዋለን... ታናናሾች የሚያድጉበት ቤት ከሁሉ ይልቅ ቁም ነገር ያለው ማኅበር ነው። በሰዎች ቤት ፅድቅ ቢያድር መንግስትም እንዲሁ በፅድቅ ይመራል፤ እንዳገር ቤቶች ይሆናል፤ ስለዚህ ልጆቻቸውን በመልካም አስተዳደግ የሚያሳድጉ ወላጆች መንግስትና አገርን የሚጠቅሙ የሕዝብ ባለሞያዎች ናቸው...»* (ገፅ 8-11)

<u>**ልግመኛው**</u>

*«መንፈሳዊ ቸልተኝነትንና ልግም ደግሞ አንድ ናቸው መፅሐፍ በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ ደኅንነታችሁን ፈፅሙ ብሎ ይመክረናል፤ አንዳንዱ ግን ብርን ለማግኘት ይቅበጠበጣል፤ መንፈሳዊ ባለጠግነትን ለማግኘት ግን አንድን ጣት አያንቀሳቅስም... እነርሱ ስለ ነፍሳቸውደኅንነት ቤተ ክርስቲያናቸው ልታስብላቸው ይከጅላሉ፤ መንፈሳቸው በዚህ ልግመኝነትን መርጧልና ይደነዝዛል፤ የገዛ ራሱን ሊያቆም የማይወድ መጥፎ አንገተ ሩጉም ይሁን፤ የደንነት ዕውቀት በገዛ ቋንቋቸው ቀርቦላቸው ሳለ ችላ ብለው ያዩታል፤ ወስፌ ቢለግም ቅቤን እንኳን አይወጋም...»* (ገፅ 12-15)

<u>**ጠንካራነት**</u>

*... የሚፈልጉትን አውቀው አሳባቸውን ሳይለውጡ በተረዱበት እውነት ሳይነቃነቁ የሚፀኑ ሰዎች*

ስለክርስቶስ መከራ እየተቀበሉ ሰማዕታት እንኳ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ዳሩ ግን ጭንቅላት የሌላቸው የጠመሙ ዕብሪተኞች በስህተታቸው ቢፀኑ ከርሳቸው ጋር አብረው የሚኖሩትን ወይም በስራ ከእነርሱ ጋር የተቆራኙትን ሰዎች መከራ አጥግበው ሰማዕታት ያደርጓቸዋል... ለሕፃናትና ለልጆች ፍቅርና ጠንካራነትን ማሳየት ያስፈልጋል፤..(ገፅ 17-19)

## ተስፋ

... ተስፋችንን የምንመሰርትበት ፅኑና ለዘላለም የማይናወጥ አለት ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። የዓለም ሁሉ ተስፋ ወደ እርሱ ወደ መድኀኒያለም ነው የሚንጠራራ። በእርሱ ብናምን የዘላለም ሕይወት አለን፤ ይህ ባለጠግነት በእጃችን የተሰጠን ነው እንጂ ለማግኘት ተስፋ የምናደርገው ነገር አይደለም... በዚያ የሚኖር በአንድ ነገር እንኳ አይገባባም በዚያ ቁም በሕይወት ቢሆን በሞት የሚያሸንፈው አንድ እንኳ እንደሌለ እርግጠኛ ተስፋ ነው፤ ከንቱ ተስፋ በበሰባሳ መሰላል የሚወጣ ሰው ወድቆ አንገቱ ይወላገዳል ይሰበራልም የገዛ ነፍስህን የምትወድ ከሆን በዚያ መውጣት አትሞክር። (ገፅ 37-41)

## የተመቸውን ጊዜ ስለ ማሳለፍ

የተመቸውን ጊዜ ዘወትር በከንቱ የሚያሳልፍ ወዝጋቢዎችና ወዘፍዛፎች አሉ፤ ባቡር ሲነሳ ይተኛሉ ቸኩለው ተነስተሰው እያተፈተፉ እንደ ውሻ ከልፍልፍ ውትፍትፍ እያሉ ወደ ባቡር መሳፈሪያ ሲደርሱ ባቡሩ ጭልጥ ብሎ ሄዶ ይቆያቸዋል ዓይናቸውንም እያሻሹ «አዬ ሰዓቴ በሌሊት ተኝቶ ኑሮአል» ይላሉ... ብዙዎች የኢትዮጵያ ምሳሌዎች ግን የተመቸውን ጊዜ እየጠበቅን እንድንጠቀምበት ይመከሩናል «አባት ሳለ አጊጥ፣ ጀምበር ሳለ ሩጥ፣ ዳኛ ሲገኝ ተናገር፣ ውሃ ሲጠራ ተሻገር፣ ቃልህ ሳይዘጋ እግርህ ሳይዘረጋ» በማለት ይመክራሉ። (ገፅ 48-51)

## ሐሜት

ከሰው ከፉ የሚያማ፣ ከእንጨት ከፉ ጠማማ፣ ባልንጀራህ ቢታማ ለእኔ ብለህ ስማ፣ የሚያማ ጠበኛ ዘወር ይበል ከእኛ... ሐሜት ምንም እንኳ ለሐሜተኛ ጨዋታ ቢመስለው ለሚታማው ሰው ግን የሚገድል ፈንግል፣ የሚያቆስል ጦር ይሆንበታል፤ በመርዛሙ ምላሳችን ነድፈን ሰውን ልንገድል እንችላለን፤ ሰውን የምንገድል በአፍ እንጂ በእጅ ብቻ አይደለም።(ገፅ 52-57)

## አእምሮ የሌላቸው ሰዎች

የዓለምን ምስጢር ሁሉ ፈፅመው ያወቁ የሚመስሉ እውቀት የሌላቸው ጉብሎች ሊቃውንት አሉ፤ ሰንዴን ከገብስ አይለዩም፤ በርበሬ ከትልቅ ዛፍ የሚለቅም፣ በሬ የሚታለብ ይመስላቸዋል፣ ውስጠ ነገሩ እንዲህ ሆኖ ሳለ ከዕውቀታቸው ከፍታ አቁልቁለው ያልተማረውን መንጋ በንቀት ይመለከታሉ፣





ባዳ ቋንቋ እየተንተባተበ ከማንም ጎፉፉ ገበሬ የበለጠ ቢመስለው እጅግ ስቷል፤ ይህ ቦልቧላ ግዙፍ ተቀጭቶ ቢቀር ማንንም አይጎዳም፤ ሰራተኛና ገበሬ ቢሞት ግን የመንግስትና ያገር ጎዳት ነው፤ ማንበብና መፃፍ ባይችል ሊያርስ፣ ሊመነጥር፣ ሊዘራ፣ ሊያጭድ ይችላል፤ ለመንግስት እየገበረ ሚስቱንና ልጆቹን በስራው ይመግባል፤ ከቡር ስለሆነ ለጥለጥ ብለህ ሰላምታ ስጠው ምንም ሳይማር ባለማወቅ መኖር የስንፍና ምልክት ነው፤ ከነገር ሁሉ የሚብስ ግን ስራን አለመማር ነው (ገፅ 80-86)

## የሴቶች ምስጋና

ስለ ሴቶችና ስለጠባያቸው የሚናገሩ ብዙ የጥንት ዘመን ምሳሌዎች በኢትዮጵያ ይገኛሉ፤«... ከሴት መምከር ደግሶ መስከር፣ ሴት ገበያ ቢመቻት ልጇን ትሸጣለች... የሴት ቀውላላ አንዱን ጥላ አንዱን አንጠልጥላ...» እነዚህ ምሳሌዎች በምፀትና በሽሙጥ በቀድሞ ዘመን ስለነበሩ ሴቶች ይናገሩ እንጂ ስላሁኑ ስለ ጠቢባን ሴቶች የሚናገሩ አይመስለኝም፤ ይልቅስ የሚንቃቃና የሚንጣጣ ይልቁንም የበሰበሰው ቅርንጫፍ ነው። ወንዶች ስለ ከፉ ከፋትን በሴቶች ላይ ላከኩ መጽሐፍ ቅዱስ ከኢዮብ ሚስት፣ ከንጉስ አክአብ ሚስት ከኤልዛቤል በቀር መቼ ስለከፉዎች ሴቶች ተረከ (ገፅ 90-95)

## የመቃብር መታሰቢያ

«ስም ከመቃብር ላይ፣ ልብስ ያምራል በሰው ላይ፡- ሰው ሁሉ በሕይወቱ ሳለ በጎረቤቶቹ መካከል ለራሱ መታሰቢያን ማቆም ይገባዋል። ሙቶ ቶሎ የሚረሳ ሰው ነፍላላና ምናምንቴ መልጓዳ መሆኑ አይቀርም... በሞታችን አንድ እንኳ ባያዝንልንና ባያለቅስልን ለአንድ ሰው እንኳ ወረታ አልዋልንም ማለት ነው...በመቃብር ላይ ውድ የሆነውን የመታሰቢያ ድንጋይ ከማቆም በምድር ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ወንጌልን መስበክ፣ ድሆችን መርዳት ይሻላል፤ ሙታንንም ከማመስገን ሕያዋንን ማስተገን ይሻላል።

«...ጊዜው ገስግሶ እንደ ወፍ ይበራል
ሰው እንዳበባ ወይቦ ይጠወልጋል
ክብረቱ ሁሉ ይመነምናል
ኃይሉም ይደገድጋል።
ጎበዝ ተቀጭቶ ይቀራል
ከወደደው ይነጠላል
ሞት ሁሉን ይነጥቃል
በዓለም ያለ ሁሉ ይጠፋል
የአምላክ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል (ገፅ 95-100)

በ አሌ ኤሪክሰን «ያንድ አራሽ ንግግር» መፅሐፍ ውስጥ በርካታ ርዕሰ ነገሮች ተስተናግደዋል፤ እኔ ግን ጥቂቱን መረጥኩ። ከእነርሱም ከአንድ አንቀፅ ያልበለጠ ፅሑፍ ብቻ አስነበብኩኝ ከንባቡ በመነሳት ብቻ የቋንቋ አጠቃቀሙን፣ የመልዕክቱን ግልፅነት፣ የአወቃቀር ስልቱን እንድናደንቅ ብቻ ሳይሆን በመፅሐፉ መደምደሚያ ላይ:-

*«... በዓለም ያለ ሁሉ ይጠፋል፤*

*የአምላክ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል።»* በሚል ስንኝ የደመደመበት የቅዱሳት መፅሐፍት ወሳኝነት የማይታለፈው ጭብጥ ሆኗል፤ የእግዚአብሔር ቃል ሊነበብ፣ ሊብላላ፣ ሊጠና ሊኖርበት የሚገባ የዓለም ሀብት ነው፤ ለኢትዮጵያም የተሰጠ ክቡር ስጦታ ነው፤ ይልቁኑ በኢትዮጵያ ያሉ ክርስቲያኖች በ66 ቅዱሳን መፅሐፍት ሊመሩበት፣ የሚችሉበት ሁነኛው ምክንያት እሱ ለዘላለም በመኖር ሁሉን ለፅድቅ ስለሚያበቃ ነው።

ይህን ሁሉ ግን ከ80 ዓመት በፊት በተፃፈው የአማርኛ መፅሐፍ ውስጥ መገኘቱ አያስገርምም? እግዚአብሔር በየጊዜው ሐላፊነታቸውን በወጉ የሚወጡ አማኞች እንዳሉትስ ይህ አያስረዳም? እግዚአብሔርስ ሰዎች በገዛ ቸልተኝነታቸው ተጠያቂ ሲሆኑ እንደሚገባ አላደረገም? ለእነዚህ ምላሹ ያስገርማል፤ ያስረዳል፤ አድርጓልም ነው።

እንግዲህ ደረጃ በላይነህ እንዳመለከተን እኛ ዘመነኞች ክርስቲያኖች ነን ብለን ደፍረን የምንናገር ከሆነ ስለለውጥ ንስሀ ገባን ካልን ቀረርቶውን በመተው ግርግሩን ቸል በማለት ከደጃችን ተኝታ ያለችውን የዘወትር መሰናከል በማስወገድ የከበረውን ስራ ሰርተን እንገኝ፤ ኩራታችን በጌታ ላይ መጠጋት ብቻ እንጂ በዘራችን፣ በወገናችን፣ በቋንቋችን፣ «በአሜሪካችን» አይሁንብን።

ከዚህ ተነጥለን ስንቆም ብርሀንና ጨውነታችን በስራ ላይ ውሎ በርካታ የተሻሉ አሌ ኤሪክሰንን ያስገኝልናል።

እንግዲህ በመሞታችን ቀን ከበጎ ስራችንንና ድካማችን የተነሳ የሚያለቅስልን፣ የሚያስታውሰንና የሚያነብልን ሀብት ትተን ለማለፍ በስራ ላይ እንሁን፤



# ቅይማት

## መግቢያ

አማኞች «አይነኬ» በመሰሉ መንፈሳዊ ርዕሶች ላይ መመካከርን፣ መማማርን ምርጫቸው ማድረግ አለባቸው። ይህን ለመፈፀም መጣር ደግሞ በብዙ ያስመሰግናል፤ የእግዚአብሔር ቃል ለመምከርና ለመገሰፅ፣ ለማቅናት እና ቀጥተኛውን ዕውቀት ለመስጠት ሙሉ አቅም እስካለው ድረስ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መነጋገር ያስመሰግናል። የዚህም ዝግጅት ዋንኛው ዓላማ ቅዱሳን በህብረት ቢቀመጡ መፍትሄ አያጡም፤ ይጠቃቀማሉ፤ ይተናነፃሉም ይህም የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ በቅይማት ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንመክራለን።

## አቀነባበር

ሀሳብን በትክክል ለመግለፅ:- ቁጭ ብሎ ራስን ማየት ይገባል፤ ከዚህም የተነሳ ጊዜ ወስጂያለሁ፤ ራሴንም አድምጬያለሁ፤ ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ የኢዮብን መጽሐፍ እንዳጠና፤ በኤስ.አይ.ኤም. አሳታሚነት የተነበበውን **ቅይማትን** እንድከልስ እና «**ሰማዩ ዝም ሲል**»ን እንዳነብ ሆኖለሁ፤ በተያያዥ የሚነገርለት ሰውን እንዲሁም ገድሉ ከፍ ከፍ የሚልለትን እግዚአብሔርን ከቅዱስ ቃሉ አኳያ በማጥናት ግልጠት ያለው ንባብ አቀናብር ዘንድ ፈልጌያለሁ። ፍላጎቴ ውጤታማ እንዲሆን «መቀየምን» በመተርጎም እጀምራለሁ።

## የማሳሰቢያ አቅጣጫ

ትምህርት ባለበት ቦታ የአስተሳሰብ ለውጥ ይከሰታል፤ ያላወቁትን በማወቅ፤ ያወቁትን

በማፅናት፣ ልብ ያላሉትን በማስተዋል የድርጊት ሰው መሆንን ትምህርት ያስገኛል።

ይህንን ለማምጣት፡- በቋንቋችን መፅሐፍት አሉ፤ ይልቁኑ መጽሐፍ ቅዱስ ከእጃችን ተገኝቷል፤ ሊገልጡ፣ ሊመክሩ የሚችሉ አስተማሪዎች ከእግዚአብሔር ተሰጥተዋል፤ ከዚህ ሁሉ በላይ መንፈስ ቅዱስ አብርሆትን ለመስጠት በዳግም በተወለዱ አማንያን ሕይወት ውስጥ ይሰራል፤ ከዚህም የተነሳ፡- በእጃችን ያለውን ሁሉ እንጠቀምበት ዘንድ ይህ ዝግጅት የማሳሰቢያ አቅጣጫን ያጣቁማል።

ተያያዡ ማሳሰቢያ፡- እግዚአብሔር በእጃችን ይዘነው የኖርነው መልሚያችንን ሳይሆን መጥፊያችን ከሆነ ያንን ፈጥነን እንጥል ዘንድ ይፈልጋል። ይህም ሌላኛው የማሳሰቢያ አቅጣጫ ነው።

በመጨረሻም፡- ሁል ጊዜ ያቀድነው ፕሮግራም በዕለቱና በሰዓቱ መቅረቡ ላይ ከማተኮር አልፈን ዝግጅታችን በሕይወታችን ምንን ለውጥ አመጣ? ለሚለው ጥያቄ እጅ መስጠቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ ለዚህ ደግሞ ትሁት ልብ፣ፅኑ ፍቅር፣ የሚማር መንፈስ ከሁላችን በቀዳሚነት ይፈለጋል።

## <u>መቀየም ማነን? ከምን?</u>

**በመደበኛ** መዝገበ ቃላት ውስጥ «ቅይማት» የሚለውን ቃል ብንፈልግ አናገኘውም፤ በሰያሜው ውስጥ ግን ከሕይወታችን ጋር ተጋምዶ የሚኖር መገለጫን እንደያዘ ስለምንገምት ይገባናል፤ «መቀየም፣ ቅያሜ፣ ቀየመ» ግን ታዋቂ ነው።

በስምነት የገለፀበትን «ቂም» ቅድሚያ በመስጠት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፤ ያዘጋጀው **የአማርኛ መዝገበ ቃላት** በገፅ 182 ላይ እንደሚከተለው ያመለከተናል።

ቂም፡- በደል የተፈፀመበት ሰው፣ በተፈፀመበት በደል ምክንያት የሚይዘው የቁጭት፣ የጥላቻ፣ የቁርሾ፣ ስሜት፤ ቂሙን ተወጣ፡- ተበቀለ፤ የበቀል እርምጃ ወሰደ።

ቂም ያዘ፡- 1. አቄመ፡- በተደረገበት በደል ምክንያት የቁጭት የጥላቻ የበቀል ስሜት አደረበት፣

2. ቂም የያዘ፡- የተፈፀመበትን በደል ያልረሳ ጠበኛ፣

ተቀየመ (ግ) በደረሰበት ወይም በተፈፀመበት በደል ምክንያት ተከፋ፣ ጥላቻ፣ ቅሬታ አደረበት፣ አኮረፈ... በማለት ይተረጉማል፤ ያብራራል።

«ቅይማት» የመነሻ ትርጉሙን ወይም መለኪያውን ያገኘው እነኚህን ከመሳሰሉት ነው።





እነርሱ ሁሉ ግን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በገጠመው የሚሆንበትን ሳይሆን ያብራሩት። ሰው ከሰው ጋር በሚኖረው ተራክቦ የተፈጠረውን ሁኔታ ገላጭ ነው።

ይህ ዝግጅት ግን መነሻውንም መድረሻውንም የሚያደርገው ከሕያው እግዚአብሔር ጋር ነው፤ ሰው እግዚአብሔርን ሲቀየም፣ በመቀየሙም ፀንቶ ሲኖር፣ ለዚያም በቂ ምክንያት ሲያቀርብ በሚሆነው ላይ እንመከራለን። ተዲያ ምክክሩ ፍሬያማ እንዲሆን፡-

- ሀ. እግዚአብሔርን የሚቀየመው ሰው እሱ ራሱ ማነው?
- ለ. በሰው ቅይማትን ያተረፈው እግዚአብሔርስ ማነው;
- ሐ. እግዚአብሔርን ለመቀየም የቻሉ ወይም የመቻል ዝንባሌ ያላቸው ቅዱሳን ነበሩ ወይ?
- መ. መጽሐፈ ኢዮብ፣ ከ66ቱ መጽሐፍት፣ ቅይማት፣ ከፊሊፕ ያንሲ ስራዎች እንዲሁም «ሰማዩ ዝም ሲል» ከጳውሎስ ፈቃዱ በተሰሩ ስራዎች ላይ መለስ ቀለስ ማለትስ ለምን አስፈለገ?ን በመመለስ አብረን እንቆያለን።

## ሀ. እግዚአብሔርን የሚቀየም ሰው ማንነት

ርዕስ ጉዳዩ በሰው ከሰው የተነሳ ስለሆነ፡- የሰውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገለፃ እና ዙሪያ ገባዊ ማንነቱን ሰነድ እየጠቀስን እናመላከት «እግዚአብሔርም አለ ሰውን <u>በመልካችን</u> እንደ <u>ምሳሌችንእንፍጠር፤</u> ምድርን ሁሉ...ይግዙ እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ <u>ፈጠረው</u> ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው እግዚአብሔርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው...ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም...» ዘፍ 1:26-28 ይህ ገለፃ መነሻ ነው፤ ሁነኛ መንደርደሪያ ነው። ይህንኑ ጭብጥ ዘፍ 5:1፣ 9:6፣ 1ቆሮ 11:7፤ 15:49 ያዕ 3:9 ያፀናሉ።

በገለፃው እግዚአብሔር ሰው አለመሆኑን፤ ሰውም እግዚአብሔር አለመሆኑን በመረዳት መነሻን የሚያቀብለው ጥቅስ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሊያቀራርበው የሚችል ፍንጭ እንዳለ አስተምሯል፤ ያንንም መልክ እና ምሳሌ በማለት አስቀምጦታል።

ፍችውን ለመገንዘብ በዘፍ. 5:3 «አዳም ልጁን <u>በምሳሌው</u> እንደ <u>መልኩ</u> ወለደው» በማለቱ የተሰመረባቸው ቃላት ገላጭነታቸው ሰው በእግዚአብሔር ምሳሌ በመፈጠሩ ክብሩ ከፍ ያለ መሆኑን፤ ይህም ከፍጥረታት ሁሉ ሰው ብቻ በእርሱ መልክ መፈጠሩን ያረጋግጣል፤ ይኸው ሰው ዓለምን ለማስተዳደር ሐላፊነት የመውሰድ አቅሙ ተገልጿል። እንዲሁም ሰውን ከፈጠረ

በኋላ «እጅግ መልካም» መሆኑን በማረጋገጥ ማብሰሩ ሰውን በእግዚአብሔር አምሳል የመፈጠሩን መሰረታዊ ምክንያት ያስጨብጡናል።

ይህን ይዞታውን ደግሞ ቅድመ ውድቀት እና ድህረ ውድቀት ብለን ልናየው እንችላለን። ይህንንም በማድረጋችን ተሻጋሪነት ያላቸውንና የሌላቸውን አስከትለን እንድናይ ያግዛል።

ሰው ሲፈጠር ትክክለኛ ዕውቀት፣ መልካም ፈቃድና ልከኛ ስሜት ያለው ነበር። ዕውቀቱ በስራ ላይ ተገልጧልና በማስተዋል ስያሜዎችን ለእንስሳት ሁሉ አወጣ፣ (ዘፍ. 2፡19-20) ስሜቱ ከዕውቀታቸውና ከፈቃዳቸው ጋር የሚስማማ ስለነበረ እራቁት ቢሆንም እንኳ አልተፋፈሩም (ዘፍ 2፡25) ሐዋሪያው ጳውሎስ በዚህ ወቅት የነበረውን ይዞታ ሲገልፅ «የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል ዕውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል» (ቆላ 3፡10) በማለት ያ ዕውቀት ሰፊ፣ የሚሰራ፣ ፅድቅና ቅድስና ያለበት እንደነበር ያረጋግጣል። ይልቁኑ «ለእውነትም በሚሆን ፅድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ (ኤፌ. 4፡24) በማለትም ትርጓሜውን ልከኛና ግልፅ አድርጎታል።

ዛሬ ያለነው እኛ ግን የድህረ ውድቀቱ ተካፋዮች ወይም ዘመነኞች ስለሆንን ከውድቀቱ በኋላ በሰው ላይ የተገለጠውን መሰረታዊ ጭብጥ አብረን እናጢን።

በዘፍ 2፡17 ላይ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ «እውን ሆነ» በተባለበት ቀን ሥጋዊ ሞት ባይሞቱም ሕይወታቸው ግን በሞት ጥላ ስር ዋለ፤ ከአለመታዘዛቸው በፊት (ከመብላታቸው በፊት) ኑሮአቸው ሁሉ መልካም ነበረ፣ ግልፅ አስደሳችና ሕያው ነበር፤ በማመፃቸው ግን ኑሮአቸው ሁሉ ተበላሸ እንግዳ ነገር ወደ ሕይወታቸው ገባ (ዘፍ 3፡7-24)።

በራሱ የሚያፍር ማንነት፣ የእግዚአብሔርን ድምፅ የሚሸሽ እና የሚደነግጥ ሆነ፤ (ዘፍ 2፡ 18-23) በዚህም መለያየት በሰዎች መካከል፤ መመከኛነት በሰው ሁሉ ላይ (ቁ.11-13)፣ መለያየት በሰውና በሌሎች ፍጡራን መካከል (3፡14-15) መጣ፤ ይህ ሀጢአት ወደ ሰው በመግባቱ የተገለጠ ነው።

ሀጢአት በትርጉሙ ወደ ታቀደ ዓላማ አለመድረስን ያመላክታል፤ ቀስተኛ ቀስቱን ይገትራል፤ ሆኖም በሆነ ምክንያት ዒላማው ወይም ፍላፃው ወደ ትክክለኛው ግቡ ሳይደርስ ከከሸፈ ሁሉ ነገር መከነ ማለት ነው። ልክ እንዳሁ ሰው ወደ ታሰበለትና ወደ ታቀደለት ደረጃ በማናቸውም ምክንያት ባይደርስ፤ ያለመድረሱ ምክንያት ኃጢአት ነው፤ ከዚህም የተነሳ ጳውሎስ ሰውን ሲገልፀው «ሁሉ ኃጢአትን ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል» አለ (ሮሜ 3፡23)።





ይህም በብዙ መልክ ተገልፃል፤ እግዚአብሔር ለሰው ሕይወት መስፈርትን ሰጥቷል፤ የሰው ኑሮ ግን ከዚህ መለኪያ ጋር አይስማማም። (ሐዋ 7፡24-27፣ ሮሜ 1፡18፣ ቆላ 3፡25)

ሀጢአት በበደልና በመተላለፍ መገለጡም ሰው እግዚአብሔር ከሰጠው መንገድ እየወጣ በሌላ በራሱ መንገድ መሄድን የሚመርጥ መሆኑን ያረጋግጣል። (ኢሳ 30፡21፣ 53፡6፣ ኤር 18፡12፣ ሮሜ.5፡15)

እንደ ቄስ ኮሊን ማንሰል «**ትምህርተ ክርስቶስ**» አገላለፅ (ገፅ 63) ኃጢአት «ከድክመት የተነሳ የሰው አንዳንድ ስህተትን መፈፀም ብቻ ሳይሆን፣ ትክክለኛውን ነገር ሁሉ አለማድረግ፣ የእግዚአብሔርንና የሰውን ክብርና መብት አለመጠበቅ፣ የእግዚአብሔርን ሕግ መካድና ከእግዚአብሔር ሕግ ውጭ እየተኖረ በፈጠረውና ሕግን በሰጠው ላይ መነሳሳትና ማመፅ ነው» ያሉበት ቃል የዚህ ዝግጅት ማብራሪያ ነው።

ሀጢአት ወደ ሰው ሁሉ ተላልፏል፤ ሀጢአት ፅኑ ብክለትን በሰው ላይ አምጥቷል። ስለ «ቅይማት» ምንነት ተነግሮ መግባባት ከሚቻልበት ሁነኛ መነሻ ውስጥ አንዱ «ይህም እንዲህ ነው» በማለት ጠያቂው ሰው ስለ ራሱ ያለውን ይዞታ ማወቅ ነው።

በኖህ ዘመን «እግዚአብሔር የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ የልቡ አሳብ ምኞቱም ሁልጊዜ ፈፅሞ ክፉ እንደሆነ» ማየቱን አረጋገጠ። ከጥፋት ውሃ በኋላም እንኳ «የሰው ልብ አሳብ ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉ» መሆኑን አረጋገጠ።(ዘፍ 8፡21)

በሙሴ ዘመን የሰው ልብ እልከኛነት የፈርኦን ልቡን በማደንደኑ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሕዝብ በእግዚአብሔር ላይ በማጉረምረሙ የመጣውን አፀና። (ዘፍ 14፡22) ኋላም ንጉስ ዳዊት «እነሆ በዐመፃ ተፀነስሁ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ» በማለት ከቤርሳቤህ ጋር የሰራውን፣ የተሸነፈበትን ኃጢአት እሱ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ የሰውን ገላጭ ማንነት በመመስከር ተናገረ። (መዝ 51፡ 5) ኋላም ነብዩ ኤርሚያስ «የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?» በማለት ራሱን ያካተተ መግለጫ አወጣ። (ኤር 17፡9) ጌታችንም የፅድቅ ሥራ በመሥራት ወደ መንግስተ ሰማይ እንገባለን ብለው እርግጠኞች የሆኑትን ሁሉ ዐመፀኞች መሆናቸውን በትምህርቱ አረጋገጠላቸው። (ማቴ. 7፡21-23፤12፡41-46፣ ሉቃ 13፡24-27) ሐዋሪያው ጳውሎስም «ፃድቅ የለም አንድ ስንኳ አስተዋይም የለም እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም ሁሉ ተሳስተዋል፤ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ጉሮሮአቸው እንደተከፈተ መቃብር ነው፤ በምላሳቸውም ሸንግለዋል የእባብ መርዝ ከከንፈሮቻቸው በታች አለ፤ አፋቸውም ርግማንና መራርነት ሞልቶበታል፤ እግሮቻቸው ደምን ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው። ጥፋትና ጉስቁልና በመንገዳቸው ይገኛል፤ የሰላምንም መንገድ

አያውቁም። በዐይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም» (ሮሜ 3፡11-18) በማለት ሰውን፣ ሀጢአትንና ፍሬውን ገለፀ።

በውጤቱም የመበከሉ ገፀ ብዙነትን በ«አእምሮ»ላይ ቅድሚያ በመስጠት መጀመር ተገቢ ነው፤ «አእምሮአቸው...ረክሷል» በማለት ጳውሎስ ለቲቶ (1፡15) የፃፈበት ዋንኛ ምክንያት ሰው እንደመሳፍንቱ ዘመን «በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ስለነበር» (መሳ 21፡25) ነው፤ ሰዎች ከገዛ ማንነታቸው ተነስተው «ይኸው ብቻ ነው ልክ» ብለው ያምናሉ፤ ያንንም የሕይወት መመሪያ ያደርጋሉ፤ መመሪው ግን ፍፁምነት ከጎደለው አእምሮ የወጣ ስለሆነ መተማመኛ አይሆንም፤ ይልቁኑ «የሰውን አሳብ በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ የሚነሳውን ከፍ ያለውን ነገር ማፍረስ» አስፈላጊ መሆኑን አዲስ ኪዳን ገልፃል (2ቆሮ 10፡5)።

ሰው እግዚአብሔር ካልረዳው በቀር ስለ እግዚአብሔር ሥራ እና ማንነቱ ምንም ማወቅ አይችልም። «ዕውር ነውና በቅርብ ያለውን ብቻ ያያል» የተባለበትም ምክንያት ይኸው ነው (2ጴጥ 1፡9) ከዚህም የተነሳ «ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም» በማለት ጌታ ሰውየውን ተናገረው (ዮሐ 3፡3፣10)።

የሰው አእምሮ መበከሉን ለማረጋገጥ ምርጫውን ልብ ማለት ተገቢ ነው፤ እሱ «መልካምን ነገር ከማሰብ ቶሎ ወደ ክፉ አሳብ ይሄዳል፤ እግዚአብሔር «ሕዝቤ ሰንፈዋልና ማስተዋልም የላቸውም ክፉ ነገርን ለማድረግ ብልሀተኞች ናቸው» በማለት ገስፃቸዋል (ኤር 4፡22)።

በአንድ ወቅት ዊንስተን ቸርችል ንግግር አድርገው እንደ ጨረሱ ወዳጃቸው «ንግግርህን አስር ሺህ ያህል ሰው ስለሰማልህ ደስ አላለህም» ይላቸዋል፤ እሳቸው ሳይገረሙ «ዛሬ ዊንስተን የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስቴር ይሰቀላል» ተብሎ ቢሆን ግን መቶ ሺህ ሰው ይመጣ ነበር» በማለት መለሱ፤ በዚህ ምልልስ ውስጥ የሚገኘው ቁም ነገር ሰው ከፋትን፣ ጥፋትን፣ መርዶን፣ ግድያንና እልቂትን በመስማት የሚደሰት መሆኑን ያረጋግጣል፤ ይህ «የዓለም ዜናዎች ተደማጭ ይሆኑ ዘንድ ከፈለግ ከአንድ መልካም ዜና በፊት 10 የመርዶ ዜና አስደማጭ መሆን አለብህ» የሚል መመሪያን የተከተለ ብቻ አትራፊ ሊሆን እንደሚችል ፅፈዋል፤ ነግረዋል፤

የሀጢአተ ብክለት እሉታዊ ተፅዕኖውን በኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት ላይም መገለፁንም ሲያስረግጥ «...እናንተ ደግሞ እስከአሁን የማታስተውሉ ናችሁን?» የሚል ጥያቄ ነበር ያነሳው በኋላም በትንሳኤው ማግስት ላይ ተገኝቶ ያደረገው ያስተውሉ ዘንድ «አእምሮአቸውን መከፈት» ነበር (ማቴ 15፡16፣ ሉቃ 24፡27)





ሐዋሪያው ጳውሎስ አማኞች ሙሉ መረዳት እንዲያገኙ ደጋግሞ ፀልዮላቸዋል፤ (ኤፌ 18 ቆላ 1፡9) ይህ ያስፈለገው እርዳታ ከእግዚአብሔር ካልመጣ በቀር የሰው አእምሮ የተበከለ ስለሆነና ለእርሱ ልክ የመሰለው ልክ ላይሆን ስለሚችል ነው።

ሀጢአት የሰውንም ፈቃድ አዛብቷል፤ ብዙ ሰዎች «እኔ ልክ ነኝ» ይላሉ፤ አንዳንዶች «አልፎ አልፎ ነው የምሳሳተው» ብለው ይናገራሉ፤ የተቀሩት ደግሞ «መልካም እንዳደረጉ ብዘልቅ ምንኛ ደስ ባለኝ» ብለው ምኞታቸውን ይገልፃሉ።

የእግዚአብሔር ቃል ግን ሰው መልካም ነገርን ማድረግ አለመቻሉን ያረጋግጣል፤ ምንም በጎ ነገር እና በጎ ፈቃድ ያለ እግዚአብሔር እገዛ አለመምጣቱን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» በማለቱና «የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም» በማለቱ ልኩንና እውነቱን አስቀምጧል (ዮሐ 15፡5 ዮሀ 6፡44)

ይህም ሰው መልካም ነገርን ማድረግ አይወድም፤ ይህንንም ምርጫው የሚያደርገው ክፋትን ለመተው ስለማይፈልግ ነው፤ ቄስ ማንስል በመሳፍንት ዘመን እስራኤል ጣዖታቸውን ከመካከላቸው ያስወገዱት መልካም ለመሆን ፈልገው አይደለም ይልቅስ ከእግዚአብሔር የሚመጣባቸውን ቅጣት ችለው መቀበል ባለመቻላቸው ነው (ማንስል ገፅ 69፣ መሳ. 10፡10-16)

የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለ እምነታቸው ብዙ መልካም ነገርን መናገር ይችላሉ። ነገር ግን አያደርጉትም። በልባቸውም ስስታቸውን ይከተላሉ። (ሕዝ33፡31) በዚህ አጋጣሚ ልጆች የታዘዙትን እያወቁ ተቃራኒውን ሲያደርጉ ይታያሉ፤ ይህም መልካም ነገርን ያለማድረግ ዝንባሌ እንዳላቸው ያመለክታል «ስንፍና በህፃን ልብ ታስሯል» ተብሎ የለ (ምሳ 22፡15)።

ሀጢአት ትልቅ ነው፤ ሀይለኛም ነው፤ ከዚህም የተነሳ ሰው እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ ይቃወማል፤ ሰዎች ክርስቶስን ይጠላሉ፤ ግና ለመጥላታቸው ምንም በቂ ምክንያት የላቸውም፤ ተቃዋሚነት ባህሪያቸው ስለሆነ እርሱን ተቃወሙት፤ ጠሉት፤ ሰቀሉት፤ «ወራሹ ይህ ነው ኑ እንግደለው ርስቱን እናግኝ» ተባባሉበት። ማቴ. 21፡38

ክርስቶስ ነብይ፣ ካህንና ንጉስ ሊሆን መጣ፤ ነገር ግን በሦስቱም ማንነቱ አልተቀበሉትም። እስጢፋኖስ «እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሮአችሁ ያልተገረዘ እናንተ ሁል ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወሙታላችሁ፤ አባቶቻችሁ እንደተቃወሙት እናንተ ደግሞ...» (ሐዋ 7፡51) በማለት የሰጠው ምስክርነት እውነት ነበር፤ ነውም።

ሀጢአት የሰውን ስሜትና ኅሊናም ማጉደፉን መዘንጋት የለብንም፤ የ«ቅይማት»ን

ልከኛውን ድንበር ለመረዳት ይህም ዋንኛው ነው። ከሰው ልብ «ክፉ ሀሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርና፣ መጎምጀት...ይወጣሉ» (ማር 7፡21-23) እኒህ የወጡት ሰው እነዚህን በማድረግ ስለሚረካ ነው «እነርሱም በጨለማ መንገድ ይሄዱ ዘንድ የቀናውን ጎዳና የሚተዉ፣ ክፉ በመስራት ደስ የሚላቸው፣ በጠማማነትም ደስታን የሚያደርጉ መንገዳቸውን የሚጠመዝዝ፣ አካሄዳቸውንም የሚያጣምሙ ናቸው» ተብሏል። ምሳ. 2፡13-15

በተያያዥም መልካሙንና ክፉውን መለየት እንዲችል እግዚአብሔር የሰጠውን ሕሊና ሰው በአግባቡ የመጠቀም ብቃት የለውም ኢሳይያስ «ክፉውን መልካም መልካሙን ክፉ» ይላሉ ብሎላቸዋል (ኢሳ 5፡20) ጳውሎስም «ንፁህ የሆነ ምንም የለም፤ ነገር ግን አእምሮአቸውም ኅሊናቸውም ረክሷል፤ (ቲቶ1፡15፣ 1ጢሞ 4፡2) ከዚህም የተነሳ አማኝ ከመሆን በፊትም ሆነ በኋላ ይህ ገፅታ በሰው ላይ ይታያል።

ይልቁኑ የሰውን የማስታወስ ችሎታ እና የሰው ሁለንተና ስለመዛነፉ ጥቂት ብለን ሰው ተኮር ጭብጦችን እንገታለን። የዕብራውያን ፀሐፊ «ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ...» (ዕብ 2፡1) በማለት ማስጠንቀቁን፡-መርሳት እና መዘንጋት የወደቀው ሰው መለያ መሆኑን ማወቅ ያስችላል።

በመሰረቱ የሁለንተና መበከል ሊመስል የሚችለው «በበርሜል ተቀድቶ በተቀመጠ ንፁህ ውሃ ውስጥ አንድ ጠብታ መርዝ ቢገባበት ውሃውን በሙሉ በክሎ መርዛም እንደሚያደርገው የሰውም በሐጢያት መበከል እንዲሁ ነው።

**ከላይ የተፈነጠቁት** ነጥቦች ሰው ይልቁኑ በክርስቶስ የሆነ አማኝ በየትኛውም ጉዳይ ላይ ራሱን ሲመዝንም ሆነ ስለሌሎች ለመናገርና ለመወሰን ሲሞክር አስቀድሞ ማድረግ ያለበት ራሱን ወይም የሰው ልጆች ሁሉ ሊኖራቸው ያላቸውን ብቃትና የተገደበ ማንነታቸውን በበቂ መረዳት ነው።

ከዚህ ግንዛቤ ጋር የማይዘነጋው እውነት፡- በክርስቶስ ተጠርተው ዳግም የተወለዱ ሰዎች እንዲሁም ያለ ክርስቶስ የሚኖሩ የሰው ልጆች ከመነሻው፡- የመፈጠራቸው መለያ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ነው። ይህ ደግሞ በሀጢአት ምክንያት ከነበረው አቅም እና ከታሰበለት ሙሉአት አውርዷቸዋል። ይህም ቢሆን የእግዚአብሔር የሆኑ ምንነቶች ግን መቶ በመቶ ይወገዱበት ዘንድ እግዚአብሔር አላደረገም፤ ሙልዐት የጎደለው ቢሆንም የምሳሌነት መገለጫውን፣ በኑሮ ሁሉ ውስጥ ያሳያል።

ይህ ዝግጅት ሰው እግዚአብሔርን ቢቀየመው እንዴት ወደ ተሻለ ማጠቃለያ ይሄዳል?





ለሚለው ከልቡ ራሱን በማየት ራሱን ይመዝን ዘንድ እንደሁኔታውም ከፈተና እና ከወጥመድ ለማትረፍ ታስቦ የቀረበ ነው።

## ከ. በሰው ቅይማትን የተረፈው እግዚአብሔርስ ማንነው?

አማኞች ካልተቸገሩ በቀር ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት መንከራተት የለባቸውም፤ ቅዱሳት መፅሐፍት አሏቸውና፤-እነርሱን በማስቀደም እምነታቸውንና ምግባራቸውን መፈተሽ አለባቸው፤ ጥናታችን ሰውን ያማከለ ቢሆንም በግራ ቀኝ እየተነሳ ጉዳዩ የሚያያዘው ከእግዚአብሔር ጋር ነው።

**ይህ እግዚአብሔር፡-** ከእግዚአብሔር ቃል እይታ ውጭ ይመዘን ወይም ይተመን ከተባለ መሰረታዊ ጥፋት በአማኞች ላይ ሊመጣ ይችላል፤ ያ ችግር ደግሞ እንደሁኔታው ራስን ከመጉዳት ጀምሮ መላውን ማህበር ሊያጠቃ ይችላል፤ ጥቃቱ አካላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ስሜታዊ፣ በመሆን ሰውን ከአዘቅት ያወርደዋል።

አንድ ሰባኪና ፀሐፊ ትውልዱእግዚአብሔርን እንዴት እንደተረዳው ሰብከዋል፤ ፅፈዋል። የተናገሩት «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳልና መልክ ፈጠረው ከዚህም የተነሳ ለሰው መነሻውም መደምደሚያውም እግዚአብሔር ብቻ ነበር፤ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ያሉ አማኞች ግን እግዚአብሔርን በገዛ አምሳላቸውና መልካቸው ፈጠሩት» በማለት አስተምረዋል። ይህን ሲሉ የጌታ ነን የሚሉት በእነርሱ አቅም የተተመነ፣ የእነርሱን ፍላጎት የሚያሟላ፣ እነርሱን ብቻ የሆነ «እግዚአብሔር» አላቸው ማለትነው። እንዲህ ሲሆን እግዚአብሔርን ማወቅ አስቸጋሪ ነው።

ይልቅስ በቃሉ የተገለፀውን እግዚአብሔርን አቅም በፈቀደ እናመላከት።

ለዝግጅቱ የአስራት ገብረማሪያም «**ትምህርተ መለኮት**» ምቹ መነሻ ይሆናል፤ ከዚህም የተነሳ በዋንኛ ነጥቦች ላይ የኝህን ኢትዮጵያዊ ላቅ ያለ ስራ አመላከታለሁ።

በቀዳሚነት ከመነሻው የእርሱን መልክ መግለፅ የሰው ልጅ አይችልም፤ ለዚህም ምክንያቱ እሱ ከማንኛውም ኹናቴ የተለየና የላቀ በመሆኑ ነው። እሱ ከአስተሳሰባችንና ከችሎታችን በላይ ነው፤ ለእግዚአብሔር ምሳሌነቱ ብቁ የሚኾን ምንም ነገር የለም፤ እሱ በመለኮታዊ ክብሩ ለዘላለም በራሱ የሚኖር ነው። ሁሉን ነገር የሚሰጥ እርሱ እንደ መሆኑ ከማንም ምንም አይፈልግም፤ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘላለማዊ ከመሆኑ ባሻገር እርሱ በሁሉም ቦታ ይገኛል፤ (አስራት ገፅ 17) ይላሉ።

ይህን መግለጫ በቃሉ በማስደገፍ ማጥናታችን ተገቢ ነው፤ እግዚአብሔርን በሕዋሳቶቻችን አማካኝነት እናውቀውም፤ የማናውቅበት ምክንያት እርሱ መንፈስ ስለሆነ ነው፤

የአንድ ነገር አንድ ክፍል ወይም ኹሉም አይደለም፤ እርሱን መለኪያ፣ የክብደት መመዘኛ፣ የቁመት ግዝፈት አይገልፀውም። ኢሳይያስ «እግዚአብሔርን ከማን ጋር ታነፃፅሩታላችሁ? ከማንስ ጋር ታመሳስሉታላችሁ» በማለት እርግጡን አውጆልናል (ኢሳ 40፡18) እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ በእውነት የሚሰግዱለትም በመንፈስ ሊሰግዱለት ይገባቸዋልም ሌላው ሰነድ ነው፤ (ዮሐ4፡24)

የእግዚአብሔር ሌላው መገለጫ ሁሉን ቻይነቱ ነው፤ እሱ የፈለገውን ነገር ያደርጋል እንጂ የማንንም እርዳታ ወይም ምክር አይጠይቅም፤ አለመጠየቁ ኃያልነቱ ከመጠን በላይና ታላቅነቱም ከሁሉም በላይ በመሆኑ ነው፤ እሱ በሚሰራበት ጊዜ ሀሳብ ያቀረበለት ወይም ይህንስ አየኸው ወይ? በማለት ያቀደውን ሊያስለውጠው የሚችል አልነበረም ኢሳይያስ «እነሆ አሕዛብ በገንቦ እንዳሉ ጠብታ ናቸው፤ በሚዛንም እንዳለ ትንሽ ትቢያ ተቆጥረዋል፤ አህዛብ ሁሉ በፊቱ እንዳልነበሩ ናቸው፤ ከምናምን እንደሚያንሱ እንደከንቱ ነገርም ይቆጥራቸዋል» ኢሳ 40፡15-16

የመቻሉ መገለጫ ብዙ ነው፤ እስራኤላውያንን ከግብፅ ሲያወጣ ባህሩን ግራና ቀኝ ከፍሎ አሻግሮ ሲያበቃ በዚያው ባህር የግብፅ ሰራዊትን በዚያው ውሃ ከድኗቸዋል።(ዘፀ 14፡21-28)።

ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎን ከነደደው የናቡከደናፆር እሳት ምንም ሳይሆኑ ሲያወጣቸው፣ የኮነኗቸው ግን ገና ከመቅረባቸው አረው ሙተዋል፤ (ዳን 3፡19-27) እንግዲህ ሉቃስ ባለው መፅናት ተገቢ ነው «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና» (ሉቃ 1፡37)።

ሰው የሚቀየመው እግዚአብሔር የማይለዋወጥ መሆኑን ማመን ወይም መገንዘብ አለበት፤ አንዳንድ ሰዎች አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በማንሳት እግዚአብሔር ሀሳቡን በፆም ብዛት፣ በፀሎት ዋይታ ሊቀይር እንደሚችል በማመን ይዋዥቃሉ፤ የንጉስ ሕዝቅያስ የአስራ አምስት ዓመት ዕድሜ መጨመር፣ በዮናስ መልዕክት ላይ «እግዚአብሔር አጠፋለሁ» ብሎ ንስሀ በመግባታቸው ሀሳቡን የቀየረ መምሰሉን በማንሳት ይጨነቃሉ።

እውነቱ ግን የሕዝቅያስ ልመናም ሆነ የዮናስም ሕዝብ ውሳኔ እግዚአብሔር ባቀደው ግብ ላይ ተጣጣሙለት እንጂ እርሱ ዋዣቂ እና ሀሳብ ቀያያሪ አይደለም ይልቅስ «ሀሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፤ ይፀፀትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም» (ዘኁ23፡19)ን፣ «እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም» (ሚል. 3፡6) «እግዚአብሔር ከመረጠና ፀጋውን ከሰጠ በኋላ ባረገው ነገር አይፀፀትም» (ሮሜ 11፡29)ን የመሰሉቋሚ መመሪያዎችን ከልብ ማመንና መጠቀም የግድ ነው።

ስለ **ቅይማት** ለመነጋገር ሌላው መገለጫ የእግዚአብሔር ሁሉን አከናዋኝነቱ ነው፤ በእርሱ ፈቃድ፣ በእርሱ ትዕዛዝ ካልሆነ በቀር ምንም ነገር አይደረግም፤ በየትም የሚሆኑ ድርጊቶችና





እንቅስቃሴዎች ሁሉ የእርሱ ዕውቅናና ውሳኔ አለባቸው «የእናንተ የራስ ፀጉራችሁ እንኳ የተቆጠረ ነው» በማለት ሲናገር በእርግጥም ሁሉን በቁጥር ያውቀዋልና ነው (ማቴ 10፡30)

እንደ አስራት ገብረማሪያም አገላለፅ፡- እግዚአብሔር የማያምኑ ነገስታትንና ልዑላንን ሁሉ በስልጣኑ ያስተዳድራል በእርሱ አማካኝነት ሁሉ ይሆናል። በእርሱ ዕውቅናም ከፉው ይፈፀማል፤ ወደ ኢዮብ ለሚሄደው ሴጣን የእግዚአብሔር እውቅና እንደተከተለው መዘንጋት የለብንም (ኢዮ 1፡ 12)።

ይህም ከእርሱ ዐዋቂነት ጋር ተሳሰሯል፤ ለዚህ ደግሞ መንደርደሪያው እርሱ በሁሉም ቦታ የሚገኝ መሆኑ ነው፤ ሐዋሪያው ጳውሎስ ሲገልፀው «እግዚአብሔር በጥበብና በዕውቀት ምንኛ ባለፀጋ ነው ፍርዱና መንገዱስ ተመርምሮ ለመታወቅ የማይችል ምንኛ ጥልቀት አለው።» (ሮሜ 33፡33) በማለት ገልጿል። እግዚአብሔር አዋቂነቱን ተምሮ ያገኘው አይደለም፤ ማወቁ የራሱ ነው፤ ከዚህም የተነሳ የትኞቹንም ክንውኖች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይፈፅማሉ እንጂ የሚታረሙ ወይም የሚሻሻሉ አይደሉም፤ ያለፈውም ሆነ የወደፊቱ የሚሆነው ድርጊት እንዳለ ኹነት እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለፈ ሆኖ የሚረሳ ወይም ወደፊት የሚሆን ሆኖ የሚናፈቅ ምንም ነገር የለውም «...እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዐይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለፀ እንጂ ከእርሱ ፊት የተሰወረ ምንም ፍጥረት የለም (ዕብ 4፡13) ዳዊት እንዲህ አለ፤-«እግዚአብሔር አያይም፤ የያዕቆብ አምላክ አይመለከትም፤ አሉ እናንተ የማይገባችሁ ሞኞች ይህንን አስተውሉና ይግባችሁ ጆሮን የተከለው አይሰማምን? ዐይንን የሰራው አያይምን? (መዝ 94፡7-10) በማለት ሕዝቡን ይሞግታቸዋል።

እግዚአብሔር በዋናነት የማንም እርዳታ የማያስፈልገው መሆኑን ልብ ማለትም ተገቢ ነው፤ እሱ የማንንም ድጋፍ አይፈልግም ግን በትይዩ ያለ እርሱ ጠባቂነት አንድም ፍጡር ለመኖር ወይም ለመንቀሳቀስ አይችልም፤ (ሕያዋኑም ግዑዟኑም) በሁሉ ቻይነቱና በጥበቡ አማካኝነት ፍጥረትን ሁሉ የሚቆጣጠረው እርሱ ነው፤ ሐዋሪያው ጳውሎስ *«እርሱ ዓለምንና በዓለም ያለውን ሁሉ የፈጠረ ነው የሰማይና የምድርም ጌታ ነው፤ እርሱ በሰው እጅ በተሰራ ቤተመቅደስ አይኖርም ሕይወትንና እስትንፋስን ሌሎችንም ነገሮች ለሰው ሁሉ የሚሰጥ እርሱ ስለሆነ ምንም ነገር አይጎድለውም፤ የሰውም እርዳታ አያስፈልገውም»* (ሐዋ 17፡24-25) በማለት እግዚአብሔር ማነው? እንዴትስ ልንረዳው እንችላለን? የሚለውን ጭብጥ በአግባቡ መገንዘብ፣ በዚህም መታመን ተገቢ ነው። ሁል ጊዜም እግዚአብሔር በሁሉ ላይ ተቆጣጣሪ፣ አስተዳዳሪ፣ በገዛ ፈቃዱ መሰረት ሰሪ መሆኑን ከተያያዦቹ ጥቅሶች ጋር ማጥናት ይጠቅማል።

- ❖ በዓለማት ሁሉ ላይ፣ መዝ 103፡19፣ ዳን 4፡34፣ ኤፌ 1፡11

- በቁሳዊ ዓለም ላይ ኢዮብ 37:5፣ መዝ 104:14፣ 135:6፣ ማቴ 5:44
- በእንስሳት ላይ፣ መዝ 104:11 ማቴ 6:26,10:29
- በሕዝቦች ጉዳይ ላይ፣ ኢዮብ 12:23፣ መዝ 22:28፣ ሐዋ 17:26-27
- በሰው ልደትና ዕድል ፈንታ ላይ፣ 1ሳሙ 16:1፣ መዝ 139:16፣ ኢሳ 45:1-6
- በሰው ሕይወት፣ ስኬትና ውድቀት ላይ፣ መዝ 75:6-7፣ ሉቃ 1:52
- በድንገተኛ እና በአነስተኛ ነገሮች ላይ፣ ምሳ 16:33፣ ማቴ 10:30
- መልካም ሰዎችን በመጠበቅ ላይ፣ መዝ 4:8,5:12 ሮሜ 8:28
- ለሕዝቡ አስፈላጊውን በመስጠት ላይ፣ ዘፍ 22:8 ዘዳ 8:3 ፊሊ 4:19
- ፀሎትን በመመለስ ላይ፣ 1ሳሙ 1:19-20፣ 2ዜና 33:13፣ መዝ 65:2፣ ማቴ 7:7
- ኃጥአንን በመቅጣት ላይ፣ መዝ 7:12፤ 11:6 (**ትምህርተ እግዚአብሔር** ማንሰል ገፅ 306) ወዘተ ሁሉ ላይልዑል የሆነው እግዚአብሐር ብቻ ይሰራቸዋል፤ እየሰራቸውም ነው። እንግዲህ እግዚአብሔር ሁሉን ለክብሩ በመፍጠር ዓላማውን ይፈፅም ዘንድ ሁሉን ይቆጣጠራል፤ እሱ እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር እንደ ሀሳቡ ሁሉን ወሰነ። (ኤፌ 1:11) ሁሉ ከእርሱ፣ በእርሱ እና ለእርሱም ነው። (ሮሜ11:36) ይህም ለክብሩ ነው።(ራዕ 4:10)

በቀደሙት በሁለቱ ክፍሎች ሰውን በአግባቡ ለመርዳት ችለናል፤ እንዲሁም በቀጣይነት እግዚአብሔር ራሱን በቃሉ በገለፀበት ማንነቱን ልብ ብለናል፤ ይህን ከግምት አለማስገባት ወደ የትኛውም ርዕስ ጉዳይ አያስገባንም፤ እንግዲህ መፅሐፍትን ተንተርሰን ሰዎች እግዚአብሔርን ሊቀየሙ የሚችሉበት ሁኔታ ካለ ያንን በቀጣዮቹ ገለፃዎች ላይ እንናበባለን።

## ሐ. እግዚአብሔርን ከመቀየም የቻሉ ወይም የመቻል ዝንባሌ ያላቸው «ቅዱሳን» ነበሩ ወይ?

ንዑስ ርዕሱ «ቅዱሳን» በማለት ከልል ወስኖለታል፤ ያለ ክርስቶስ ያልሆኑትን አልጠቀሰም፤ አልፈለገም፤ ለእነርሱ በፍጥረተ ዓለም ውስጥ የሚካሄደውን ሁሉ ያለ እግዚአብሔር ስለሚተረጉሙትና እና በእግዚአብሔርም ስለማያምኑ በሆነው ነገር ሁሉ ላይ «እከሌን ብለው አያሳቅሉም፤ የመጣውን ይቀበላሉ፤ የሔደውንም ይሸኛሉ።





«ቅዱሳን» ተብለው የተጠሩ ግን በእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥሪ በዘመናት ውስጥ ተጠርተው ከእግዚአብሔር ጋር የነበሩትን ይመለከታል፤ ይህም በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ አዲስ ያሉትን ወገኖች ያካትታል።

ዮሴፍ አባቱን የሚታዘዝ ቅን ልጅ ነበር፤ ስለ ወንድሞቹ ለማወቅ ተላከ:- በምላሹ ግን ወንድሞቹ አጉላሉት ሸጡት፤ በግብፅ የገጠሙትን መከራዎች ተቋቁሞ በዋንኛው ቤት ተገኘ ግና በአስተዳዳሪው ሚስት ተፈተነ:- የፈተናውን መለኪያ ማነፃፀሪያ እግዚአብሔርን አድርጎ እምቢተኛ ሆነ፤ በውሳኔው ውሸት ተፈበረከበት፤ እስር ቤትም (ዘብጥያ) ወረደ:- በዚያም ሊወጣ የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሮ ሳለ ግን ነፃ የወጣው ሰው እረሳው:- እነዚህ ተከታታይ ገጠመኞች በጎ ባደረገ ቁጥር ተቃራኒ ውጤት ለገጠመው ሰው ምላሹ:- በማጉረምረም - በመቃወም - በማመፅ በእግዚአብሔር ላይ በ«መቀየም» ሊገለፅ ይገባው ይሆናል ግና በምትኩ ፀሐፊው «እግዚአብሔር ግን ከእርሱ ጋር ነበረ» የሚልን ተደጋጋሚ መግለጫን ይሰጣል።

ይህን ምስክርነት ዮሴፍ ልብ ይበለው አይበለው የሚታወቅ ነገር የለም። የእግዚአብሔር ምስክርነት ግን እርሱ ከዮሴፍ ጋር መኖሩን ማረጋገጥ ነበር።

እርግጥ ነው ወንድሞቹ በእርሱ ፊት በቀረቡ እና ስለራሳቸው ማንነት ከተረዱ በኋላ መሳቀቃቸውን ተመልክቶ እሱ የኋላ ዘመኑን በሙሉ በመገምገም «እግዚአብሔር ሁሉን ለመልካም በማድረጉ አትጨነቁ» ነበር ያላቸው።

በመሰረቱ ዮሴፍ በገጠሙት ጉዳዮች አጉረምራሚ - ተቀያሚ እንዳይሆን የሚከለከለው አልነበረም።

ኤርምያስ ሌላው የእግዚአብሔር ተጠሪ ነው። እሱ የእግዚአብሔርን መልዕክት ተቀብሎ ወደ ሕዝቡ ያደርስ ነበር። እሱ ከማንም ይልቅ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ሀሳብ የሚረዳ ነብይ ነው።

እሱ ግን እንደማንኛውም ሰው ስለነበረ በእግዚአብሔር ላይ ተፃራሪ ሆኖ የተነሳበት ወቅት ነበር፤ ይህም በኤርምያስ አስራ ሁለት ላይ በከፊል ተገልፃል።

የፍትህ መጓደል፤ ከፉዎች በግፍ ተደላድለው መኖር እና መባረክ ግራ አጋባው፤ እሱ ሁሉን ነገር እግዚአብሔር እንደሚያውቀውና እንደሚፈፅመው ያስተውል ነበር እና «እንዴት?» የሚል መልስ አልባ ጥያቄ ተፈጠረበት እናም ይህን ክርክር አነሳ:-

«...የከፉዎች መንገድ ለምን ይሰምራል?

የከዳተኞችስ ኑሮ ለምን ይሳካል?

አንተ ተክለሀቸዋል ሥርም ሰደዋል

አድገዋል ፍሬም አፍርተዋል።

ሁል ጊዜ አንተ በአፋቸው ላይ አለህ

ከልባቸው ግን ሩቅ ነህ...» (ኤር.12፡1-3) አለው።

ኤርምያስ፡-በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን ሀገራዊ ጉዳዮን ሁሉ በአግባቡ ተመልክቷል፤ አጢኗል፤ ግና በተደጋጋሚ እያየ ያረጋገጠው፡- «እግዚአብሔር ተስፋችን ነው» ብለው የሚተዳደሩ ቅዱሳን እየተጎሳቀሉ፤ የተቀሩት ያለ እግዚአብሔር ያሉትና በእግዚአብሔር ታምነናል ብለው ግን የጥፋት ሕይወትን የመረጡ ሲባረኩ እና ስኬታማ ሲሆኑ ማየት አሳዘነው።

ኤርምያስ በአጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ ቢጨናነቅም ዞሮ ዞሮ «አንተው ራስህ ትክክለኛ ሆነህ መገኘትህ» አይቀሬ ነው ብሎ አረጋገጠ በዚህም ተረጋጋ።

በወንጌላት ውስጥም ከምናገኛቸው የማስተማሪያ ምሳሌዎች ውስጥ አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሀሳቡን ከግብ ለማድረስ የገለፀው ምሳሌ ነው፤-ኢየሱስ አሰሪውን ባለሀብት አመጣ፤ እሱ እቅዱ እንዲፈፀም ሰራተኞች አስፈለጉት፣ ከዚህም የተነሳ እከፍላለሁ እያለ ሰዎችን ቀጠረ የቀጠረው በ3፣ በ6፣ በ9፣ እና በ11 ሰዓት ላይ ነበር። ከዚህም የተነሳ ለዘጠኝ ተከታታይ ሰዓት ድንጋይ ሲሸከሙ የነበሩ ነበሩ፣ ለስድስት ሰዓታት እንጨት ሲፈልጡ የነበሩ አሉ። ለሶስት ሰዓት ቀለም የቀቡ ነበሩ፤ ለአንድ ሰዓት ብቻ ወዲያወዲህ ያሉ ነበሩ። አሰሪው አስራሁለት ሰዓት ላይ ሁሉን አሰልፎ ከኋላ ወደ ፊት መክፈል ጀመረ አንድ ሰዓት ብቻ ለሰሩት አንድ ብር ከተከፈለ ከዚያ ቀድመው የመጡና በተለይም ከጠዋቱ ጀምረው የደከሙ በርካታ ብር ሊያገኙ እንደሚችሉ አመኑ ግና ከፋያው ለሁሉም ያው አንድ ብር ብቻ ነበር።

ከዚህም የተነሳ አሰሪው (ባለሀብቱ) ተቃዋሚ ገጠመው፤ «ፍትህ የለም» የሚሉ ተነሱበት እሱ ግን የሰጠው ምላሽ «በገንዘቤ ምን አገባችሁየተዋዋልኩትን እስከሰጠው ድረስ»የሚል ሆነ።

እንግዲህ ይህ ንባብ «ቅይማት»ን አንስቶ በሪቻርድ ላይ ከማነጣጠሩ በፊት ኢዮብን ቅድሚያ ሰጥቶ ያስነብባል።

## መ. አጠራር በኢዮብ ላይ





*የኢዮብን ታሪክ ያጠኑ እና ብዙ በኢዮብ ሕይወት ላይ የሰበኩ፣ የመከሩ፣ የፃፉ ሰዎች፡- በብዙ መከራ ውስጥ ያለፉትን በዚያም ፀንተው ያሉትን «ትዕግስት እንደ ኢዮብ» ሲባሉ በመከራ ውስጥ መኖራቸውን እያወቁ ተጨማሪ መከራን በምክር ስም የሚያቀርቡትን ደግሞ «የኢዮብ አፅናኞች» በማለት መጥራት ከተጀመረ ከራረመ። የኢዮብ ትምህርት ዘመኑን ወደ ኋላ በመውሰድ ከአብርሀም ተጠግቶ በሙሴ ዘመን የተካተተ እውቀትን መያዙ ቢያስገርምም ግና ዋንኛው ገለጣ የመከራው ታሪክ ነው፤ ይህን የግለ ሕይወት ገለፃን ብዙዎች እውነት ነው ይላሉ፤ ብዙዎች fact ትን ከ Fiction የቀላቀለ «Faction»(እውነትና ልቦለድ) በማለት ይጠሩታል።*

እንዲህ ያስባላቸው በኢዮብ የመጣውን ተከታታይ መከራ ለመቀበል ባመፈለግ ወይም ባለማመን ያሉበት ነው።

ሚዛናዊ መሆን እንድንችል፤ በዚህ ጉዳይ ላይ የመነጋገሪያ ጥናት ያቀረቡትን David Pawson ንን Unlocking the Bible ገፅ 416 በመነሻነት ላመላከት፡-

ኢዮብ የነበረ ሕያው ሰው ነው፤ ለዚህም ሕዝቅኤል፣ ኖህን እና ዳንኤልን በዝርዝሩ ባነሳበት ኢዮብም መዘከሩ እንዲሁም በአዲስ ኪዳን በተለይም በያዕቆብ መልዕክት መከራን በመቻል መጠቀሱ፣ ለእውነተኝነቱ እውነተኛ መረጃ ነው።

ኢዮብ በገጠመው ጥፋት ምላሹ እውነት ነበር፤ ገጠመኙ ሁሉ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፤ ከዚህም የተነሳ እውነት ነው።

ኢዮብ በገለፃው ከእውነት ጋር አልተያያዘም ብለው የሞገቱ ያነሱት፡- *በምዕራፍ አንድ ላይ አራት ጥፋቶች መጡ ያንንም መርዶ ለማምጣት አንድ ሰው ብቻ መቅረቱን እያሳወቀ ይናገራል። ታሪኩ ሲጠናቀቅ በድጋሚ ያገኛቸው የልጆች ቁጥር ሰባት ወንዶችና ሶስት ሴት ልጆች ነበሩ በዚህ ደግሞ ኢዮብ በመነሻ ቢያጣም በመጨረሻ ያንኑ በማግኘቱ ቀድሞ የነበረውን የረሳ ያህል አድርጎታል፤ ከዚህ ሌላ በመፅሐፉ ውስጥ ያሉት መካሪዎች ሁሉ አነጋገራቸው ቅኔያዊ ሆነው ነው የቀረቡት ይህ ደግሞ መሆን መቻሉ አጠራጣሪ ነው በማለት ግራ ይጋባሉ።*

በዚህ ዝግጅት ግን ኢዮብን በዋናነት የምናነሳው ለቅይማት የሚያበቁ ተከታታይ መከራዎች በእርሱ ላይ መምጣታቸው ነው። አሳሳቢው፡- ኢዮብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈፀም ዕለት ዕለት ራሱን የፈተሸ ሰው መሆኑ ነው። ሌላው ቢቀር ልጆቹ በድለው ሊሆን ቢችል በማለትም ስለ እነርሱ መስዋዕት አቅራቢ ነው።

**የተደካደከኑሮ፣ የተከበረ ሰው፡-** ተሰሚነቱ በሁሉ ዘንድ የገነነለት የስኬት ባለቤት

ነበር። ይህ ግን ከምዕራፍ 1 ቁጥር 13 በኋላ ባለው ጥፋት ነገሮች በነበሩበት ሳይሄዱ እንዲቆሙ አድርጓል።

> ቁጥር 15 *በሬዎቼንና አህያዎቼን በሙሉ በሰባውያን ጥቃት ተወሰዱ... ይህን ለመንገር የተረፈ አንድ ሰው መጣ፣*
>
> ቁጥር 16 *የእግዚአብሔር እሳት ወርዳ በጎችንና አገልጋዮቼን በላች እኔም ብቻዬን አመለጥሁ የሚል አንድ ሰው መጣ፣*
>
> ቁጥር 17 *ከለዳውያን ግመሎችህን ወሰዱ፣ አገልጋዮቹን ገደሉ እኔም ብቻዬን አመለጥሁ የሚል ሌላ አንድ ሰው መጣ፣*
>
> ቁጥር 18 *ወንዶቹንና ሴቶች ልጆቹን ሁሉ ታላቅ አውሎንፋስ ወደቀባቸው ሞቱ ይህንንም አንድ የተረፈ ሰው መጥቶ ነገረው፣*

በዚህ ጊዜ ኢዮብ ልብሱን ቀደደ፤ ራሱን ተላጨ፤ በምድርም ተደፍቶ ሰገደ፣ ይህ ከሆነ በኋላ ግን ተጨማሪ ፈተናዎች በራሱ ላይ መጣ፡- ቆሰለ በሰበሰ፤ ወገኖቹ መካሪ ሆነው አጎሳቆሉት፣ ሚስቱ ሕያው እግዚአብሔርን ይከድ ዘንድ አሳሰበችው ከዚህም የተነሳ ኢዮብ በገጠመው መከራ ዘርፈ ብዙ ጥቃት ገጠመው።

- **<u>አካላዊ</u>** በሆነ ገፅታው፡- ከራስ ፀጉር እስከ እግሩ ጥፍሩ ድረስ በሰበሰ ስጋው በላዩ ላይ ፈረሰ፣ ተወገደ፤ ሸተተም፤ በዚህም አካሉን በማጣት ማንነቱን ለመለየት የሚያስቸግር ሰው ሆነ። እንደዛሬ ቢሆን መለየት የሚቻለው በDNAምርመራ ይሆን ነበር።
- **<u>ማህበራዊ</u>** በሆነ ገፅታው በገጠመው በቆዳ መቀየርና መፍረስ ከአካባቢው ርቆ መናኞች ከሚጣሉበት ዳርቻ ላይ ተገኘ፣ ማህበረሰቡ ናቀው ተጠግቶም «እግዜር ይማርህ» የሚለው በማጣት የሰው ረሀብተኛ ሆነ።
- **<u>ስሜታዊ</u>** ገፅታው በህሊናው እያወጣ እያወረደ «ለምን ይህ ሆንብኝ» በሚል ጥያቄው ተጨናቂ ሰው በመሆን ተሰቃየ ይልቁኑ ራሱን በእግዚአብሔር ፊት ለማሳየት ያደረገው ጥረት ከንቱ በመሆኑ ጉዳይ ያልተቋረጠ የህሊና ሙግት ፈጠረበት፣
- **<u>መንፈሳዊ</u>** ገፅታ፡- ከቀደሙት ሁሉ የከፋ የሆነበት ስቃይ ይህ ነው፤ ሰው ከሰው ጋር በተያያዘው ጉዳይ ላይ መፍትሄ አልታጣለትም ግና ጉዳዩ ከእግዚአብሔር ጋር የተሳሰረ





አድርጎ እግዚአብሔር ይህን በእኔ ላይ ሲበይን ምን አይቶብኝ ይሆን? እውን ከሌላው እኔ እሻል ብሆን እንጂ እንዴት ከማንም የከፋ መከራን እግዚአብሔር በእኔ ላይ ያመጣል? በሚል መንፈሳዊ ውጥረት ውስጥ የገባ ሰው ሆነ፣

**የኢዮብ ምላሽ፡-** በራሱ ላይ ማጉተምተሙን ባይተውም ነገር ግን እግዚአብሔርን ለመቃወም የበረታ አቅም አልነበረውም፤ በቅይማት መፅሐፍ የተነሱት ሦስት ጥያቄዎች በእርሱም ዘንድ ተነሺ ሆነዋል።

ይልቁኑ ለባለጉዳዩ ወዳጆቹ የአቅማቸውን መከሩት። ባለቤቱም «እግዚአብሔርን ሰድበህ ከደህ ከእርሱ ተለይ» አለችው።

በመሰረቱ የኢዮብ ሚስት አቋም በመፍትሄነት ተመራጭ ሊሆን ይችላል። የቅይማቱ ሪቻርድ፡- በመከራ ጫፍ ላይ ራሱን ሲያገኝ ያደረገው ቅዱሳት መፅሐፍቱን ማቃጠል እና ኢየሱስ ክርስቶስን መካዱ ነበር።

የኢዮብ ሚስት እግዚአብሔር የለሽ የሆነው ማህበረሰብ ጉዳዩን «ጌታ፣ አዳኝ፣ መድህኒት» አለኝ ብሎ ስለማያምን በሆነው ሁሉ ላይ ያለው ሙግቱ በገደብ ነው፤ ሄዶ ሄዶ ይተወዋል።

ቅዱሳን ግን ይፈተናሉ፤ መለኪያ ስላላቸው፣ መመሪያ ስላላቸው አጣብቂኝ ውስጥ ይገባሉ፤ ምን ማድረጉ ነው? ምንስ ባደርግ ነው? ብለው ጠይቀው በፍፃሜው «መቀየምን» ምርጫቸው ያደርጋሉ።

የኢዮብ ሚስት ግን እግዚአብሔርን የሌለ ያህል በመቁጠር «ሞትም ቢመጣ ይምጣብህ» የሚል መግለጫ አወጣችበት። ኢዮብ እንደ «ሰነፍ ሴት» ቢቆጥራትም እሷ ግን እውን የሆነውን በመተው መገላገልን ምርጫው እንዲያደርግ ገፋቻው ኢዮብ የተወለደበትን ቀን እረገሚል፤ ወዳጆቹ ተሳልቀውበታል፤ ዘርፈ ብዙ ጥቃት በላዩ ላይ ነግሷል ግና እግዚአብሔርን ልብ ያለበት አቅም በምዕራፍ አንድና ሁለት ላይ ያነሳነውን የሰውን ገደብ፣ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ከግምት አስገብቶ መኖር ነበር። እነዚህን ምስክሮች ሳንዘነጋ ቅይማት ምን መልዕክት አስፍሮ ተዋወቀን።

## ቅይማትና ዝክሮቹ

ፊሊፕ ያንሲ በርካታ መፅሐፍትን የፃፈ ሰው ነው፤ በ1988 የፃፈው «Disappointment with God» ሰፊ ስርጭትን አግኝቶ ተነበለታል። ከየትኛውም ስራው በበለጠም እሱን አሳውቆታል፤

ይህ መፅሐፍ በ1999 እ.ኤ.አ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተወዶ የኤስ.አይ.ኤም. የስነ ፅሁፍ ክፍል (SIM) በአማርኛ ቋንቋ አስተርጉሞታል፤ እሱን መፅሐፍ የማረም ዕድል ገጥሞኝ አንብቤ የሰጠሁት ምስክርነት *አንድ ነው፤ አያነበቡት የሚሞግት፡- በሙግቱም መርታትን ወይም አለመርታትን የሚያፈልቁበት ሥራ መሆኑ ተገንዝቢያለሁ።*

«ቅይማት» ለዚህ መፅሐፍ የተሰጠው ስያሜ ነው፤ ሰዎች ብጤያቸውን ሳይሆን ርቀው ተጉዘው ከእግዚአብሔር ጋር ቢቀያየሙ ሊቀየሙበት የሚችሉት ርዕሰ ጉዳይ ምን ምን ሊሆን እንደሚችልና እንደቻለም ያስረዳል፤ «**በአደባባይ የተፈሩ ሦስት ጥያቄዎች**» በማለት ከፊት ሽፋኑ ላይ ያስተዋውቃል።

- እግዚአብሔር አድሎአዊ ነውን?
- እግዚአብሔር ፀሎትን አይመልስምን?
- እግዚአብሔር ስውር ነውን?

እነህ ጥያቄዎች ሊጠየቁ የበቁት በአደባባይና በገሀድ ሳይሆን በውስጥ ነበር። የነፍስ ጥያቄ፣ ለሰው የሚያጋሩት የመሰለ ፈተና ሆኖ ራስ ከራስ ጋር የሚላተምባቸው መጠይቆች ናቸው። በቀደሙት ምዕራፎቹ ሰውን በልኩ አይተን፤ እግዚአብሔርን በተረዳነው መጠን ልብ ብለንዋል። ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔርን መቀየም በእርግጥ መቻል አለመቻሉን ከዚህ መፅሐፍ ላይ ተነስተን እንመከራለን።

የ East Africa Baptist College በ2002 ያስመረቃቸውን የዲግሪ እና የዲፕሎማ ተማሪዎችን ስራዎች በ2003 በቤዛ ባፕቲስት አውደ ጥናት ላይ ቀርቦ ተፈትሾ ነበር። «የእግዚአብሔር ልዐላዊነት በድነት ሥራው ላይ» የሚለው የወንድሜ የመኮንን ታደሰ ዝግጅት ቀርቦ ውይይት ሲከፈት አንዲት ታዳሚ በመሰረታዊ ጥያቄዎች ተሞልታ ብቅ አለች። በመሰረቱ በመመረቂያ ፁሑፍ ላይ የተነሱት፡- ክርስቶስ ለገዛ በጎቹ ብቻ የመሞቱ ነጥብ፣ በጎቹ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የተጠሩ እና የተወሰኑ መሆን፣ እንዲሁም ሰው እግዚአብሔር ካላዳነው በቀር በራሱ የመዳን አቅም ፈፅሞ የሌለው መሆኑተገልጦ ነበር፡ በጊዜው ከታደሙት መካከል አንዲት እህት ፈራ ተባ ብላ እጇን አወጣች አቅራቢውንም «ያቀረብከው ከምርህ ነው! እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ የሰራው የመስቀል ስራ ለዓለሙ ሁሉ አይደለምን?... እውነት ያልከው እውነት የሚሆን ከሆነ እኔ እግዚአብሔርን እቀየመዋለሁ» በማለት ደመደመች።

የአቅራቢው ምላሽ «እኔን ብትቀየሚኝ ይሻላል እንዴት አንቺ እግዚአብሔርን ልትቀየሚ ትችያለሽ?» በማለት ነበር ወደማብራሪያው የገባው።





ቅይማት ሮጦ ሮጦ ድንገት ከፈተና በወደቀው ሪቻርድ ሕይወት ላይ አትኩሯል፤ «እግዚአብሔር ካለ እቀየመዋለሁ ከሌለም እገላገላለሁ» ወደሚል ደረጃ ደርሷል፤ ይህንንም በአደባባይ ይዞ መቀየሙን ለፊሊፕ ያንሲ አረዳው።

በዚህም እሰጥ አገባ እያንዳንዳችን ራሳችንን እንድንመዝን ያደርገናል። ፊሊፕ ያንሲ በመቅድሙ ያስተዋወቀን «ከእግዚአብሔር ጋር ስለመቀያየም እየፃፈ መሆኑን የሰሙ ወንድሞችና እህቶች እየደወሉ «እባክህ ስማችንን ሳትጠቅስ የኛንም የመቀየም መንስኤ እያጋመድህ በሥራ ውስጥ ከተተው» አሉት፤ ያሉት ሁሉ በዝግጅቱ የየገዛ ጥያቄያቸው እንዲመለስ ናፍቀዋል፤ ሌሎች አጋሮችም እንዳላቸው ለማረጋገጥ ዕድሉን ሊጠቀሙበት ፈልገዋል።

እንደ ፊሊፕ ያንሲ አገላለፅ «...ብዙ ሰዎች ከክርስትና እምነታቸው በሚጠብቁትና በሚሆኑት መካከል ሰፊ ክፍተት እንዳለ አስተውያለሁ... አንዲት ሴት እንዲህ ብላለች «ብዙ ጊዜ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ግላዊ ግንኙነት መመስረት» የሚል ሐረግ ስሰማ ኖሬአለሁ የሚያሳዝነው ግን ይህን እግዚአብሔርን አላየሁትም፣ ድምፁንም አልሰማሁትም ወይም ተለማምጄው አላውቅም ከተነገረን መልዕከት ወይም ከእኔ በአንድ የተበላሸ ነገር አለ ማለት ነው» አለችው።

«ቅይማት የሚፈጠረው፡- ልምምዳችን በተስፋ ከምንጠባበቀው አሽቆልቁሎ ሲገኝ ነው...ቅይማት የዋጣቸው ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለመመርመር ብዙም ትዕግስት እንደ ሌላቸው አውቅያለሁ... ይልቅኑ አንድ ጊዜ ለጓደኛዬ ስለማዘጋጀው መፅሀፍ ሳብራራለት ራሱን በመነቅነቅ «ከዚህ በፊት ለእግዚአብሔር ሥነ ልቦናዊ ምርምር እንዳላደርግሁለት እርግጠኛ ነኝ» በማለት መለሰልኝ እኔ ግን እንዲህ ለማድረግ አልፈለኩም ነበር። ያልኩት ቃል፡- «እግዚአብሔርን በይበልጥ ለማወቅ እፈልጋለሁ አንዳንድ ጊዜ ግን ለምን እንዲህ በምስጢራዊ መንገዶች እንደሚሰራ ወይም ደግሞ ለምን ምንም የማይሰራ እንደሚመስል ለማወቅ እሻለሁ...» እውነቱን ልንገራችሁ እኔ የምፅፈው በአንድ ወይም በሌላ ወቅት የእግዚአብሔርን ዝምታ ላደመጡ ሰዎች ነው፤ እነርሱንም ሆነ እራሴን መርዳት እፈልጋለሁ ለዚህ ደግሞ እግዚአብሔርም ይረዳኛል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ» አልኩ። ይህ ከመቀየም የተቆጠረ መንደርደሪያ ነው፤ ይህ መተዋወቂያ መዝ. 44፡ 23-24 ንና እኒ ዲላርድን ቃል ከግምት እንድናስገባ ያስገድደናል።

አቤቱ ንቃ ለምንስ ትተኛለህ?
ተነስ ለዘወትርም አትጣለን።
ለምንስ ፊትህን ትሰውራለህ? (መዝሙረኛው)

«ከቤት ውጭ ፅልመት ባጠላበት ሰፍራ መቀመጥ የለብህም ነገር ግን ከዋክብትን ለማየት ከፈለግህ ጨለማ መኖር እንዳለበት ትገነዘባለህ። ከዋክብት ጨለማውን እንደ አንድ መስፈርት አይፈልጉም አይጠይቁትም።» (አኒ ዶላርድ)

***

እነዚህ ሁለት ገለፃዎች አንደኛው ከቅዱስ ቃሉ አንደኛው ከተሞክሮ እና ከገጠመኝ የመጡ ናቸው፤ ሰው በሰው ኑሮ ውስጥ እግዚአብሔርን ሲመለከት የሚረዳበትንም እይታ ነው የሚገልፀው።

ፊልፕ ያንሲ ቅይማትን ከመፃፉ በፊት ለቅይማት መነሻው የነበረውን ቀዳሚ መፅሐፉን አልረሳውም «where is God When it Hurts?» «በተጎዳን ጊዜ እግዚአብሔር ወዴት ነው?» ይህን ካስነበበ በኋላ ብዙዎች ሰቆቃቸውን አካፈሉት በውጤቱም ይህን መፅሐፍ ለመፃፍ ተነሳሳ:-

**አንዷ:-** ቆንጆዬ ልጅ ወለደች። በዚህም ባልና ሚስቱ ተደሰቱ ግን ህፃኒቱ ዘላቂ ችግርን ይዛ ተወልዳ ነበርና ያላቸውን ሀብት ሁሉ በልጅቱ ሕክምና ላይ አዋሉ፤ ሀብታቸውም አለቀ፤ ኑሮአቸውም መቀመቅ ወረደ፤ በዚህ ችግርም ወላጆች ተለያዩ፣ ልጅቱም በሰቃይ መኖሩን አዘለቀች፤ ከዚህም የተነሳ የልጅቷ እናት «አፈቅረዋለሁ ያለችውን እግዚአብሔር አብሮኝ አልነበረም» አለችው (ገፅ 1)

**ሌላኛው:-** በአንድ «የእንመካከር» የስልጠና ዝግጅት ውስጥ ከክርስቲያን ቤተሰብ የተወለደችው ወጣት አደገች፤ ተወደደች፤ በዚህ ወቅት የባል ወንድም በገጠር «በመሀይምነት» እንዳለ ተሰማ፤ ሚስትም (እናቷ) «አዲስ አበባ ካልመጣ ካልተማረ» የየቀኑ ሙግቷ ሆነ። መጥቶም በቤታቸው አደገ፤ ተማረም ግና ያቺን አንድዬ ልጅ አታሎ ደፈረ። በዚያው ወቅት አረገዘች። በወላጆች ምክር የተረጋጋ ውሳኔ ላይ ሳይደረስ ፅንሱን አስጨነገፈች። በዚህ ውዝግብ ባልና ሚስት የነበራቸውን ፍቅር እያጡ መማረርን መገለጫቸው አደረጉ። ልጅቱ ብታገባም እንኳ የመውለድ ችግር እንዳለባት እንዲሁም በዘላቂ በሽታ መያዟ፣ እናትየው በመኪና አደጋ የአከርካሪ አጥንቷ መሰበር፣ አባትየው ወንድሙን ለፍርድ ባለማቅረብ ተጠያቂ ሆኖ ወደ እስር ቤት መጣሉ ተደራርቦ በሁሉም ቤተሰብ አባላት ዘንድ «እግዚአብሔር ሲያጠፋን መጥቷል» በሚል ቁዘማ ውስጥ ወደቁ።

**የቅይማት:-** ደራሲ ሰዎች እየመጡ በአደባባይ የተፈሩ ሦስት ጥያቄዎች ባነሱለት ቁጥር እሱም ሰው በመሆኑ አብሮ ጠያቂ መሆኑን ከግምት አስገብቶ ስለሚፅፈው ወይም ሊፃፍለት ስላለው የጥያቄ መልስ ግልጥልጥ ያለ ግንዛቤ ይኖረው ዘንድ እያጠና ተማፀነ።

ሪቻርድ የስነመለኮት ተማሪ ሆኖ ሁለተኛ ድግሪውን እየሰራ ሳለ ነበር:- ፊሊፕ ያንሲ





ስለ መፅሐፉ አስተያየት እንዲሰጠው ደውሎ የነገረው፤ የሚፅፈው «በኢዮብ መፅሐፍ እና በኢዮብ ተግዳሮት ላይ» ነበር፤ ተመካከረው መፅሐፉ ማተሚያ ቤት ከገባ በኋላ ግን «ድንገት» በሚመስል ጥሪ ሪቻርድ ፊሊፕን ለማግኘት ተጣደፈ መገናኘታቸው ደስ እያሰኘም ነበር፤ ተማሪው «መቶ በመቶ እግዚአብሔርን መቀየሙን ሲያረዳውና መፅሐፉ ታትሞ ከሚወጣ እሱ ቢሞት እንደሚመርጥ» መንገር ነበር ፤ «እውነቱን ልንገርህ ፊልፕ በመፅሐፉ ውስጥ ያሰፈርኩትን ሁሉ አላምንበትም ይህን ልነግርህ ብቻ እፈልጋለሁ...እግዚአብሔርን «እጠላዋለሁ...በእግዚአብሔርም አላምንም» በማለት ሲቃ እየተናነቀው ተናገረው ቀጥሎም ወደ ኋላ ወደ ፊትም እያለ ዕድገቱን ተናዘዘለት፤ እናት አባቱ ተጣሉ ለማስታረቅ ጣረ ግን ከመፋታት አልቀሩም፤ እጮኛው ሼረን ምክንያቱን ሳታሳውቀው ተለየችው፤ ከርሞ ከርሞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄድ አላስካ ላይ ተከስክሶ ስላለቁ ዘጠኝ ሚሲዮናውያን እያዘነ ተናግሮ ግን በትይዩ በሌላ አውሮፕላን ሲጓዝ አደጋ ገጠመው እና በተረፈው ሌላ አገልጋይ ላይ መደሰቱን «እናመሰግን» በማለቱ ተገረመበት (ገፅ 12)።

«በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ምን እያደረገ ነው?» ብዬ ለመንኩት ምንም ምላሽ አልነበረም ከአራት ሰአት ፀሎቴም በኋላ ያው ነበር፤ ከእነዚህ ሁሉ በኋላ «ለምን ራሴን ሳሰቃይ ልኑር ለምን እግዚአብሔርን ዘንግቼ እንደ አብዛኞቹ የአለማችን ሰዎች አጭሩን ሕይወቴን አልመነዝርም?» በማለት ወሰንኩ። ከዚህ ውሳኔዬ በኋላም በማጠቃለያው ፈተና እንዳለፍሁ ወይም የመንጃ ፈቃድ እንደተቀበልሁ ያህል እፎይታና ነፃነት ተሰማኝ፤ በቃ፤ ትግሌ ተፈፀመ ሕይወቴም የእኔው ሆነች... ከዚህም የተነሳ የተፃፈው መፅሐፍ እኔን አይወክልም... «እግዚአብሔር የለም ካለም ልቀየመው መብት አለኝ» በማለት አቋሙን በመግለፅ ነበር (ገፅ 14-15) ስፊ ትንታኔው የጀመረው።

ይህ ዝግጅት መላውን የመፅሐፉ ታሪክ ለመተረክ እቅድ የለውም፤ ዝግጅቱ እግዚአብሔርን መቀየም ከተቻለ (የሚቻል ከሆነ) እንዴት ነው እያንዳንዳችን ይህን መሰል ገጠመኝ በመጣብን ቁጥር ሁኔታውን የምንቋቋመው፤ ተቋቁመንስ በትክክለኛው መሰረት ላይ የምንቆመው? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽን ወይም አወያይ ጭብጥን ማድረስ ነው። ከዚህም የተነሳ ዝርዝር ስራ በመፅሐፉ ላይ አይኖርም፤ ግርድፉ ግን ጠቃሚ ነው።

## ሰው የማይደፍራቸው ጥያቄዎች

በሪቻርድ ጀርባ አድብተው የመሰጉት ጥያቄዎች፤ እግዚአብሔር ኢ-ፍትሐዊ ነው፣ እግዚአብሔር ዝም ባይ ነው፤ እግዚአብሔር ድብቅ ነው የሚሉ ናቸው እነዚህን ጥያቄዎች ብዙዎች ጮክ ብለው አያሰሟቸውም ቢያደርጉት ትህትና የጎደላቸው ወይም መናፍቅ ተብለው ይለያሉ (ገፅ 16)

እነዚህ ለሆሳሳውያን ከህዲዎች አይደሉም በመሰረቱ እውነተኛ ኢአማንያን (ኤቲስቶች)

ከእግዚአብሔር ጋር ቅይማት አይፈጥሩም። እነርሱ ከእግዚአብሔር የሚጠብቁትም ሆነ የሚቀበሉት ምንም ነገር የላቸውም ይልቅስ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ሰዎች በምላሹ ከእግዚአብሔር አንድ ነገር መጠበቃቸው ተፈጥሮአዊ ነው። በዚህም ወቅት ነው መተላለፉ የመጣው፤ የሚመጣውም። (ገፅ 18)

ፊሊፕ ያንሲን ሪቻርድ «ቅይማቱን» አጫውቶት ተለይቶታል፤ ግና ከሶስት ዓመት በኋላ በሺካጎ ተገናኝተው በድጋሚ ተጨዋውተዋል፤ ያኔ ደግሞ ያጫወተው ካትሪን ኩልማን የምታካሂደውን የፈውስ የጅማ አገልግሎት በቴሌቪዥን መስኮት ተከታትሎ፤ በውስጡ እየሞተ የነበረው የእምነት እይታ ዛሬስ ሊለወጥ ነው ብሎ ማመን ነበር፤ «ዳሰኛል» የሚለው መዝሙር እየተዘመረ በቃሬዛ ሽከም አንድ ሰው ገባ። እሱ ከቃሬዛው ተነስቶ በመድረክ ላይ ሲመላለስ ተደነቀ። ሰውየው ደግሞ ሀኪም ነበር ዶክተር። በማይድን የሳንባ ካንሰር ተይዞ ስድስት ወራቱን እያገባደደ ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜም ቆሞም ሄዶ መሰከረ።

በዚህ ግዜ ነበር ሪቻርድ ስሙን ፅፎ አድራሻውን አፈላልጎ አገኘ ከዚያም ደውሎ ስልኩን ላነሳቸው ሴት «እባክዎ ዶክተር...» እፈልጋለሁ ይላታል፤ ከረዥም ፀጥታ በኋላ «እሱ እኮ ባለቤቴ ነው፤ አሁን ግን አታገኘውም ሞቷል» መባሉን በመስማቱ ያዝናል። ፊሊፕንም «ዛሬም ይህን መሰል ታሪክ ይከተለኛል እንግዲህ ስማኝ! የኢዮብ ሥራዬ አጥፊ እንጂ አልሚ አይደለም» ይለዋል (ገፅ 21)።

ሪቻርድ «እውነት እግዚአብሔር ታማኝ አምላክ ከሆነ ከሦስቱ ጥያቄዎች አንዱን ብቻ እንኳ ቢመልስ! እንኳን አለሙ ሁሉ ያምንበት ነበር፤» «ወንድ ከሆነ ለምን ይህን አያደርግም» (ገፅ 22) የሚለው ሙግት አሁንም ትኩስ ነው።

እውን ግን ጥያቄዎቹን በሙሉ እግዚአብሔር ቢመልሳቸው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ይጣጣማልን? እውን እነዚህ ጥያቄዎች በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ተመልሰው አያውቁምን? ለቀዳሚው ጥያቄ «አይጣጣምም» ለሁለተኛውም «ተደርገው ያውቃሉ» ነው።

ፊሊፕ ያንሲ እስራኤላውያንን የብዙ ማብራሪያ መሰረቶች አድርጎ ለማስተማር ካነሳው ገለፃ አንዱ «ሕዝቡ ግልፅ የሆነ መመሪያን እግዚአብሔር ሰጥቶአቸው ሳለ እሱን ለመታዘዝ አይፈልጉም ነበር «ከአሞራውያን ጋር ወጥተው እንዳይዋጉ አዘዛቸው እነርሱ ግን ወጡ፤ በመውጣትም ተሸነፉ፤

እስራኤላውያንን ፊሊፕ እግዚአብሔር እንደ ህፃናት መኖር የሚችሉበትን ሲያመቻች እንደ አዋቂ መኖርን ምርጫቸው ያደርጉ እንደነበር ገልፃል (ገፅ 26)

እስራኤላውያን በተአምራት ተትረፍርፈዋል፤ ግን በእነርሱ ላይ የታየው ግን የተአምራት





ሱሰኞች መሆንን እንጂ ተአምራቱ የእግዚአብሔር ፈላጊዎች አላደረጋቸውም እነርሱም እግዚአብሔርን አልፈለጉም (ገፅ 28)።

ሪቻርድ «እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ውስጥ ምን ምን ያህል ሥቃይ እያስከተለ እንዳለ የሚያውቅ አይመስልም» በማለት ጮኋል። እነዚህን የመሰሉ ተገዳዳሪና ቅን ጩኸቶች በአማኞች ሁሉ ሊከሰቱና ሊመጡ ይችላሉ።

ይህ ዝግጅት ሪቻርድ የሁላችን ተወካይ ሆኖ እሱም ለካ ሰው ነው፤ እንደ እኛው ነው፤ እንድንል ያግዛል ከዚህ ባሻገር ግን አማኝ ተመሳሳይ ነን ብሎ አይቆምም ልዩነት ማምጣት አለበት።

## ልዩነቱ ወደ ምንጩ

ፊሊፕ **«ምንጩ»** የሚል ርዕስ ሰጥቶለታል፤ የሪቻርድን ጥያቄ ለመመለስ አስራ አምስት ቀናት ቤቴን ለቅቄ ፀጥታ ወደሚገኝበት ስፍራ ወደ ኮሎራዶ ሄድኩኝ ይለናል፤ በርካታ መፅሐፍትን ይገኼ ሄጅያለሁ ግን በእነዚህ ሁሉ ቀናት መጽሐፍ ቅዱሴን ብቻ አጠናሁ፤ እግዚአብሔርም ተለመነኝ በማለት ገለፃውን ያረዝማል፤ ዝግጅቱ ለዚህ መፅሐፍ ሲመጠን፤-

«ለተለምዶአዊ አኗኗር የዳረጉን ብዙ ረብ የለሽ ልምምዶችና እምነቶችን ይዘናል» ይላል በክርስትና የሕይወት ዘመኖቻችን በአመዛኙ ያደመጥነው፤ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው፣ ሁሉን አዋቂ ነው የሚሉትን ነው። ከዚያ በተቃራኒው የገለፁትን ልብ አንልም፤ ወይም አልሰማንም ወይም ለመስማት አልፈለግንም ከዚህም የተነሳ የቅይማት ጥያቄዎቻችንን በሙሉ በሰማናቸው ብቻ ይመዘናሉ።

ብዙ የወንጌል ስርጭቶች «ለጥያቄያችሁ ሁሉ ኢየሱስ መልስ ነው» በሚል አጓጊ መፈክር ሕዝቡን ያመቻቻሉ።

ዘማሪያንም «ለጥያቄ ሁሉ ኢየሱስ መልስ ነው» ብለው ይዘምራሉ። በልሙጡ ይህ ገለጣ ደስ ያሰኛል፤ ተግባራዊ በሆነው የሰው ኑሮ ውስጥ ግን ኢየሱስ ለሁሉም መልስ አይሆንም፤ መልስ እንዲሰጥም አይገደድም፤ ይልቅስ «መልስ ሊሰጥ የማይችልበት» በርካታ ጉዳይ እንዳለ ማወቅ የተገቢም ተገቢ ነው።

ፊሊፕ ቅዱሳን መጽሐፍትን ብቻ የሙጥኝ በማለቴ ልብ ያልኩት ቁም ነገር በማለት ከዘፍጥረት መጽሐፍ ያስተዋለውን ያስነብበናል።

የራሱን አንድ ነገር ከእነርሱ ውስጥ ለማየት በመሻት በራሱ አምሳል ሰዎችን ፈጠራቸው። እነርሱ ደግሞ እንደመስተዋት ሆነው ራሱን በማንፀባረቅ መኖር ግባቸው ነው፤ (ገፅ 36)

ይህም ቢሆን ግን እነዚሁ ሰዎች በትይዩ በእግዚአብሔር ላይ የማመፅ ችሎታም የነበራቸውም ነበሩ።(ገፅ 26)

በዚህም አቋም «መልካሙንና ክፉውን የሚያሳውቅ» የተባለለትን ዛፍ ለመሞከር የአቋም አንድነት ኖራቸው አደረጉት። ለዚህ እግዚአብሔር የሰጠው ምስክርነት «እነሆ አዳም መልካሙንና ክፉውን በማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ...» የሚል ነበር (ዘፍ 3 ገፅ 37)

**አዳምና ሔዋን** በራሳቸው ምርጫ በእግዚአብሔርና በእነርሱ መካከል መጋረጃ አበጁ ፊት እንደ ልብ ይገናኙ ነበር፤ አሁን ደብቁኝን መረጡ፤ መራቅን መሸሽን መለያ አደረጉ እንዲህም ሆነው ግን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ማድረግን ፈልጓል፤ ያንንም በዘመናት ውስጥ አከናውኗል። ቅይማት ከሚዘነጋቸው ጭብጦች አንዱና ዋንኛው እግዚአብሔር ከሰው ጋር ማበርን የመፈለጉ እና የመተግበሩን መገለጫ ልብ አለማለት ወይም አለማወቅ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ሰው ሕግጋትን ሁሉ እያፈራረሰ መዝለቁን አልሸሸገም። አዳም አጠፋ፤ «ወዴት ነህ» ለማለት መጣ ቃየልን «ምን አደረገህ» ለማለት መጣ። የሰው ተቃዋሚነት ግን በየጊዜው ስለ ተስፋፋ በጥፋት ውሃ ቀጣ። ከዚያም ሰውን ዳግመኛ በውሃ ጥፋት እንደማይቀጣ በመግለፅ ግንኙነቱን አሳደገ። ግና ሰዎች ኋላ ላይ የባቢሎንን ግንብ በመስራት የእግዚአብሔር ተቃራኒ ሆኑ፤ እግዚአብሔር ግን ሊጠፉ ያላቸውን ከቃል ኪዳኑ የተነሳ ሳያጠፋ ተወ።

በእነዚህ ዘመናት እግዚአብሔር በግልፅ ስለሚሰራም ማንም ሰው ስለ ድብቅነቱ ወይም ዝምተኛነቱ አይወቅሰውም።

ዘፍጥረት 12 ሲጠና ግን እግዚአብሔር ከአብርሀም ጋር ተደራደረ፤ «ታላቅ ሕዝብ አደርግሀለሁ...ስምህንም አከብረዋለሁ የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» አለለት።(ዘፍጥረት 13፣14፣15) ይህ ሰው ኑሮው ሲፈተሽ ለዚህ ዝግጅት ጥሩ መነሻ ነው፤ እግዚአብሔርን በዘመኑ «ተቀይሞት» ስለነበረ።ብዙ መገለጦች ተአምራት በፊቱ ሆነዋል ግን የተስፋ ቃሉን በተመለከተ ዝምታ ሆነ ግራ የሚያጋባ ረዥም ፀጥታ ሆኖባቸዋል።

ግና የግንኙነትን መስመር በማቋረጥ ወደ ኋላ አላላም፤ አላሉም። አብርሀም ልኩን ተረድቷል። ማመን ማለት ለማመን የሚያስችል ምንም ምክንያት በሌለበት ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ መደገፍን ተግባራዊ ማድረግ ነው። አብርሀም ዘሩ ምድርን ሲሞላ የማየት ዕድል ባይገጥመውም ግን





ይስሀቅን አቅፏል። በዕብራውያን 11 ም በእምነት ቅይማቱ መረታቱን አሳውቋል።

ፊሊፕ ያንሲ በመገረም ከሚያነሳቸው ግንዛቤዎች ውስጥ ይስሐቅ መካን ሴት አገባ፣ ልጁ ያዕቆብ እንዲሁ፤ የቃል ኪዳን እምነት እናቶች - ሣራ፣ ርብቃ፣ ራሄል፣ ልጅ የመውለጃን ሰዓት ተላለፉ፣ ከዚህም የተነሳ የወጣትነት ዘመናቸውን በጭንቀት እና በጉድለት አሳለፉ፤ ይህንን አልፎ ግን ብርሀናት ፈነጠቁ፤ እነዚህ ጨለማዎች ከእምነት በስተቀር በምንም ሊሞሉ አልቻሉም።

በዕብራውያን 11 ከተነሱት ሰዎች ውስጥ ዮሴፍ አንዱ ነው፤ በዘፍጥረት የመጨረሻ ምዕራፎች ላይ ሰፊ ገለፃ የያዘውም እርሱ ነው፤ የዚህንም ሰው አኗኗር ግን ልብ ማለት እና እግዚአብሔርን «ለመቀየም» በቂ የመሰለ ምክንያት ያለ ሲመስል ልከኛው መርቺያ ምን እንደሆነ ሕይወቱ ያስረዳል።

ዮሴፍ «ደግነት»ን መለያው ስላደረገ ብቻ መከረኝነትን እንደ ውሃ ጠጣ፣ የሚላክ በሌለበት ለአባቱ «አለውልህ» ብሎ ተላከ፤ ለወንድሞቹ ሕልሙን ነገረ፤ በዚህ ጦስ ከጉድጓድ ተጣለ፤ የወሲብ ፈተና ገጥሞት በተቋቋመ፤ ወደ እስር ቤት ወረደ፤ የእስረኛውን ህልም በፈታ ፈፅሞ ተረሳ...እነዚህ ሁሉ «ተቀየምኩ» ለማለት በቂ ቢሆኑም ታሪኩ ግን «እግዚአብሔር ሁሉን ለበጎ አደረገው» በሚል ተጠናቀቀ።

ሰዎች የነገን ምንነት አያውቁትም፤ በእነርሱ እጅ ስላልሆነ፤ ሰዎች ሊያውቁ የሚችሉት የትናንትን ነው፤ እሱም ታይቷልና ነው፤ የታየው ግን ከነገ ጋር ተያይዞ የሚመጣውን ፍፃሜ ከቅዱስ ቃሉ ጋር በማነፃፀር ማየት ተገቢ ነው፤ በዚህ ሂደት ውስጥ በርካታ ጥያቄ እና እንቆቅልሽ መፍትሄን ያገኛል።

## የዝምታን ዘመን የመዝለል ክባዜ

ርዕሱን ቀይሬዋለሁ ፊሊፕ ያንሲ «በቀጥታ የሚተላለፍ የፀሐይ ብርሀን» የሚል መግለጫ ነው ለምዕራፍ 8 የሰጠው ከእሱ በበለጠ ግን የእኔ «ገላጭ» ነው ብዬ አመንኩኝ።

ብዙዎች በዘፍጥረት እና በዘፀአት መካከል የ400 የፀጥታ አመታት መኖራቸውን ልብ አይሉም። አለማለታቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ ዘመን እንዴት እንደአለፈ የተገለጠ ታሪክ ባለመኖሩ ሊሆን ይችላል። ባይኖርም ግን 400 ዓመታት ነበሩ። ዛሬ ላይ ቆመን ስለገነነችው አሜሪካ እናወራለን ይህ ታሪክ የ400 ዓመት ታሪክ ብቻ መሆኑን ልብ አንልም፤ ከዘፍጥረት ምዕራፍ 50 ማግስት ጀምሮ ምን ዐይነት እምነት፣ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍናና አኗኗር እንደነበረ ልብ ብንል መልካም ነው። ከእግዚአብሔር አኳያ ግን እስራኤላውያንን እግዚአብሔር ዝም ብሎአቸው ነበር። በዚህ

ወቅት ዕብራውያኑ እግዚአብሔርን ተቀይመውታል፤ ተለይተውታል፤ ከደውታል።

በመሰረቱ የሰው ልጅ ተፈጥሮ ፈጥኖ ድልን መስማት፣ ተጋድሎን ማንበብ ስለሚፈቅድ ነው ዘፀአት አንድን የዘፍጥረት ህምሳ ቀጣይ ምዕራፍ የሚያደርገው፤ ከዚያም በመቀጠል የድል በድል ታሪክን በህሊናው ይዞ የሚዘልቀው፤ ዝምታዎች ከዚህ ኋላም ነበሩ፤ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መካከል 400 ዓመታት በእግዚአብሔር ዝም ባይነት ፀንቷል። እኛ ግን ከብሉይ 39ኛውን ጨርሰን ወደ ማቴዎስ የምንሸጋገረው ያለ ብዙ መጨናነቅ ነው፤ ተራምደን አሁንም የመቻልን፣ የማድረግን፤ የተአምርን ድርጊቶች በማንበብ ውለን እናድራለን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ12 ዓመት ዕድሜው የሆነውን ወንጌል ነግሮን ከዚያ በኋላ 30 ዓመቱ ላይ ያመጣናል። ይህንንም ገፅ እንደ መግለጥ ያህል ቀጥረን በመሀል የነበሩትን የኢየሱስ ክርስቶስ 18 ዓመታት እንዴት ነበሩ ብለን በታሪኩ ውስጥ አናጋምድም። ከፉ ጊዜያት፣ መራራው ዕድሜዎች፣ ፅኑ ውጣ ውረዶች በኢየሱስ ሕይወት ሳያልፉ አልቀሩም፤ ይህም ከመጣበት ተልዕኮ የተነሳ ሊሆን የሚችል ነው።

ከ18 ዓመታት እስከ 400 ዓመታት የተተዉ ዘመኖችን ማወቅ ቅይማት እንዲቀንስ፤ እንዲረግብ ወይም እንዳይኖር የማድረግ አቅምን ይፈጥራል።የዕብራውያን ፀሐፊ *የተፃፈው ሁሉ ለትምህርታችን እንደሆነ አረጋግጧል፤የሚጠቅም ከሆነ እና አቅማችንን የሚገልፅብን ከሆነ በቅዱሳት መጽሐፍት ተጠቁመው የተተዉትን መመርመር ድንቅ መፍትሄን ሊያቀብለን ይችላል።*

**አማኞች** እግዚአብሔርን በሁለንተናው ማንነቱ ሊረዱት ይገባል፤ ሰውንም በእግዚአብሔር ገፅታው እንዲሁም በውድቀት ማንነቱ መገንዘብ ትክክለኛ አቅምን ይፈጥራል።

በርካታ አንባቢ ተረቱን እውነተኛ ታሪክ ወይም ግኝት አድርጎ ይረዳል፤ በዚያም ሲያምን ከእውነተኛው ይርቃል ወይ ልክ ነው በማለት ከእምነቱ ጋር ይገዳደራል፤ በዚህም ለቅይማት መነሻ ይሆናል።

የዝምታ አባዜ፡- በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መካከል ረዝሞ በመምጣት ሰዎች የየራሳቸውን ግንዛቤ እና እምነት ፈጠሩ፤ ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ሀሳብ ጋር የራቁ ድርሳናት በመተካታቸው በኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን የተገደገዱ እንቅፋቶች ሆኑበት፤ ሆኑባቸው፤ በጊዜው የነበረው መፍትሄ እንቅፋቶቹን አግባብ በሆነ መንገድ ማስወገድ በምትኩም «ልኩን» መተካት ነው፤ ይህ ለቅይማት መንስኤ የሚሆኑ ነባራዊ (ሰዋዊ) ክስተቶችን ይቀርፋል፤ በምትኩም ግንዛቤን በማስፋት መረጋጋትን ያመጣል።





ባልተገለፁት የኢየሱስ 18 ዓመታት ብዙዎች በ30ኛው ዓመቱ ለጀመረው የተለየ አገልግሎት ወደ ሩቅ ምስራቅ በመዝለቅ «አስማታዊ እና ተአምራዊ የአሰራር ስልቶችን ተምሮ መምጣቱን ሲፅፉ፣ ሌሎች ትዳር መስርቶ ዘሩን ማብዛቱን ይናገራሉ። መገመት እና የተፈጠረን ጥያቄ ለመመለስ መሞከር አእምሮ ላለው ለሰው ልጅ ሁሉ የተሰጠ ቢሆንም አቅሙን ባዛባ ሁኔታ ተጠቅሞ እንደ «Davinchecode» የመሰሉ በልብ ወለድ መልክ የቀረቡ ስራዎችን ያስመጣሉ። በመሰረቱ ይህን የመሰሉ ግንዛቤዎች ለምን ተፈጠሩ? ማለት አይቻልም። ይህ ያለ እና የሚኖርም የሰው ግንዛቤ ነው፤ እነህን ግን አማኞች መለኪያ እስካላቸው ድረስ በዚያ መመዘን አለባቸው።

ይህን መለኪያ - መመዘኛ ልታመንበት አልፈልግም ላለ አማኝ በማያዘልቀው የቅይማት ኑሮው መጓዝ ይኖርበታል፤መድነኒቱን *የጣለ ሊፈወስ አይችልምና። ፊሊፕ ያንሲ፡- ስመ ጥር* ክርስቲያኖች እና የተመሰገኑ ሙሁራን ድንቅ መንፈሳዊ መፅሀፍት ፅፈዋልና እሱ እነርሱን ሁሉ ጭኖ ወደ ኮሎራዶ ቢዘልቅም ግን ቅድሚያ ሰጥቶ ለአስራ አምስት ቀናት ከቅዱስ መጽሐፍ ጋር ከረመ። ከዚህም የተነሳ የሚተርፍን ምክር ይዞ ተመለሰ።

**ዚክ ኑሩ** (ባለቤቱን) ኢዮብ ላይ በደረሰው ግፍ አዝኛለሁ ኢዮብ ባይቀየም እንኳ እኔ እግዚአብሔርን ብቀየምለት ለክፉ ይሰጠኛል ወይ? ብያት የሰጠችኝ ምላሽ «የኢዮብን ሚስት ውሳኔ ለራስህ መወሰን ከቻልክ ብቻ መፍትሄ ታገኛለህ» የሚል ነበር። የኢዮብ ሚስት ያለችው «ከደኸው ሙት» ነው፤ መካድ ማለት እግዚአብሔር የለም ማለት ነው፤ ይህ ሁሉ ችግር የመጣው የሌለውን ተስፋ አድርገህ ከመኖር እሱ የሞተ መሆኑን ማወቅህ ይረዳሀል ማለቷ ነው።

በእግርጥ ኢአማንያን የሚቀየሙት የላቸውም፤ ከዚህም ተነሳ በዚህ ፈተና ውስጥ አይወድቁም፤ ይቸገራሉ፣ ይታመማሉ፣ ይሞታሉ፤ በቃ፤ ከዚህ ውጭ እምነት የላቸውም፤ የኢዮብ ሚስት እንዲህ እንዲያስብ ብቻ ሳይሆን ይህን እንዲያምን ፈለገች። ኢዮብ ግን እግዚአብሔርን በሁለንተናው ተረድቶታል እና «እንደሰነፍ ሴት መናገሯን» ገለፀ።

ዚክ መቀየም የፈለገ ሁሉ «ከአቅሙ በላይ ተንጠራርቶአልና ወደ ራሱ ይመለስ» ማለቷን፤ ልብ ብዬ ራሴን ከክፉ ለመጠበቅ በቅቻለሁ።

በዝምታ አባዜ ውስጥ ፈተና ሊኖር መቻሉን ወይም መቀየም ሊፈጠር እንደሚችል ሌላ አቅጣጫ ያሳየችኝ ፀጋ ፈቃደ ነች «እግዚአብሔርን ለመቀየም የሚያስችል የመሰለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻ ይኖራል ወይ?» የሚል ጥያቄ አድርሼላት ነበር፤ ልብ ያላልኳቸው ጠንካራ ነጥቦችን ያሰፈረ ዝግጅቷን አንብቤ የአሳፍ መዝሙር ላይ ያተኮረውን ስራዋን ለዚህ ጭብጥ ማዳበሪያ አድርጌዋለሁ።

መዝሙረ ዳዊት የአንዱ የዳዊት ቅኔዎች ብቻ በብቸኝነት የተከማቸበት ስራ አይደለም፤ ሌሎችም ቅኔያቸውን አስፍረውበታል፤ ከእነርሱ አንዱ አሳፍ ነው። መዝ 73፡1-28 ቅይማቱንና ፅኑ መፍትሄውን አስተሳስሮ አቅርቧል፤ ሰው እንደመሆኑ ሊገለፁ የተገባቸውን ገለፀ፤ ማለፊያ መልስ ይሆናል ያለውንም በእርግጠኝነት አሰፈረ፡- ከእኔ ማብራሪያ ይልቅ የእሱ ትንታኔ ይበልጣልና እየዘለልኩ ላያይዘው፡-

*እግዚአብሔር ልባቸው ንፁሕ ለሆነ... እንዴት ቸር ነው፤*

*እኔ ግን እግሬ ሊሰናከል አዳልጦኝም ልወድቅ ጥቂት ቀረኝ፤*

*ከፉዎች ሲሳካላቸው አይቼ በዐመፀኞች ቀንቼ ነበር እነርሱ፡-*

*አንደኛ ጣር የለባቸውም፤ ሰውነታቸውም ጤናማና የተደላደለ ነው*

*በሰዎች የሚደርሰው ጣጣ አይደርስባቸውም*

*እንደማንኛውም ሰው መከራ አያገኛቸውም።...*

*«ትዕቢት የአንገት ጌጣቸው ነው ዐመፅንም እንደ ልብስ ተጎናፅፈዋል*

*...ልባቸውም በከንቱ ሐሳብ ተሞልቶ ይፈስሳል*

*...አፋቸውን በሰማይ ላይ ያላቅቃሉ አንደበታቸውም ምድርን ያካልላል...*

*ለመሆኑ እግዚአብሔር እንዴት ያውቃል?*

*በልዑልስ ዘንድ ዕውቀት አለ? ይላሉ»*

*እኔም...ይህን ሁሉ አይቼና አረጋግጬ*

*ለካ ልቤን ንፁህ ያደረግሁት በከንቱ ነው*

*እጄንም በየዋህነት የታጠብኩት በከንቱ ኖሯል...እላለሁ*

*ይህን ነገር ለመረዳት በሞከርሁ ጊዜ አድካሚ ተግባር መስሎ ታየኝ፤*

*...በሰማይ ከአንተ በቀር ማን አለኝ በምድርም ከአንተ ሌላ የምሻው የለኝም...*

*ለእኔ ግን እግዚአብሔርን መጠጊያዬ አድርጌዋለሁ ስለ ሥራህም ሁሉ እናገር ዘንድ»* በማለት አሳፍ ተግዳሮቱን በግልፅነት፣ የልቡን ድካም ሳያሻማ፣ ሁለገቡን በመመርመር ፅኑ መፍትሄውን ያለመጠራጠር ይፅፋል፤ ይቃኛል፤ ለካስ እግዚአብሔር በአማኞች ሕይወት ውስጥ በዝምታ የሚተዋቸው ምንም ነገሮች የለም።

ፊሊፕ ያንሲ እግዚአብሔር በዘ - መፅሐፍቱ - ዘፍጥረት፣ ዘፀዓት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኁልቅ፣





ዘዳግም ውስጥ ራሱን በቅርበት እና በግልፅነት ከሕዝቡ ጋር አገናኝቷል፤ ይህ በመሀላቸው መሆኑ ግን ልክ «እግዚአብሔር በኃጢአተኛ ሕዝብ መካከል ለመኖር እንደተቸገረ ሁሉ እስራኤላውያንም ቅዱሱን አምላክ በመካከላቸው አኑረው ለማስተናገድ ተቸግረዋል (ገፅ 48)

ይህንንም ዘፀዐት እግዚአብሔር ወደ እነርሱ ሊመጣ እንዳለው ሲናገር ሕዝቡ «እነሆ እንሞታለን፣ እንጠፋለንም... ከዚህም የተነሳ ድምፁን አንስማው» ጩኸታቸው ሆኖ ነበር፤ ኢሳይያስም «ከእኛ መካከል ከሚበላ እሳት ጋር ሊኖር የሚችል ማን ነው?» (ኢሳ 33) ብሎ ጠይቋል። ይህ የሚሰጠን ፍንጭ እግዚአብሔር የተደበቀ ወይም የራቀ መምሰሉ ምህረቱና ፀጋው ከመሆኑ የተነሳ ነው ማለት ነው። የተደበቀ በመሰለ ሁኔታ ባይገናኘን ኑሮ መጥፋታችን ለካስ ቅፅበታዊ ነው።

## ኪዎ ቶልስቶይ

ፊሊፕ ያንሲ፡- «ሪቻርድ በፍትህ የሚሰራ፣ በግልፅ የሚናገርና ራሱን ገሃድ የሚያወጣ አምላክ ቢኖር ማንም ሰው እንደ ታማኝ ውሻ እንደሚከተለው ያምናል» ይህ ግን አዋጪ አለመሆኑን በሌዎ ቶልስቶይ ታይቷል፤ ቶሎስቶይ «ልጅ ሳለ በዘጠኝ ዓመቱ እግዚአብሔር ለመብረር እንደሚያስችለው በማመን ከሶስተኛ ፎቅ መስኮት ራሱን ጣለ» ግን ወደቀ እንጂ አልበረረም፤ በዚህም ትንሹ ቶልስቶይ እግዚአብሔርን ተቀየመ፤ ይህ ቅይማቱ ላይ ግን የሳቀው ከአደገ በኋላ ነበር፤ በበሰለ ጊዜ ራሱን በተረዳ ጊዜ የጅልነት ተግባር መፈፀሙን በማመን በራሱ ላይ ተደንቋል።

ከሪቻርጅ መነሻን ያገኘው ፊሊፕ «ጌታ ሆይ በዚህ ሀይቅ ላይ እንድራመድ እርዳኝ፣ ያንን ልጅ እንድደበድበው እርዳኝ፣ ሳላጠና ጎበዝ ተማሪ አድርገኝ...» ብለው ይህ ሁሉ ቢሳካላቸው እነርሱ በድል ሕይወት እንደሚመላለሱ ይገምታሉ፤ ይህ ግን እግዚአብሔርን ለማመስገንም ሆነ ለመከተል አቅም አይኖረውም::

እግዚአብሔር አማኞች በድንቅ ድርጊቶች እና ተአምራቶች ላይ ተደግፈው ይከተሉት ዘንድ አይፈልግም፤ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ሰዎች የጠየቁትን ሁሉ እየመለሰ ለእነርሱ ደስታ አይኖርም። ይልቁኑ ሰዎች እንደተመኙት ቢሆን እና ይህም በተግባር ቢገለፅ ማንም በሕይወት ይኖር ዘንድ አይችልም ነበር።

በአንድ ወቅት አዛውንቱ ቄስ «ክርስቶስ ከድንግል መወለዱን እንዲሁም ከሞት መነሳቱን የሚገልፁ የወንጌል ክፍሎች ቃል በቃል መተርጎም የለበትም» በማለታቸው መላው የቀዬአቸው ሕዝበ ክርስቲያን ለተቃውሞ ወጥቶ ነበር። በዚሁ ጊዜ በ13ኛው ክፍለ ዘመን ተሰርቶ የታሪክ ማስታወሻ የነበረው የካቴድራል ጣሪያ በመብረቅ ተመታ፣ በዚያው ቀን በሰሜን አውሮፓ የሚገኘው

ካቴድራል በእሳት ጋየ... በዚህ ጊዜ ነበር እግዚአብሔር ፈጣን መልስ ሰጠ፤ «የእጁን በእጁ፤በደጁ» አገኘ ተባለ ይህንንም ታዋቂው ታይም መፅሔትም ዘገበው።

ይህ ከነውን ለሪቻርድ እና እሱን ለመሰሉ አማኞች ይጠቅም ይሆናል፤ ግን እግዚአብሔር በዓለም ዙሪያ ለተፈፀሙ ነውሮች ሁሉ ፈጣን ምላሽን እንደኤልያስ ዘመን ቢሰጥ እውን ማን በህይወት ይኖር ነበር? ከዚህ ይልቅ ግን እግዚአብሔር አጠቃላይ ጥበቃውን በማድረግ ይተጋል።

ለሪቻርድ መሰረታዊ ጥያቄዎች ፊሊፕ ያንሲ መልስ የሰጠበት The disappointement with God «ቅይማት» መፅሐፍ ለሁለት የተከፈለ ነው፤ የመጀመሪያው ክፍል እስከ ገፅ 118 ዘልቋል፤ የዚህን አዘላለቅ ከራሳችን ጉዳይ ጋር እያያዝኩ ናሙናዊ ገለፃ ለማድረግ ሞክሪያለሁ፤ የቀሩ ብዙ ማብራሪያዎች አሉ፤ ያሻው ቢያጠናው ተመራጭ ነው፤ የመጽሐፉ ሁለተኛው ክፍል «በድቅድቅ መመልከት» በማለት ጀምሮ ተግባራዊ በሆኑ የመፍትሔ ጭብጦች ላይ አትኩሯል፤ እኔም መልከቱን አሳጥሬ በዚያውም አጠቃልላለሁ፡

## ፍልስፍና ፩

**«ፍልስፍና ፩»** በዩንቨርስቲ በመማር ላይ ባለ በአንድ ተማሪ የተፃፈ ሥራ ነው፤ ተማሪው ብሩህ ዓለምነህ ይባላል። ህትመቱ በ2003ዓ.ም. ለአማርኛ ቋንቋ ተጠቃሚዎች እንዲነበብ ሆኖ ቀርቧል።

ኢትዮጵያዊ ፀሐፊ ገፅ አንድ፡- በማለት የጫጫረው «አንድ እምነት ይዘን ተደላድለን በመኖር ላይ ካለን ያንን በመናድ ራሳችሁን ፈትሹ» ይላል፤-

> *«...እናንተ የምታውቁትን ነገር እኔ በተለያየ አቅጣጫ እያሳየኋችሁ ግራ እጋባችኋለሁ፤ ደግሞም አስገርማችኋለሁ። እውነት ነው ብላችሁ የያዛችሁትን ነገር በሌላ አቅጣጫ ሌላ ሀሳብ አመጣና አደረምስባችኋለሁ፤ ይሄ ነው ትክክል ብላችሁ ያደላደላችሁትን ነገር ባዶ መሆኑን ስታዩ ትናወጣላችሁ፤ ያን ጊዜ መጠጊያ አጥታችሁ መሀል ላይ ትዋልላላችሁ፤ ስሜቶቻችሁና የፅኑ እምነቶቻችሁ መነቃነቅ ሲጀምሩ ያን ጊዜ ትክክል ማሰብ ትጀምራላችሁ፤ ይህ ጥርጣሬና ምርመራ ነው ይበልጥ ወደ እውነት የሚወስዳችሁና ከቀኖና እስር ቤት ነፃ የሚያወጣችሁ፤ የፍልስፍና ዓላማም ሰዎችን ከእንደዚህ ዓይነት ነፃነት ላይ ማድረስ ነው...»* (ገፅ 10-11) በማለት ይጀምራል።

ይህ ገለፃ በልሙጡ ሲመለከቱት ደስ አያሰኝም፤ ያስበረግጋል፤ ሊያስቆጣም ይችላል። ይሁንና አማኞች ሕይወታቸውንና አኗኗራቸው በምድራዊ እይታ እና በሰዋዊ ግንዛቤ ላይ ብቻ አትኩሮ የፀና ሳይሆን





በተጨማሪም ሕይወት ከእግዚአብሔር እቅዱና ተግባር ጋር አያይዘው ስለሚያምኑ ስለሚዘጋጁም፤ ለምንም ነገር አይሰጉም፤ እርሱ ፍልስፍና የራሱን ዘርፍ በስርዓተ ትምህርት ውስጥ ወግ ባለው መልኩ ከመካተቱ ቀድሞ የነበረ መሆኑን በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ በተገለፁ ገፀ ባህሪያት ተዋውቀናል።

የእግዚአብሔር ቃል እምነታቸው የተደረመሰባቸውን፣ የያዙትን የለቀቁ በብዙ ተግዳሮት ውስጥ በማለፍ አቋማቸውን ስለአሻሻሉ ወይም ስለቀየሩ ሰዎች ነግሮናል። እነርሱም ከፊታችን ቀድመው መሄድ የዛሬን ኑሮአችንን አቅለን እንድንረዳው አግዞናል።

ብሩህ አለምነህ ግን በ2003 የምህረትዓመት ላይ ተገኝቶ ስለተማረውና ስለመሰለው የሚናድ ነገር ሊኖር እንደሚችል ይገልፃል፤ እርግጥ ነው ሁሉን በዝምታ፣ ሁሉን በልብ ይዘው እምነታቸውን ሳይገልጡትና ሳይጠይቁት የኖሩ አማኞች ፈጥነው ሊቀየሙ፣ በቶሎም እምነታቸውን ሊንቁ ይችሉ ይሆናል።

እውነቱ ግን በእግዚአብሔር ላይ የተነሱ ጥያቄዎች በሙሉ በአግባቡ በቀዳሚነት በቅዱሳን መጽሐፍቱ እገዛ፤ በሰው የማንነት ገደብ እና በእግዚአብሔር ልኬየለሽነት ላይ በመመስረት የክፍል ሁለትን የፊሊፕ ያንሲን አመላካች ጭብጦችን እንያዝ፡-

ፊሊፕ ሚዛናዊ ገለጣ ያሳያል፤ በኢዮብ እንደ ዴቪድ ፓውሰን ወይ በኢትዮጵያ ኤስአይ. ኤም. (SIM) እንደተዘጋጀው የብሉይኪዳን ቅኝት ገለፃ «ኢዮብ የመከራ መገለጫ፣ አፅናኝ ተብዬዎችም የመከራ ቁስሎች» አድርገን እንዳናስብ ይመክራል። ይልቅስ በኢዮብ ሕይወትና በመላው መፅሐፉ «እምነት» ምንድን ነው? እንዴትስ ይገለፃል?ን ብናስብ እሱንም ብናምን የተሻለ ነው» ይላል በገለፃውም፡-

> «...ኢዮብ ምን አጠፋ? ምንም። እርሱ ከሁሉም የተሻለ ሰው ነበረ፤ ራሱ እግዚአብሔር *«ፍፁም ቅን እግዚአብሔርንም የሚፈራ ከክፋትም የራቀ»* ብሎ ጠርቶታል፤ እንግዲህ ኢዮብ ለምንድነው መከራ የሚጠግበው? ሊቀጣው አይደለምን? ምላሹ በሚገርም ሁኔታ አልነበረም። እርሱ የተመረጠው በሰማያዊ አካላት ታላቅ ውድድር ውስጥ ዋነኛ ተዋናይ እንዲሆን ነው። (ገፅ 127)

ሰይጣን ኢዮብ ከንቱ ሰው እንደሆነና ለእግዚአብሔርም የታመነ የመሰለው «በዙሪያው ያለው ሁሉ ስለታጠረለት እንደሆነ መናገሩ የታሪኩ መነሻ ነበር፤ ሰይጣን እግዚአብሔር በብቻው ሊወደድ የማይገባው ሆኖ ሳለ እንደ ኢዮብ ላሉት ሰዎች «ጉቦ» በመስጠት ተከታይ እንደሚያደርጋቸው በመግለፅ ኢዮብ ጊዜው ትንሽ ቢለወጥ (ቢከፋ) እግዚአብሔርን ከመከተል ይመለሳል በማለት አወጀ።

እግዚአብሔር አማኞችን በኢዮብ መነሻነትና መገለጫነት እግዚአብሔርን «አለኝ» ከማለት ባሻገር እንዲረዱት እንዲሁም እንዲያምኑት ይፈልጋል። ይህም ተግባራዊ በሆነ አኗኗር ከእምነት የተነሳ ሲተገብሩት ሁሉም ጥያቄዎች በራሳቸው መልሶች መሆናቸውን ያስተምራል፤ ያሳውቃል፤ ይህ መሆን መቻል አለመቻሉን ያረጋግጥ ዘንድ ፈቃድ ለሴጣን ተሰጥቶት ስለ ነበር ተከታታይና ዘላቂ የመከራ ጎርፍ አዘነበ።

በሁሉም ውስጥ ኢዮብ እንደ እውነተኛ ሰው መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለውስጡ አንብቧል፤ ለውጮቹም አሰደምጧል፤ አፅናኞቹም ሙግታቸውን ራስነታቸውን መነሻ፣ እሱን ደግሞ ማስረጃ በማድረግ ገልፀዋል፤ እግዚአብሔር የውስጣችንን እንድንተነፍስ መነሻን ሁል ጊዜ መስጠቱ ቸርነቱ ነው፤ ፀጋው ነው፤ በዚህ እሱ ትዝብት ውስጥ አይወድቅም፤ እኛው ራሳችን በጊዜ ውስጥ በትዝብቱ ውስጥ እንከተታለን።

እስቲ እንደመካሪ ሆኖ ኤሊሁ የተናገረውን እናንብብ ስንጨርስም ንግግሩ እና አስተሳሰቡ ምን ያህል የተደነቃቀፈ እና የተሳሳተ መሆኑን ልብ እንበል፤ እየበሰበሰ እየጠፋ ላለው ኢዮብ እንዲህ ብሎት ነበር፡-

> *«...ኃጢአት ብትሰራ ምን ትጎዳዋለህ?*
>
> *መተላለፍህስ ቢበዛ ምን ታደርገዋለህ?*
>
> *ፃድቅስ ብትሆን ምን ትሰጠዋለህ?*
>
> *ወይስ ከእጅህ ምንን ይቀበላል?*
>
> *እንደ አንተ ያለውን ሰው ክፋትህ ይጎዳዋል። ለሰውስ ልጅ ፅድቅህ ይጠቅመዋል»* ይላል። እንዲህ የሚቀናጣበት የኢዮብ ማንነት ኋላ ላይ ሕዝቅኤል በትንቢቱ ሲገልፀው ኢዮብ፣ ዳንኤልንና ኖህን በማንሳት ታማኝነታቸውን፣ በአደባባይ ይገልፃል።

በመሰረቱ ብዙዎች መቀያየምን የሚጀምሩት በትዳር አጋር ሞት፣ በልጅ ስቃይ፣ በአሳዛኝ አደጋ፣ ከሥራ ገበታ በመነሳት፣ በጋብቻ መፍረስ፣ በፍቃደ ሥጋ ችግር...ወዘተ ሰው ይቀየማል፤ ...ዳሩ ግን ኢዮብ ሲጠና ትግሉ የሚካሄደው በውስጥ ነው፤ በሙግቱም እውን እግዚአብሔርን በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆነን እናምነዋለን? እምነታችን ልዑል እግዚአብሔርንና አጠቃላይ ስራውን እንደንመለከት ያግዘናል ወይ? በማለት ይጠይቀናል። (ገፅ 135) እንግዲያስ...ለምን እግዚአብሔር ጋዜጣዊ መግለጫ አይሰጥም።(ገፅ 149)





*ሪቻርድ የፊሊፕ ያንሲን ማብራሪያ በመተው አንተ ከምትናገረኝ እና ነገር ከምታበዛ ለምንስ እግዚአብሔር ስለሚፈፅመው ነገር ሁሉ መግለጫ ለምን አይሰጥም ይላሉ።*

እርግጡን እንስማ እግዚአብሔር ለሁላችን መከራ ዝርዝር መልስ አይሰጥም። ኤሊሁ ለተሳለቀው መሳለቅ እንኳ «እንግዲህ እየኛ አላለውም፤ ኢዮብም ላጉረመረመበት «እንካ መልሱን» አላለውም ይልቅስ አስጨረሰው፤ አስጨረሳቸውም።

ጭራሽ ኢዮብ የጠየቀውን በርካታ «መሰረታዊ» ጥያቄ ከግምት ሳያስገባ፣ ሳይመልስለት ጊዜው ሲደርስ እርሱ ራሱ ይጠይቀው ገባ፤ በዚህም ወደ ልቡ፣ ወደ ልኩ ወደ ራሱነቱ ተመለሰ፤ መመለስ የአቋም ለውጥ ማድረግ ነው፤ ንስሀ ነው።

ፊሊፕ፡-ፍሬድሪክ በችግር ከሰበከው እና ካነሳው ምሳሌያዊ ታሪክ ጋር በማገጣጠም፤ አባታችንን እንዳንገድል ይመክረናል።

> *የ12 ዓመት ዕድሜ ያለው ልጅ አባቱ ቁጭ ብሎ ስራውን እየሰራለት ባለበት የአባቱን ጠመንጃ በመውሰድ ተኩሶ ይገድለዋል፤ በፖሊስ ታስሮ ሲጠየቅም «ከአቅሜ በላይ እየጠየቀኝ ያበሳጨኛል፤ ከዚህ በኋላ እየጠየቀ እንዳያስቸግረኝ ፈልጌ ነው» የልጁ ምላሹ ነበር። ይኸው ልጁ ግን በእስር ቤት እያለ «አባቴን እፈልገዋለሁ» እያለ ያለማቋረጥ ይጮህ ነበር።* (ገፅ 209)

ሰዎች ሁሉ እንደዚህ ልጅ እንዳይሆኑ ይመከራሉ፤ ዛሬ ማህበረሰቡ እስር ቤት እንዳለ ልጅ ነው፤ አባታችንን ገድለነዋል። ለእግዚአብሔር ስፍራ ሳይሰጡ መኖር ምንም ትርፍ አያመጣም። እንግዲያስ ትርፍን ወደሚያመጣ ማጠቃለያ እንምጣ።

## ቀዳማይ ማጠቃለያ

**ሰው** ሰውን መቀየም ይችላል፤ በውድቀት ውስጥ ያለ ሰው፣ ሀጢአትንና ሀጢአተኝነትን የያዘ የሰው ልጅ፣ በእርግጠኝነት እርስ በርሱ ይቀያየማል፤ በአማኞች ሕይወት ውስጥም ይህ ባይፈቀድም ሊገኝ ይችላል፤ በመነጋገር፣ በመቀባበል፤ ይቅርታ በመጠያየቅ፤ ይልቅኑ የክርስቶስን የፍቅር ልብ በመያዝ ከማንም ጋር በሰላምና በፍቅር መኖር የፈተናው ማለፊያ ውጤት ይሆናል።

ይህ መቀየም ግን ወደ እግዚአብሔር ደርሶ እርሱን «አንድዬን» መቀየም የሚቻል የሚመስል አካሄድ ይኖራል። ይህ አካሄድ በበርካቶች የቅዱሳን አኗኗር ውስጥ ታይቷል ግን አዋጪ መሆን አልቻለም፤ ይልቅኑ፡-

እግዚአብሔር አድሎአዊ በመሰለበት፣ ፀሎትን የማይመልስ በመሰለበት ወይም ራሱን የደበቀ በመሰለበት ከስተት ሁሉ ላይ አማኞች ልብ ሊሉት የሚገቡ ጭብጦች አለ።

**አንድ፡-** ሰው በሀጢአት ከመውደቁ በፊት የነበሩትን ድንቅ ዕድሎች በገዛ ምርጫው ያጣ ፍጡር ነው፤ ከዚህም የተነሳ በእግዚአብሔር ላይ መቆጣት ወይም የመቀየም መብት የለውም።

**ሁለት፡-** ሀጢአት ብክለት ነው፤ መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን በሙልዐት ለመረዳት አቅም አይሰጥም፤ ይህ እግዚአብሔርን ብቻ ሳይሆን ራስነትንም ጭምር ነው፤ ከዚህም የተነሳ አማኞች ውስን አቅም ያላቸው መሆናቸውን ልብ ሊሉት ይገባል።

**ሦስት፡-** እግዚአብሔር ፈጣሪ፣ ሰዎችም የእርሱ ፍጡራን መሆናቸውን ማወቅ፣ ማስተዋል አለባቸው ይህን መገንዘብ የቅይማት አቅጣጫን ሚዛናዊ ያደርጋል።

**አራት፡-** እግዚአብሔርን የመውደድ የመገለጫ ድንበርን «ነገርን ሁሉ ለበጎ እግዚአብሔር ገጣጥሞ በእያንዳንዱ ሰው የሚሰራ መሆኑን ማመን ነው።

**አምስት፡-** ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳኩቶ መከፈትንና ለምኖ ማግኘትን በማቴዎስ ወንጌል 7፡12 ላይ ቋጭቶታል፤ እሱም ለራሳችን ሊደረግልን የሚገባውን ያንኑ ለሌላው በማድረግ የፀሎት መልስን በሰው ውስጥ ማኖሩን አለመዘንጋት ነው።

እንግዲያስ ኢትዮጵያውያን በተናጥልም ሆነ በጋራ በርካታ ተግዳሮቶችን ዕለት ዕለት የምንፋለም ሕዝቦች ነን፤ አማኞች የዚህ ሕዝብ አካል ናቸው፤ ከሕዝቡ ጋር በረከቶቹን ይጋራሉ፤ ከሕዝቡ ጋር ችግሮችንም ይጋፈጣሉ።

*አማኞች እግዚአብሔር በሰጣቸው ባልተቋጨ ዘመናቸውም ውስጥ ሐላፊነት አለባቸው፤ ተጠያቂም ሆነው ይቀርቡበታል፤ በሚኖሩት ኑሮ ጨለማ የመሰለ ችግር አይገጥማቸውም የሚል ተስፋ፣ ቃልም የላቸውም፤ ያላቸው ቃል በመከራ ዓለም ውስጥ ከመከራው ጋር አብረው ሊኖሩ ነው፤ በዚህ ውስጥ አብሮአቸው ያለውን ጌታ በመታመን ኑሮአቸውን ይመዝኑት ዘንድ የእግዚአብሔ ፈቃድ ነው።*

ሼክስፒር «ችግርን (መከራን) በጥቅም ላይ እንደማዋል ጣፋጭ ነገር የለም» ይላል፤ ይህን ግን የተረዳው በኢዮብ አኗኗርና ሕይወት ነው፤ እንግዲያስ አማኞች ተግዳሮቶችን ሁሉ ከእግዚብሔር ዕቅድና ሀሳብ ጋር በማያያዝ ከውስጡ የሚገኘውን መልካም መዓዛና ጣፋጭ ጣዕም ለመቋደስ ይበርቱ፤ እንበርታም።





## ተከታይ ማጠቃለያ

የማጠቃለያው ማጠቃለያን ነው ተከታይ ማጠቃለያ ብዬ የጠራሁት፤ በ2003 እ.ኢ.አ ጳውሎስ ፈቃደ When Heaven is silent የሚለውን የሮናልድ ዶን መፅሐፍ ተርጉሞ ለንባብ አቅርቧል፤ የመፅሐፉንም ስም «ሰማዩ ዝም ሲል» በማለት ገላጭ ስያሜን ሰጥቶታል፤ ይህ መፅሐፍ «በሕይወት ተግዳሮቶች ውስጥ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያቆመን» የሚል የማጠቃለያ አብይ «አጤሪራ» ተሰጥቶታል።

ይህ መፅሐፍ ቅይማት ሊገጥማቸው ወይም በገጠማቸው የመጽሐፍ ቅዱስ አብይ ገፀ ባህርያት ላይ አትኩሮአል፤ ያዕቆብንም፤ ዮሴፍንም ሌሎችንም ሁሉ ኢዮብንም ጨምሮ እንዴት ተግዳሮትን ተቋቁመው እንደዘለቁ ያብራራል።

ማብራሪያውን ሮናልድ ዶን በሕይወት ከገጠሙት ተፈታታኝ ጉዳዮች ጋር አጠማምሮ ስለፃፈልን ተጠቅመናል።

ደራሲው 1973 «እንግዳ አገልጋዮች» በማለት ነበር ምዕራፍ አንድን አንድ ብሎ የጠራው፡- በዚያም የውስጥ ሰውን ሁነኛ የግንዛቤ ችግርን ያስተዋውቃል፤ በራሱ ላይ የሆነውን፤ እርሱም በሌላው ላይ ያደረገውን ያስተዋውቅና ቶሎ ቶሎ ወደ መፅሐፉ መዳረሻ ድረስ ያለትዕግስት እንድናነበው ግድ ይለናል።

**ሮናልድ ዶን፡-** በአንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለማቋረጥ ለሰባት አመት አገልግሏል፤ እያገለገለም ነው፤ ታዲያ ምዕመኑ ሁሌም እሁድ የሚያደምጡት ሙሉ ልብሱን ለብሶ በከረቫቱ ቂቅ ብሎ ነው።

ዶን አንድ ቅዳሜ እኩለ ለሊት ላይ ቁምጣውን እንዳደረገ፣ ቡቴውን ሳያወልቅ ለእሁድ ቁርስ የሚያስፈልግ አስቤዛ ለመግዛት ባለቤቱ ወደማይዘጋው ሱፐር ማርኬት (ሞል)ላከችው። እሱም ታዞ ሸማመተ፤ ከፍያውንም ፈፅሞ፤ ሊወጣ ሲል የቤተክርስቲያኑ አባል በመደናገጥ ትኩር ብላ አየችው? እሱም ተገርሞ እያለ «ዶን ከሙሉ ልብስና ከራቫት ውጭ አላውቅህም ነበር» በማለት ተገረመች።

ዶን ወደ ቤቱ እየተመለሰ አንድን ቁም ነገር ልብ አለ «ለካስ ራስን የመደበቂያ ምርጥ ዘዴ የደንብ ልብስ መልበስ ነው ምክንያቱም ሰዎች የደንብ ልብሱን እንጂ ለባሹን ሰው አያዩም» አለ በልቡ።

ለንደን ላይም ቴክሳስ ሳለ የሚያመላልስለት ፖስተኛ ያለ ደንብ ልብስ መጥቶ ሰላም ሲለው አለማወቁን አረጋግጦ «አትፍረዱ ይፈረድባችኋልም» ገባው።

ከዚህም በመነሳት የሕይወት ተግዳሮትን ተቋቁሞ ለማለፍ እያንዳንዱ አማኝ በዚያው ያለውንና በራሱ እና በሌላው የሚፈፀመውን ድርጊት በአግባቡ መመልከት፣ ውስጡን ውጩን ማወቅ ይጠበቅበታል፤ የሰው የማንነቱ መገለጫ በዩኒፎርሙ እና በፊት ገፅታው አይለካም ውስጡን ልብ በማለት ለዚህም በመስራት መትጋት ተገቢ ነው።

ተያያዡን የተግዳሮት ወይም የቅይማት መቋቋሚያን ደግሞ እንደሚከተለው አስነብባለሁ፤ ይህ ደግሞ ሮናልድ ዶን ከተሞክሮ ያገኘው አይዘንጌ የድል መንሻው ነው።

ሀኪሙ የመረመረውን ሰው እናዞ በመጨረሻ ላይ ማደረግ ያለበትን ሁሉ እየዘረዘረለት ሳለ ታማሚው እሱን አቋርጦ «ኪኒን ነገር ልትሰጠን አትችልም?» ነበር አለው። ሐኪሙ ለጫወታ ለቀልድ የጠየቀው መስሎት ቀና ብሎ ሲያየው ያንኑ ጥያቄውን ደገመለት።

በሽተኛው ለአስር አመታት ሳያቋርጥ አገልግሏል፤ ተንከራቷል፤ አንድን ጨርሶ ወደ ሌላው እየተሸጋገረ ቀን ከሌት ሰርቷል፤ በዚህ ኑሮው የምግብ ግዜው ን አክብሮ አያውቅም፡- «የፋስት ፉድ» ደንበኛ ነው፣ የየለቱ ውጣ ውረድ በሽታ ላይ ጥሎታል፤ ከብደቱ በ13 ኪሎ ቀንሶ ጨጓራው ከፉኛ ተጎድቷል፤ አጠቃላይ ገፅታው ተበላሽቱዋል። ለዚህም ነበር ወደ ሆስፒታል የሄደውበሄደበት ዶክተሩ እውነተኛ መፍትሔን አቀበለው «...አሁኑኑ መጀመር ያለብህን ነገሮች እነግርሀለሁ አንደኛ በቀን አምስት ኪሎ ሜትር ገደማ ያህል በሳምንት ለአራት ቀናት የእግር ጉዞ ማድረግ አለብህ፣ ይህንንም በአርባ አምስት ደቂቃ ውስጥ በየቀኑ ታደርጋለህ፤ ሁለተኛ፡- ቢያንስ በቀን ሁለቴ ሥርዓት ያለው የተመጣጠነ ምግብ መመገብ አለብህ፤ ሶስተኛ በየምሽቱ ሰባት ወይም ስምንት ሰዓት ያህል የእንቅልፍ ጊዜ ሊኖርህ ይገባል፤ ይህ ደግሞ ከእኩለ ሌሊት በፊት መሆን አለበት፤» እያለው ሳለ ነበር፤- አራተኛውን ላለመስማት «ኪኒን ወይም ሌላ ነገር ልትሰጠኝ አትችልም» ያለው።

ታማሚው የሐኪሙን ትዕዛዙ ለመፈፀም ከወዲሁ አልፈለገም፤ የፈለገው ቀላል መፍትሔን ብቻ ነው፤ ኪኒን ውጦ የቀደመውን ስራ ያለለውጥ መቀጠል ። ከዚህም የተነሳ ሰውየው «ጤነኛ ለመሆን ሥራ ይበዛበታል ግና ጤናው እንዲመለስ ደግሞ ይፈልጋል እንደ ዶን አነጋገር (ገፅ 17) ሰውየው የኑሮ ዘይቤውን ሳይለውጥ ጤና ልሁን ባይ ነው።

ይህ ግን አያዋጣም፤ አማኞች ሰውንም እግዚአብሔርንም ተቀይመው በዚያው መቀጠልን ማዝለቅ የዚህ ዝግጅት ዓላማና ፍላጎት አይደለም።





እንደ ዶን አገላለፅ «ሕመምተኛው ፍላጎቱንና ስሜቱን ብቻ እየተከተለ እንዲኖርና እነዚህም ከሚያስከትሉበት የማይመች ሁኔታዎች በሚታደጉት ኪኒኖች ላይ ተማምኖ መቀጠል ይመኛል፤ ለዚህም የሕይወት አቅጣጫ ለውጡን አላስፈላጊ የሚያደርግለትን ኪኒን ብቻ ይፈልጋል» በማለት ፅፏል።

እንግዲያስ መንፈሳዊነት ቀላልና ፈጣን መፍትሄን የመፈለግ ኑሮ አይደለም፤ አቋራጭ መንገድ የትም አያደርስም፤ ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔርን በቅጡ እንወቀው ራሳችንን እንፈትሽ፤ አቅማችንን እናረጋግጥ «በማረፍ እና በመመለስ» የመዳንንም አቅም እንገንዘብ።

**«ሰማዩ ዝም ሲል»** ለተገዳዳሪ ፈተናዎች ሁሉ፡- ጥሩ ሀሳብ ሁል ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ መለኪያ አለመሆኑን፣ እግዚአብሔር የሚመዝነን በእጃችን ከንውን ሳይሆን በልባችን የመነሻ ምኞት መሆኑን፣ እግዚአብሔር «እንቢ» ሲለን በረከታችንን ሊነጥቀን ሳይሆን ወደ ተሻለው ሊመራን መሆኑን መረዳት እና እጅግ ከከፋ ነገር ውስጥ እግዚአብሔር ምርጥን ነገር ማውጣት እንደሚችል ማስተዋል እና በቃሉ ላይ የተመሰረተን ፀሎት ማድረስ መድህኒት ሆኖ ያፀናናል፤ ያኖረናል፤ ፍሬያማ የሆነውን ሕይወት በመኖር እንድንዘልቅም ያግዛል፤ ይህ ደግሞ ራሳችንንም እድነን በዚሁ መከራ ውስጥ ያሉትን ነጥቀን ለማውጣት አቅምን ይሰጠናል። አሜን!

## «ወንድ በኢትዮጵያ አውድ ውስጥ»

### መግቢያ

ይህ ዝግጅት አቅምን ለማሳደግ፣ እርስ በርስ ለመግባባት፣ ኃላፊነትን ከተጠያቂነት ጋር ለማስተሳሰር እንዲሁም በዋነኝነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ በአግባቡ ለመፈፀም እና ቅድሚያ ለመስጠት የወሰነ ነው።

አወያይ ትምህርቱ «በወንዶች» ላይ ያነጣጥራል፤ ወንድ እና ሴት በፆታዊ አደላደል እኩል እኩል ድርሻ ያላቸው ፍጡራን ናቸው፤ ወንድና ሴት በመኖራቸው፣ ስለፍቅር መነጋገርን፣ በፍቅር መኖርን፣ ቤተሰብን መመስረትን፣ ልጆች ማሳደግን፣ አባት እናት፣ አያት፣ ቅድመ አያት... መሆንን የሚያዘልቅ የትውልድ ሰንሰለትን አመላካች እና አስገኚ ነው። ይህ እንዲህ ባይደረጅ ዛሬ የምንነጋገርበትን ርዕሰ ጉዳይ ባላገኘን «ወንድ በኢትዮጵያ አውድ ውስጥ» በሚል ርዕሰ መምከር ደግሞ አንድም፡- ስለ ኢትዮጵያ እና ኢትጵያዊነት እንድናይ ግድ ይለናል። አንድም ስለ ክርስቲያንነት የመነሻ ምንነት መነጋገርንና መተማመንን ያመላክታል። አንድም፡- የወንድ የማንነቱ መገለጫዎችንና ያልተገቡት የግሌ ያላቸው ምንነቶችን የሚያይበትን ዕድል ይህ ዝግጅት ይፈጥራል።

### የምልከታው ገደብ

ዝግጅት ሁሉ ካልተገደበ አጓጓዙ በጊዜ ብክነት፣ በተመሰቃቀለ እይታ፣ በተቃየጠ አስተምህሮ ላይ ሊጥል ይችላል፤ ከዚህም የተነሳ በውስን ጉዳዮች ላይ ብቻ ማተኮር ግድ ነው፤ እኔም በቢጋሬ ላይ በዘረዘርኩት ቀዳሚ ጉዳዮች ላይ ብቻ አተኩሬ በፍፃሜው በየቤቱ ሁሉ ይመከርበት ዘንድ አሳስባለሁ።





እንግዲህ የምልከታው ገደብ፣ ከዕውቀት ሙሉዕነት መመጠን፣ ከስነሰብ ጥናት የአቅም ማነስ፣ እንዲሁም ከታሪክ ትንታኔ መገታት የተነሳ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ አይገባም። ይህ ማለት ግን ግልፅ፣ ምጥን እና ተገቢ እውነት አይዘከርም ማለት አይደለም፤ ይልቁኑ «ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም...» በማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረበትን መሰረታዊ ስልት እከተላለሁ፤ ያንንም አብረን እንከታተላለን።

### ሀ. መግቢያ

### ለ. የምልከታው ገደብ

1. ወንድ በ66ቱ ቅዱሳን መጽሐፍት ውስጥ፣
2. ወንድ በአማርኛ መዝገበ ቃላት ውስጥ፣
3. ወንድ በስነ ቃል ዘርፎቻችን ውስጥ፣
4. ወንድ በአሸቱ ድባብ የ«ተባእታይ አገዛዝ በኢትዮጵያ» መፅሀፍ ውስጥ፣
5. በአዘጋጁና በሌሎች ኑሮ የተገለጡ ምንነቶች፣
6. ክርስቲያን ወንድ በገዛ ዘመኑ ሊያስብበት የሚገባ ጭብጦች፣
7. ማጠቃለያ።

## ምዕራፍ አንድ

## ወንድ በ66ቱ ቅዱሳት መፅሐፍት ውስጥ

ይህን ምዕራፍ ማስቀደም የምገደደው መጽሐፉ በመንፈስ ቅዱስ ደራሲነት በመፃፉ እና ቅዱሳን ሰዎች በጥንቃቄ በመፃፍ ለእኛ ያስተላለፉት ሰነድ ስለሆነ ነው፤ ይህ መፅሐፍ መድብለ ብዙ ሆኖ ግን ያለመጋጨት፣ ያለመሳከር፣ በግልፅ የተፃፈ፣ እንዲሁም ማንም ዳግሞ በመወለድ አብሮሀተ እግዚአብሔር ላገኘ ሁሉ የሚገልፀው እውነት ቅድሚያ ተሰጦት መለኪያ፣ መመሪያ መሆን መቻሉ ነው በቀዲሚት ያስጠራው።

ይህንንም ስል ማንም በጥራዝ ነጠቅነት «ይህማ ይህ ነው» ብሎ ሊዘነጥለው በወደደው

አካሄድ ሳይሆን የታቃስ ስልትን በአግባቡ በመከታተል ሂደት ውስጥ በማለፍ መጓዝ ነው መነሻውም መደምደሚያውም።

**ታ- ታሪካዊ ዱራ፡-** ሁሉንም ወደ መነሻቸው አውድ በመጓጓዝ የነበራቸውን እሴት ማጥናት፣ **ቃ- ቃኩን** በቃሉ በመፍታት ልከኛውን መልዕክት ለመረዳት መጣር፣ **ስ- ስርዓተ ቋንቋን** በተገቢው አቅም በማደርጀት ቋንቋ በመደበኛነቱ የሚያስተላልፈውን መገንዘብ፡- እኒህን ሶስቱን በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት በመታገዝ፣ በፍፁም ፍቅርና ትህትና የተደረሰበትን መውሰዱ ብቻ ሁሉንም ይጠቅማል፤ ማለያየቱ ሳይሆን በአንድ ጅረት በመፍሰስ የተግባር ሰው ያደርጋልና ይህን ቅድሚያ ሰጥቻለሁ።

ከዚህም የተነሳ «ወንድ» ላይ ተመልካች ሊሆኑ የተገባቸውን ጭብጦች እንናበብ፡- በመሰረቱ ዘፍጥረት ብዙ ታሪኮችን በውስጡ የያዘ መፅሐፍ ነው፤

በመልዕክቱ የጋራ ሐላፊነትን፣ የጋራ ማንነትን፣ የጋራ ተጠያቂነትን በ6ኛው ቀን ለፈጠረውና ላበጀው ሰጠው እሱንም «ሰው» ብሎ ጠራው።

በማቴ 4፡4 ኢየሱስ ክርስቶስ «ሰው የሚኖረው እግዚአብሔር በሚናገረው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይደለም» አለ፤ በዚህም «ወንድ ሴት» ሁለቱንም በእኩል መጠሪያ «ሰው» በማለት ጠራቸው፤ ይህንኑ ስያሜ በማር 8፡36 ላይ አፀና፤ *«ሰው የዓለምን ሀብት ሁሉ አግኝቶ ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል?»* በማለት ኃላፊነታቸውን ከተጠያቂነት ጋር ሲወጡ የተገባቸው «ሰዎች» መሆናቸውን ያለ ወንድ ሴት መለያ አኖረ።

ይህን ደግሞ ከእግዚአብሔር የመነሻው አደረጃጀት ጋር ይጣጣማል፤ «...ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር «ሰውን በመልካችን በአምሳላችን እንፍጠር...» ዘፍ 1፡26 አለ፤ በወል ስምነት ስለተጠሩት ወንድና ሴት አፈጣጠር መነሻውም መደምደሚያው ከእግዚአብሔር መልክና ምስያ መምጣት ነው፤ ይህ ከእግዚአብሔር የሆኑትን ባህሪያት በከፊል ተካፋይ እንደሆኑ ማረጋገጫ ነው፤ ሰው ከሌሎች ህያዋን ፍጥረታት መለየቱን (ከመላዕክት፣ ከእንስሳት ከመሳሰሉት) በዚህ አፀና።

ሰው በቀጣይ መገለጫው እግዚአብሔር በዘፍ 2፡7 «ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ ከመሬት አፈር ወስዶ «ሰውን» ከአፈር አበጀው» ይላል። በዚህ ሰው ማንነት ውስጥ ወንድ እና ሴት አዳምና ሔዋን ተገላጭ ሆነዋል።

ሀጢአት ወደ ሰው ከመግባቱ በፊት ይኖሩበት የነበረውን ይዞታ ሲያብራራም ባል እና ሚስቱ ራቁታቸውን ነበሩ ይሁን እንጂ አይተፋፈሩም ነበር። (ዘፍ 2፡25) በማለት ገለፀልን።





አለመተፋፈር የጋራ ጉዳይን በጋራ፡- በፍቅር፣ በሰላም፣ በደስታ ያከናወኑ እንደነበር፤ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ህብረት ሰምና ወርቅ መሆኑን ያበስራል። ዘፍጥረት መሰረት ጣይ መፅሐፍ ነው፤ ዘልቆም «የአዳም ዝርያዎች የስም ዝርዝር ከዚህ የሚከተለው ነው፤ እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረ ጊዜ በራሱ አምሳያ ፈጠራቸው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ባረካቸው ሰው ብሎም ሰየማቸው...» ይላል ይህ ገለፃ እውነትን በአግባቡ የማስቀደም አደራደር ነው።

የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጽሐፍት ፊት አውራሪ የሆነው ዘፍጥረት ይህን ካመላከትን ቀጣዩ የአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጽሐፍት መጀመሪያ የሆነው የማቴዎስ ወንጌል ደግሞ ጭብጡን ሳያዛባ ይልቁኑ ብሩህ አድርጎ አኑሮታል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ቀድሞዎቹ መምህራን፡- ኢቃይጦ፣ አሳከሮ ወይም አቻችሎ ሳይሆን እንደ ባለስልጣን በማስተማሩ አድማጮቹ ተደነቁ በመገረምም ማስተማሩን በፈፀመ ጊዜ ሕዝቡ በትምህርቱ ተደነቁ ምክንያቱም እንደ አይሁድ ሃይማኖት መምህራን ሳይሆን እንደ ባለስልጣን አስተምሮአቸው ስለ ነበር ነው። (ማቴ7፡28-29) የሚል ፅኑ ምስክርነትን ፃፈልን።

እሱ ባስተማረ ቁጥር፣ በተጠየቀ ቁጥር «ሁሉም ነገር እግዚአብሔር ወደ ፈቀደለት ወደ እርሱ ፈቃድ ይመለስ ዘንድ በተደጋጋሚ *«ለቀደሙት አትግደል የገደለ ይፈረድበታል እንደ ተባለ ሰምታችኋል እኔ ግን ወንድሙን ያለ አግባብ የሚቆጣ ይፈረድበታል... አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል እኔ ግን እላችኋለሁ ሴትን በምኞት ዐይን የተመለከተ ሁሉም በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል... ለቀደሙት ሰዎች በሀሰት አትማል... እንደተባለ ሰምታችኋል እኔ ግን ፈፅሞ አትማሉ... ዓይን ስለ ዐይን ጥርስ ስለ ጥርስ እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ ክፉ አድራጊውን ሰው አትቃወሙት ወዳጅህን ውደድ ጠላትህን ጥላ እንደተባለ ሰምታችኋል፤ እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ ለሚያሳድዷችሁ ፀልዩ...»* እያለ ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ወደ መፈጠሩ አቅም መምጣት እንዳለበት ማስተማሩ ነበር፡- ኢየሱስን ልዩ ያደረገው፤ ይልቁኑ ፈሪሳውያን *«ለመሆኑ አንድ ሰው በማንኛውም ምክንያት ሚስቱን መፍታቱ ተፈቅዷልን»* ባሉት ጊዜ ያላቸው *«ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አድርጎ እንደፈጠራቸው አላነበባችሁምን? ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣመራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የተባለው በዚህ ምክንያት አይደለምን...»* አላቸው። ለዚህ ጥያቄ ሰፊ ማብራሪያ ከሰጣቸው በኋላ እነርሱ ግን «ባህላቸውን፣ ትውፊታቸውንና አኗኗራቸውን በማስተሳሰር «ታዲያ ሙሴ ወንድ የፍቺውን ምስክር ወረቀት ሰጥቶ ሚስቱን እንዲያሰናብት ለምን አዘዘ?» ብለውት ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን «ሙሴ የልባቸውን ጥንካሬ አይቶ ሚስቶቻችሁን እንድትፈቱ ፈቀደላችሁ እንጂ ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም» በማለት ወደ እግዚአብሔር መሰረታዊ መርሐ ግብር መለሳቸው (ማቴ 19)፡፡

በአዲስ ኪዳን የመፅሐፍት ተርታ ቀዳሚ የሆነው የማቴዎስ ወንጌል ይህንን ቅድሚያ ሰጥቶ እንዳመለከተ ሁሉ ማርቆስም በ10፡6 «...ነገር ግን ከፍጥረት መጀመሪያ አንስቶ «እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው...» ያለለትን ልብ ማለት ተገቢ ነው። የእግዚአብሔርን መሰረት ጣይ እቅድ ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ መፍጠሩ ነው።

በዚህ እውነት በመጓዝ ላይ ያለች የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሁሉን ተቋቁማ መቆም እንድትችል በአሕዛብ መካከል በመገኘት፣ የምስራቹን በመንገር የፀናችው ቤተክርስቲያን በጳውሎስ አማካኝነት ሰው ሰውነቱን፤ ወንድና ሴትም ያላቸውን እኩላዊ መገለጫ ኢየሱስ በመስቀሉ ሥራው ከውድቀት በፊት ወደ ነበረው አቅም እንደመለሰው አስተማረ፤ ይህንንም በገላትያ ላሉ ቤተክርስቲያናት *«ሁላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ስለሆናችሁ በአይሁዳዊና በግሪካዊ፣ በአገልጋይና በጌታ፣ በወንድና በሴት መካከል ምንም ልዩነት የለም...»* አለ።(ገላ 3፡28)

በዝግጅቱ ቀዳሚነት የተሰጠው የ66 ቅዱሳት መጽሀፍት ሁነኛ ጭብጥ በምንነጋገርበት ርዕስ ጉዳይ ላይ በመነሻም በመድረሻም የሚለው ሰውን እግዚአብሔር ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ ሲፈጥራቸውም አፈጣጠሩ በራሱ መልክና አምሳል ሆነ፤ ወንድና ሴት በሁሉም ገፅታ እኩል ሆነው ይኖራሉ።

በማህበራዊ ሕይወት፣ በትውልድ ሰንሰለታማነት፣ በሰዎች መካከል በተፈጠሩ መስተጋብሮች አማካኝነት «እልፍ የተበላሹ ጉዳዮችም» ኢየሱስ ክርስቶስ ከመጣ በሁዋላ ወደ እግዚአብሔር ፈቃድና ሀሳብ በመመለስ፣ ግንዛቤን፣ እምነትን፣ እውነትን በአግባቡ ማየት ግድ መሆኑን እንዳስተማረ ቅዱሳት መፅሐፍት አሳወቁን። ይህን ልብ በማለት የቀጣዩ ምዕራፍ ጭብጣችንን ወደ ገዛ እይታችን በማምጣት ኢትዮጵያውያን «ወንድ»ን እንዴት እንደሚረዱት ከየሰነዱ እናነባለን።

## ምዕራፍ ሁለት

## ወንድ በአማርኛ መዝገበ ቃላት ውስጥ

*በ1962 ለንባብ የበቃው የደስታ ተክለ ወልድ «ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት» በገፅ 446 ላይ «ወንድ»ን እንዲህ ይፈታል፤ ያብራራል «አሱና አንተ የሚባል፣ የሩቅና የቅርብ ሰው፣ ተባዕት የሴት ባል፤ ገዢዋ አሳዳሪዋ፤ በጢም፣ በድምፅ፣ በትእምርተ ተባዕት፣ (የመሽኛና የወሲብ አካል) በጡት፣ በብዙ ወገን ከሴት ልዩነት ያለው ብርቱ፣ ኀበዝ እከሌ ወንድ ወጣው እንዲሉ ቅፅል ሲሆን ወንድ ልጅ ይላል»*

በዚህ ትንታኔ ለሴት ባል በመሆን ገዢዋ አስተዳዳሪዋ መሆኑን ፣ ከሴትጋ ሲነፃፀርም ብርቱ ኀበዝ





ጠንካራ በመሆን ከእርሷ የሚለይ መሆኑን ያፀናል።

*በ1951 ታትሞ ለአገልግሎት የበቃው የተሰማ ሀብተ ሚካኤል ከሳቴ ብርሀን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በገፅ 946 ላይ «የተከፈተ ብስ አካል የሌለው የወንድ ሰነ ፍጥረት ያለው ሁሉ ወንድ ይባላል»* ይላል።

በዚህ ፍቺ ወንድን በሰው ላይ ብቻ ባተኮረ መተርጎም ሳይሆን የእንስት ተቃራኒ የሆነው ተባዕት የሚለይበትን ቅድሚያ በመስጠት ተርጉመዋል።

በ1993 የታተመው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያዘጋጀው አማርኛ መዝገበ ቃላት በገፅ 412 ላይ *«ወንድ (ቅ) 1. ከሴት የሚለይበት ተፈጥሮአዊ የፆታ ምልክቶች (ለምሳሌ ፂም፣ ወይም ሌሎች መለያዎች ያሉት ሰው ወይም ሌላ ስጋዊ ፍጡር፣ እንስሳ 2. ኀበዝ፣ ጀግና»* የሚል ትርጉም ተሰፍሮለታል።

በየካቲት 2004 ለአደባባይ የበቃው**«ዘርጋው ክፍተኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት»** በገፅ 715 ላይ «ወንድ»(ስ) 1. የሴት *ተቃራኒ፡- ሴት ያልሆነ ወንዴ ፆታ* 2. ኀበዝ፣ ጀግና ደፋር በማለት *ተጋሪ* ትርጉም ሰጥተዋል።

በዚህም የቀደሙት የሰጡትን ትርጓሜዎች በገደብ በመያዝ የጋራዎችን አፅንቷል። መዝገበ ቃላት ሙሉ ለሙሉ ትክክለኛውንና የመጨረሻውን ትርጉም በመስጠት የትርጓሜ ቀኖናዎችን ያወጣሉ አይባሉም። በላጭ ትርጓሜዎች ማህበረሰቡ በቀዳሚነት ቃሉ በተጠራ ቁጥር ይወክልልኛል በማለት ፈጥኖ የሚግባባበትን ቀዳሚ አድርጎ ስለሚነሳ አንዳንዴ መዝገበ ቃላቱ ያሉትን ፍቺዎች «እንዳለ» ላይወስዳቸው ይችላል፤ ይህም ቢሆን ግን በጋራ ማህበረሰቡ ሊግባባበት ወይም በየጊዜው ሊሆን ያለውን በመጠቆም ብርቱ አጋዥ መሳሪያዎች ናቸው።

በአራቱ መዝገበ ቃላት በ«ወንድ» ላይ ለመምከር መነሻን አግኝተናል አስከትዬ «ወንድ» በስነ ቃል ዘርፎች ውስጥ የተገለፀባቸውን እናነባለን።

## ምዕራፍ ሶስት

## ወንድ በሥነ ቃል ዘርፎች ውስጥ

*እንደ ዘሪሁን አስፋው ትንታኔ «ስነ ቃል በመናገር፣ በመተረት ወይም በማዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከውን ቃላዊ ፈጠራ በመሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል ወግና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያና ልዩ ልዩ ክስተቶችንና የሕይወት መልኮቹን መግለጫ ኪነጥበብ ነው... በስነ ቃል ህዝቦች ማንነታቸውን ያሳውቁበታል፣ የዘርያቸውን አመጣጥ ይተርኩበታል፤ ስለ አካባቢያቸውና በአጠቃላይ ስለአለማቸው ያላቸውን ፍልስፍና ይቀርፁበታል» በማለት በገፅ 20 ላይ አብራርቷል።*

1992ኢ.ም. በአዘጋጀው **የስነፅሑፍ መሰረታውያን መፅሐፍ** ላይ ያለውን ይህን ጭብጥ መነሻ በማድረግ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ አብረውን የኖሩት ተረቶች፣ አፈ ታሪኮች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ባህላዊ ዘፈኖችና የመሳሰሉት በ«ወንድ» ጉዳይ ላይ ያኖሩት ግንዛቤ በየዘመኑ ላሉ ወንዶች ምን በጎና አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረው እንደነበር ያሳያሉ፤ ከዚህም የተነሳ በመረጃነት ይጠራሉ። ይህ ግንዛቤ በሴቶቹም ላይ ላለው አንድምታ ተቀራራቢ ውጤትን ይዞ ይመጣል።

ከመግቢያ መንደርደሪያው እንዳነበብነ:- ስነቃል ባህል ነው፤ ወግ ነው፤ ልማድ ነው፤ ታሪክ ማስተላለፊያም ነው። ይህም የሆነበት መሰረታዊ ምክንያት ሰው ማህበራዊ ፍጡር በመሆኑ:- ሰው ከሰው ጋር፣ ሰው ለሰው፣ ሰው በሰው ይኖራል። ይህ የኑሮ መስተጋብር ከሰው ልጅ ጅማሬ ጋር ነበረ፤ ዛሬም አለ።

ባህል ሁለንተናችን የሚገመድበት ልብ ሳንለው የራሳችን አድርገነው የምንሄድበት «መቅረጫ» ነው፤ በዚህ ዓለም ውስጥ ሆነን ሳናውቀው ስንቀረፅ፣ ስንበጅ አንዳንዴ ሊፈተሹ፣ ሊጠኑ የሚገባቸው ያልጠሩ መቅረጫዎች በእያንዳንዱ ላይ ተካተው:- እነርሱው እምነትን ፈጥረው ልክ ሳይሆኑ ልክ ሆነው፤ ሀሰት ሆነው ሳለ እውነት ሆነው ይጓጓዛሉ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድም ይሸጋገራሉ፤

ከእነዚህ ተሻጋሪዎች ፍቅርን፣ ፅናትን፣ በጎነትን፣ መተሳሰብን፣ ጥረትንና ግረትን፣ ዕድገትን፣ አክባሪነትን፣ በሁሉ ዘንድ እያሰፉ በሚጓዙት ላይ ጥያቄ የለኝም፤ ግና በ«ወንድ» ላይ በማተኮሩ ማህበረሰቡ ተቀብሏቸው በእኩል አቅም በወንዶችም በሴቶችም ላይ ተግባራዊ ሲሆኑ ተቀባይነት ያገኙ አጓጉሎች አሉን። ጌታቸው በለጠ በ2004ኢ.ም. **የጥበባት ጉባኤ** በማለት በጠራው መፅሐፉ ገፅ 108 ላይ *«ስነ ቃል የአንድ ማህበረሰብ ባህል መገለጫ ከሆኑት መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል በዋነኛነት*





*ይጠቀሳል እንደሰያሜው ስነ ቃል የሚተላለፈው በንግግር ቃላት አማካኝነት ነው የስነ ቃል ዓይነቶች ደግሞ በቁጥር አጅግ በጣም ብዙ ቢሆኑም ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ተረታተረቶች፣ እንቆቅልሽ፣ ቀልዳቀልዶች፣ እርግማንና ምርቃቶች፣ ቀራርቶ፣ ፉከራና ሽለላዎች፣ የቡሄና እንቁጣጣሽ ግጥሞች ሕዝባዊ ዘፈኖች፣ አፈ ታሪኮች፣ ሀተታ ዘፍጥረት፣ እንካ ሰላቲያዎች... በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፤...»* በማለት መሰረት ጣይነታቸውን በዝግጅቱ አፅንቶበታል።

እነርሱን ከኢትዮጵያ ምድር ላይ ተነስተን ዙሪያችንን እየቃኘን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወጣ እያልን ከዋንኛ ርዕሰ ጉዳያችን ጋር እንገጣጠማለን።

## ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ደበበ ኃይለጊዮርጊስ እንግዳ ባዘጋጀው የ1999ኢ.ም. አዲሱ **የምሳሌያዊ አነጋገሮች** መፅሐፍ ገፅ 285 ላይ:-

- ወንድ ሊበላ የሴት ሌባ
    - ለሌላው ሌላው መጨነቁን፣
- ወንድ ልጅ በበላበት አንበሳ በሰበረበት
    - ወንድ ሆዱ ያታልለዋል፤
- ወንድ ልጅ በተሾመበት ሴት ልጅ ባገባችበት
    - ሁሉም ጥቅም ወዳገኘበት ያደላል፤
- ወንድ ልጅ አንዴ እንደ አባቱ አንዴ እንደ እናቱ
    - ወንድ አንዳንዴ ያሸንፋል አንዳንዴ ይሸነፋል።

በማለት «የወንድ» ደረጃንና ማንነት ከማህበረሰቡ በመቀበል ፅፎታል፤ ብርሀኑ ገ/ፃድቅም **«ምርጥ የአማርኛ ምሳሌዊ አነጋገሮች»** በሚለው የ1998 ዝግጅቱ ገፅ 94 ላይ ስብስቡን አሰነብቧል፤ በደበበ ላይ ያልሰፈሩትን ላስከትል:-

ወንድ ልጅ ለፈረስ፣ ሴት ልጅ ለበርኖስ፣
ወንድ ባለ በዕለቱ፣ ሴት ባለች ባመቱ፣
ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንደ አባቱ፣
አመልማሎ ይሰጡት ይፍተል እንደናቱ።

ወንድ የሞተበት ወንድ አይሻገርበት፤

ወንድ እንደያዙት ነው፣

ወንድ ከዋለበት ከብት ከተሰማራበት፣

ከእነዚህ አንዱን እናጢን፡-

«ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንደ አባቱ

አመልማሎ ይስጡት ይፍተል እንደናቱ»

በመሰረቱ እንደ አባት መሆን ብዙ ገፅታ አለው፤ ጉዳዩ በመልክ ቁርጥ አባቱን በመሰለው ወንድ ልጅ ላይ አይደለም፤ የተወለደው ወንድ ልጅ አባቱን በሁሉ ነገር መውረስ አለበት፤ ጀግንነት ቢኖረው ጀግንነቱን፣ ሺ መላሽ ቢሆን ሺህ መላሽነቱን፣ አንባገነን ቢሆን አንባገነንነቱን፣ ወርሶ እንደ አባቱ መሆን ይጠበቃል፤ በጎ ጎኑ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ጎን ለጎን ካባቱ ማን አለብኝነትን የወረሰ ወንድ ያንኑ ለልጁ ማውረሱን ልብ ልንል ይገባል። እነህ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ምናልባት ከአማርኛ ቋንቋ ዕድሜ ጋር እኩል እድሜ እንዳላቸው ማሰብም ተገቢ ነው፤

## ቅኔ

ቅኔ ውበት አለው፤ ቁም ነገሩ ብዙ ነው፤ ዜማዊ ሆኖ ስርስር ይገባል፤ በገባበት ውሎ ያድራል፤ እየተባባሉበትም በውስጡ የተላለፈውን ትምህርት እምነት አድርገው ሊይዙት የሚያስችልም አቅም አለው፤ በ**«እዲሱ የአማርኛ ቅኔ ከነመፍቻው»** መፅሀፍ ገፅ ፤ ላይ *«...ቅኔ የጥንት «ዩኒቨርስቲዎቻችን» በነበሩበት፣ የቅኔ ት/ቤቶችና የመንፈሳዊ ትምህርት አድባራት፣ በግዕዝም ሆነ በአማርኛ እየተቀኘና፣ እየተዘረፈ፣ የበሳል አእምሮ መለኪያ፣ የርቱዕ አንደበት መገምገሚያና የምሁራዊ ቁንጮ መስፈርት ሆኖ የዚያን ጊዜውን የትምህርት ደረጃችንን ርቀት ሲገልፅ ይኖራል...»* በማለት ፅፏል፤ ይህ አባባል አእምሮ ኮርኳሪነቱን፣ አስተማሪነቱንና ጥንታዊነቱን ያሳያል፤ ቅኔ ዘርፈ ብዙ ነው፤ አንዱ መገለጫው ደግሞ ኅብርን በመያዝ ሰምና ወርቁን መለየት፣ ማብራራት እና ማጥናት ነው። በኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ ቀድሞ በብሔራዊ ቋንቋነት አሁን በሥራ ቋንቋነት ያገለግላል፤ ቋንቋው ከዕድገቱ ባህሪይ የተነሳ የበርካታ ቋንቋ ባለቤቶችን በማገናኘት በሀገሪቱ ውስጥ ሰፊ ግንኙነትን መስራች ሆኗል።

ይህን አቅሙን ካገለበቱት አንዱ የትምህርት ማዕከላት ናቸው፤ ዘመናዊ ትምህርት ከመደርጀቱ በፊትም ሆነ በኋላ ቅኔ ተጠሪ ሆኖ ተገኝቱዋል። ይህ የማስተማሪያ ዘርፍ «ወንድ»ን በተመለከተ ያመለከታቸውን ጥቂት ስራዎች ላቀባብል፡-





1. **ወንድ ልጅ አርግዤ እስከ ቢልቢላው**

   **ወየው ቀኔ ደርሶ ተገላግዬው።**

ሊተላለፍ የተፈለገው-ተገላግዬው በሚለው ድርብ ፍቺ ቃል ላይ በማተኮር ወልጄው ወይም ሞቼው ማለት ነው። አቀኛኙቱ ግን «ሴት ልጅ አርግዤ...» በማለት ይህን ለማዳበር አልፈለገም፤ በመሰረቱ ፍቺውን በየትኛው አቀኛኘት ማምጣት ይቻላል። አርጋዧን ከወንድ ልጅ ጋር ማሰቡ ግን ተዋልዳዊ ነው።

2. **እኔማ ወለድኩኝ ሁለት ወንድ እና ወንድ**

   **ተበቃይ ከሆኑ ከዚያች የሰፈር ልጅ።**

የወላጅ ያውም የእናት ቃል ሆኖ ነው የተመዘገበው፤ ወንድ ልጆች ለአንድ ጥቅም እንደሚፈለጉ ታረጋግጣለች፤ እሱም ተበቃይ ሆነው «ጠላቴ» ያለቻቸውን ያስወግዱላታል፤ በመሰረቱ ተጠቂ የሆነችው ሴት መሆኗ የሀዘን ደባብ ቢፈጥርም ግን የመበቀል አቅም ያለው የሕብረተሰብ ክፍል ወንድ ልጅ ሆኗል።

**ወንድን ከአፈር ሰርቶ ሲያበጃጀው፣**

**ሴቷን ካጥንት አርጎ መውጊያን ሰጠው።**

ረዳትነትን ሳይሆን ሴትን በዘመኗ መነሻና መድረሻ ሁሉ ወንድን ወጊ አሰቃይ እና ጎጂ መሆኗን ቅኔው ያረጋግጣል፤ ወንድ ከአፈር ተበጀ መልካም፤ ሴት ግን ከአጥንት አጥንት ሆና ወጣች። ሕብሩን ካጥንት አድርጎ ቢነሳም ግና የሚያቀባብለው ጭብጥ ወንዱ የሁልጊዜ ወጊ ጠላት እንዳለው ነው።

ይህ በቅኔ ጥልቅ ሀሳብ ማስተናገጃ እያደረገውም፤ ይልቅስ «ሰው ሰራሽ» ትምህርትን፣ ተረትን እውነት ነው ብሎ እንዲቀበለው ማድረጊያ ነው።

## ግጥም

የግጥም ስም ሲነሳ ክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤልን አስታውሳለሁ፤ ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህንን፣ ሊቀ ሊቃውንት መንግስቱ ለማን አስባለሁ፤ ዘመነኞቹ ደግሞ ብዙ ናቸው። ብዙ ይገጥማሉ፤ ብዙምይላሉ፡- ዳዊት ፀጋዬ **«እርነት በወጡ ሀሳቦቹ»** ይህን አስነብቦናል፤ በ2003ዓ.ም. «እውነት» ብሎ የጠራው ግጥሙ፡-

«አምላኬ ሆይ!
የሰጠኸኝ ሴት
ወደብ አልሆን ብላ
ነፍስና መንፈሴ
ሥጋዬም ተጉላላ
«ወተት ሁኚ» ብላት
ሆነችብኝ ውጋት
ብሎ ቢያሳቅላት
አምላክ መለሰለት
«ታዲያ ይህች ሴት
ምንድነው ስህተቷ?
ምንድነው ጥፋቷ
እንዴትስ ይባላል
የትሄደ ወተቷ?
ቀድሞም አጥንት ናት
መዋጋት ነው መብቷ»

ባስነበበን በዚህ ግጥም ስሜታችን ተኮርኩሯል፤ ደስ ብሎን አጨብጭበን ይሆናል። ግና ግጥሙ በቅኔዎች ከተላለፈው መልዕክት ጋር ተዛምዷል። በመተጋገዝም«ወንድ» ጠላት እንዳለው እሷም «ሴት» መሆኗን ያረዳል።

ተስፋዬ ድረሴ **«የዕድሜ እስቤዛ»** በማለት በ1999 ኣ.ም. ባሳተመው የግጥም መድበሉ፡- «ድምፅ አልባ ጠለፋ»፡- በማለት በገፅ 55 ላይ እንዲህ ብሏል፡-

እንጀራዋን አድን ብላ
ያለ ነቃሽ ተዋውላ
ስንቷ ትሆን መብቷን ሽራ
የምትኖር ተሳቃ አፍራ
ለአለቃዋ ራሷን ድራ?
ወንዱ ቢያንሰው ስልጣኔ
ሴቷ ደግሞ ሀሞት ወኔ
በየቢሮው ጠለፋ አለ
አስገድዶ መድፈር ጭምር





እሪ ብሎ ለማስያዝ
አንድ ብሎ ማን ይጀምር?
ሳይጮህማ ባለቤት
ሙች ይደርሳል ጎረቤት...

ግጥሙ «ጉድ» በማለት እንተዛዘብበት ይሆናል ግን ጎን ለጎን መሆን ያለበት የውዴታ ግዴታ አለ። እሱም ለወንድ «አለቃ» ማደር ፍላጎትንም መሸጥ ነው፤ ይህን ሴቲቷ ፈርታ የምትፈፅመው ያስመስልባታል፤ ግን ፍርሀት አይደለም ውርስ የሆነ ኑሮ እንጂ፡- «ሳይጮህ ባለቤት ማን ይደርሳል ጎረቤት» እስከተተረተ ድረስ።

በመሰረቱ አንዳንድ ግጥም በአፈ ታሪክነት ሊመዘገብ ይችላል፤ ከ50 ዓመት በፊት ተፅፎ ኋላ በ1999ኣ.ም.ዳግመኛ በታተመው የከበደ ሚካኤል **«የቅኔ ውበት»** ውስጥ «አዳምና በሬው» የሚለውን ስነቃላዊ መልዕክት እናገኛለን በመፅሐፉ ገፅ 92-3 ላይ የምናገኘው መነሻውን ከሰው የውድቀት ታሪክ ይጀምራል

**«ከወጣ በኋላ ከገነት ተሰዶ**
**አዳም ያርስ ነበር በሬዎቹን ጠምዶ።**

ከዚያም አዳም በበሬው ላይ በደል አደረሰበት፡- ደጋግሞ መታው፤ በወቅቱ እንስሳት ከሰው ጋር በቋንቋ ይግባቡ ስለነበር፤ በሬው የሙብት ጥያቄ አነሳለት፡- አዳም ወንዱ ግን ቀበቀበው በዚህ ጊዜ በሬው ተናገረው፤-

**አንተ እኮ እከው . . .**
**የበከስ ፍሬ የቀመስክ ከታ**
**ትዕዛዙን ስታፈርስ ያኘን ያህል እዝና**
**አልደበደበህም እንደዚህ ጨክኖ» እከው**

አዳምም እግዚአብሔርን «ቅጣቴ መች አነሰ ይዝለፈኝ እንስሳ» በማለት በመጮሁ እግዚአብሔር ለአዳም እዘነ እና መፍትሄ አበጀለት፡- በአዳም በወንዱ የፀሎት ጥያቄ እግዚአብሔር ታዛዥ በመሆን በሬን ብቻ ሳይሆን እንስሳን ሁሉ ዱዳ አደረገ። በዚህም ከአዳም ከወንዱ ጥቃት በሚመጣ ህዘን እንስሶች እንዳያሳቅሉ...»

**በጣም አዘነና በዚህ የተነሳ**

**እሮሮ እንዳይሰማ አዳምን ኪረዳ**

**ከዚያን ቀን ዝምሮ አምካከ በመደዳ**

**እንስሳትን ሁሉ አደረገ ድዳ።**

በዚህ ቅኔ ወንዱ አዳም እግዚአብሔርንም ተገዳድሮ ውጤታማ ከሆነ በሴቶች ኑሮ ውስጥ የልቡን የማይፈፅምበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

**«አንተ ባትፈጠር»** በሚል ርዕስ ግጥሟን ያኖረችው ልዩ ወርቅ ወንድ አፍራሽ ያስነበበችውን ከግምት እንከተተው:-

**ፍጥረትህ ነግሮኛል**

**አቅምህ ተረጋግጧል**

**አእምሮ ብሩህ ነው**

**እኔን እኑረሀል**

**እኔኮ እኔማኮ ሴት ነኝ**

**የሁለት ፊደል ቅምር**

**የማነስ ምልክት ከሶስቱ ወንድ ጋር**

**አንተ ባትፈጠር**

**ምን እሆነው ነበር።**

ግጥሙ በሴት መፃፍ ለአሉታዊ ገፅታው ተጨማሪ አሉታን አመንጪ ነው፤ ሴት ያመነችበትን በአደባባይ በማውጣት ወንድ እግዚአብሔር ከሰጠው አቅም ሁሉ ወጥቶ ራሱን እንዳያውቅ ያደርጋል፤ ሰው ግብዝ ነው፤ ግብዝነቱን ያንራል።

ይህ በምክንያታዊነት ያልተደገፈ ሙገሳ ነው፤ ወንድ በሶስት ፊደል መፃፍ የ«ሴት» በሁለት ፊደል መከተብ የመተናነስ መገለጫ ሆኖ መዘከሩ አጉል ነው፤ ገጣሚዋ ምነው በእንግሊዝኛ ፅፉ Man ን ከ Woman ብትቆጥረው፤ ከዚያ በላይ ግን የተባለለት በመምጣቱ ይቀበለው እንጂ ፍጥረቱም ሆነ አቅሙ የማንነቱ የማረጋገጫ ሰነዶች አይደሉም።





## ተረት ተረት

እንደ ዘሪሁን አሰፋው አገላለፅ «ተረት ከተጀመረ ዘመን የለውም ተረት የማውራት ውስጣዊ ስሜትና ተረት የማዳመጥ ፍላጎት ትረካን (ተረትን) በስልጣኔ ታሪክ ውስጥ የሰው ልጅ የተፈጥሮ አኩያ እንዲሆን አድርገውታል... ተረት የማህበረሰቡን ወግና ልማድ ስነ ምግባርና አጠቃላይ የዓለም አመለካከት ሊያስተላልፍ ይችላል...» (ገፅ 28-9) ይላል።

ከዚህም በመነሳት የሰው እኩል ዕድሜ እንዳለው የሚነገርለት ተረት በኢትዮጵያ ማህበረሰብ ውስጥ ግዙፍ ስፍራ አለው።

በአገልግሎቱ በጎ ውጤቶችን አስገኝቷል፤ ልክ የለሽ ጥፋትንም ያመጣበት ገፅታው ብዙ ነው። ተረት ህፃናት ያድጉበታል፣ ወጣቶች ጎልማሶች አዛውንቶች አይርቁትም፤ ይሉታል፤ ያደምጡታል።

ተረት ፈጠራ ነው፤ በብዙም የተጋነኑ ጉዳዮች አሉት ግን በስምምነት «ለምን ይህ ሆነ?» በማለት መጠየቅ አይፈቀድም፤ የለምም፤ ባለመኖሩ ግን «የቅብብል - ትረካ - እውነት እስኪመስል ድረስ ተላልፎ ሰዎች ተረት ነው እያሉ የኑሮአቸውን አካሄድ ይመሰርቱበታል። ያኖሩበታልም። ከዚህም የተነሳ ለርዕሰ ጉዳያችን ማዳበሪያ የሚሆን የሕዝብ ሁለት ተረትን መጥኜ አስነበባለሁ።

### ተረት አንድ

*ተረት ተረት - የመሰረት (የላም በረት)*

*ጥንት አንዲት ሴት ብቻ በምድር ላይ ትኖር ነበር፤ ከእርሷ በቀር እንስሳት ሁሉ ወንድና ሴት ስለነበሩ እርስ በርሳቸው ተጋብተው በፍቅርና በሰላም ይኖሩ ነበር፤ ሴቲቱ እነርሱን ሲዋለዱ፣ ሲተጋገዙ፣ ሲፈነድቁ እያየች ትገረማለች! ከዚያም ጥያቄ በእርሷ ውስጥ ይፈጠራል «ለምን ብቻዬን ቀረሁ?» ትላለችም፤ ይህን ጥያቄዋን ዝም ብሎ ከመያዝ ብላ በዙሪያዋ ያሉትን እንስሳዎች ጠየቀቻቸው።*

*እነርሱም «ፈጣሪ አንቺን የመሰለ ወንድ ቢሰጥሽ ተቃዋሚው፣ በዳዩ፣ አሳዛኙ እና ገዳዩ መሆንሽን ስላወቀ ነው ብቻሽን የተወሽ» አሏት፤ እሷ ግን «እንዲህ እኮ መሆኔን በምን አውቀዋለሁ ቢሰጠኝ ግን እንዳለው ሳይሆን እንደ እናንተ ሚስቶች ሆኜ እገዛለታለሁ፣ እወደዋለሁ፣ ፈቃዱን ሁሉ እፈፅማለሁ» አለቻቸው።*

*ይህን እያለች ባለበት ሰዓት ሰማይና ምድር ተገናኝተው ካለበት አድማስ አንድ የሚያምር ሰው ወደ እነርሱ መጣ እሱም በቀጥታ ወደ እርሷ ተጠግቶ «ፈጣሪ እንዳልሽው የምትሆኚለት ከሆነ ሰውየው ይኸው ቃልሽን ካጠፋሽ ግን እሱ ጠላትሽ ይሆናል፤ ከእርሱም ልትለይ አትችይም መከራም አይለይሽም» አላት።*

*እሷ ግን መልዕክተኛው እያናገራት ተጠጋቸው፣ አቀፈችው፤ እሱም አቀፋት። በዚያ ቀን ሴቲቱ የምትሆነውን አጣች «እንግዳ ወርቅ ነው» ብላም አስገረመችው። በሁለተኛው ቀን ግን «እንግዳ ብር ነው» እያለች ከትናንት በቀነሰ አስተናግዳው በሦስተኛው ቀን «እንግዳ ብረት ነው» ብላ ማመናጨቅ ጀመረች። በዚህ ግዜ ሰውየው «ሰዓቱ አለቀብሽ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ምንም መብት የለሽም፤ ፈቃድሽ ሁሉ ወደ እኔ ነው አስተዳዳሪሽም እኔው ነኝ እገዛሻለሁ እንደፈለኩትም አደርግሻለሁ» አላት ይባላል ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ።*

ይህ ገለፃ በተረትነት ይመደባል፤ በአፈ ታሪክነትም ይጠራል፤ለአፈ ታሪክነቱ የመነሻ ታሪኩ አዳም ብቻውን እንደነበረ ይህ ገለፃ ደግሞ ሴቲቱን ብቻዋን አድርጎ ያሳያል ሀጢአት ወደ ዓለም በመግባት ያመጣውን ቀውስ የሚመስል አተራረክ አለው፤ ይህ አካሄድ እውነትን መነሻ አድርጎ ቀሪውን በፈጠራ ስለሞላው የአፈታሪክ ባህሪይ አለው በጥንት ዘመን በማለት ጀምሮ የራሱን የተረት ባህርይ ስለያዘ፤ ተረት ነው፤ እንስሶችን ያነጋግራል፤ ያልተጠበቀ ታምርን ከአድማስ ጥግ ያመጣል።

ገለፃው አፈታሪክም ሆነ ተረት እየተባለ የመጣው በዘመናት ሁሉ ውስጥ ነው፤ ተረት ህፃናትን እንቅልፍ ማስወሰጃ ብቻ ሳይሆን ማስተማሪያ ነው፤ በማስተማሩም ልጆችን፤ ወጣቶችን፣ ጎልማሶችን ሁሉ ያደላድላል፤ በዚህ ተረት ውስጥ አልፈው ያደጉ ተረቱን ቢረሱት እንኳ የጀመሩትን የአቋም ፈተናና የአመለካከት ዘላቂነትን ግን አይተዉትም። በዚህም ሴቲቱን ተጠያቂ ማድረግ፣ በገዛ መነሳሳቷ የገባችበት ጣጣ መሆኑን፣ ምን ግዜም ተገዢ ሆና መኖሯን በመቀበል መፅናቷን፤ በወንድ በእኩልም ሥራዬ ብሎ ለሚኖርበት እቅምን ይፈጥርለታል።

እነዚህን የመሰሉ ተረቶች ብዙ ናቸው የጥንት ግሪካውያን፣ ሮማውያን፣ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ተለይተው እንደተጠሩ የሚነገርላቸው «እስራኤላውያንም» ተመሳሳይ ይዘታ ያላቸው ተረቶችና አፈታሪኮች አሏቸው።





## ተረት ሁለት

*ተረት ተረት - የመሰረት*

*«...ልጆች ሴቶች ከምን ከምን እንደተሰሩ ታውቃላችሁ? አታውቁም፤ እኔ ግን ከድሮ ጀምሮ ሲነገር የመጣውን ታሪክ እነግራችኋለሁ፤ እግዚአብሐር ወንድን ከአፈር አበጀና እስትንፋሱን እፍ አለበት፤ በዚህ ጊዜ ብድግ ብሎ ቆመ፤ የቆመበት ስፍራም ስለተንቀጠቀጠ ፈጣሪው «ፀጥ ብለህ ተገዛ!» አለለት፤ መንቀጥቀጡንም ተወ፤ የተፈጠረው ወንድም ጉብኝት ሲጀምር «ትላልቅ ዛፎች» ጎንበስ በማለት ሰላምታ ሰጡት፤ «አስተዳዳሪያችን አንተ ነህ እኮ» እያሉ አጨበጨቡ ወደ ደኑም ገብቶ ጉብኝቱን ሲቀጥል አንበሳ፣ ነብር፣ ዝሆን ከበውደስታቸውን ገለፁለት ከዚህ በኋላም እግዚአብሔር ወንድን ከፈጠረ በኋላ ሌላ የመፍጠሪያ እቃዎች ስላነሱት ከሁሉም የተራረፈውን ወስዶ ሴትን እንደፈጠረ ሰምታችኋል? ካልሰማችሁ ሴትን እግዚአብሔር የፈጠረው የሚከተለውን አዋህዶ መሆኑን እወቁ፤ የጨረቃን ድንቡሽቡሽነትና የወይን ዘለላነት፣ የቄጤማን ለሸባይነት፣የሸንበቆን ሸንቃጣነትና የአበባን ፍካት፣ የቅጠልን ቀላልነትና የብርሀን ፀዳል ፀጥታን፣ የደመናን እንባና የንፋስ ዋዣቂነት የጥንቸልን ፈሪነትና የአውራዶሮን ትምክህተኛነት፣ የርግብን ልብ ልስላሴና የአልማዝን ጠንካራነት፣ የማርን ጣፋጭነትና የበረዶን ቀዝቃዛነት፣ የፍየልን ምላሳምነት እና የአዕዋፋትን ዘማሪነት፣የጦጣን አታላይነት እና የሴት አንበሳን ታማኝነት፣ በመቀላቀል ሴትን ከሰራ በኋላ ራሱ እግዚአብሔር «ይኸው ረዳትህን ተቀበለኝ» ብሎ ሰጠው። አዳም ግን ሳምንት ያህል ብቻ አብሯት ቆይቶ ይዞለት በመምጣት «ጌታ ሆይ የሰጠኸኝ ይቺ ፍጥረት ነፍሴን አጎሳቆለች መሸከም እስከማልችል ድረስ ያለማቋረጥ ትናገራለች፣ እንደ ትንሽ ልጅ ሁል ጊዜ እሹሩሩ እንድላት ትፈልጋለች፡ በዚህ ጊዜዬ አለቀ ከለቅሶ በቀር ስራ የላትም ስለዚህ ውሰድልኝ» ብሎ መለሰለት ይባላል።*

እንግዲህ፡- «ይባላል» መባሉን ልብ በሉ፤ አቅርቦቱ ተረት ነው፤ እውነት አይደለም ግን ተረቱ ብዙ እንድምታዎች አለው፡- በአፈታሪኩ ውስጥ ጠንካራ እና ደካማ ጎኗን የሚገልፁ ተነፃፃሪ ምሳሌዎችን ወይም መፈጠሪያዎችን ስለያዘች የተመጣጠነ ነው ብለን እንድናስብ ያደርጋል፤ ይህን ብቻ ግን አመቻችቶ አልተወም። በሀጢአት የተበከለ ሰው ከቀናው ይልቅ ወልጋዳውን የመምረጥ ዝንባሌ አለው፤ ከዚህም የተነሳ የወንዶች ዓለም፡- ሴት እንደ ጥንቸል ድንጉጥነቷን፣ እንደ በረዶ ቀዝቃዛነቷን፣ እንደ ፍየል ምላሳምነቷ ላይ እና እንደ ጦጣ አታላይነቷን በመዘከር መዝለቅን ይወዳል፤ ዘልቋልም፤

ይህ ደግሞ አሉታዊ ተፅዕኖን በማዝለቁ አሌ አይሰኝም፤ ይልቅኑ ከትርፍራፊ ተረፈ ምርት ተገኝቶ ለአፍታ ቢያስቅም ለሁል ጊዜ ግን ለቅሶን ይዘራል። መላው የዓለም ሕዝብም ሆነ ኢትጵያውያንን በግልፅ የማንጋፈጣቸውን ቁም ነገሮች በእጅ አዙር ወደምንፈልገው እንዲያደርስልን እናደርጋለን። ልብ ብለን ረጋ ብለን ካሰብን ወንድስ ከምን ከምን ተሰርቶ ይሆን? የሚለውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ትኩረት መስጠት ይጠቅማል፤ እንግዲህ ተረቶችን፣ ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ ወዘተ ሁሉ ዞር ብለን ልንፈትሽ ይገባል።

## መፅሐፍት እና የስነ ቃል አገካከፃቸው

ስነ ቃል መገለጫ ነው፤ ማንነትን፣ አገነዛዘብን፣ እምነትን ሁሉ በማስተሳሰር በሰው ደም ውስጥ የሚገኝ ዓለም አቀፍ ሀብት ነው፤ ሰው ባለበት እሱም አለ፤ የስነ ቃል ሀብታምነት ባለፀጋነት ነው፤ ትምህርት ቤት ነውና ህፃናትን፣ ወጣቶችን፣ ጎልማሶችን አዛውንቶችን ሁሉ ያግባባል እውቀትን እና «ሀይማኖትን» ያቀባብላል።

ከዚህም የተነሳ በኢትዮጵያ ያሉ ወንዶች ስለራሳቸውም ሆነ ስለሌሎች ዛሬ ላይ ይዘውት ለሚዘልቁት ግንዛቤና አመለካከት ወሳኙ አብሮ መኖር ያሳደገው የስነ ቃል መገለጫዎቻችን ናቸው፤ በመነጋገሪያ የመነሻ መንደርደሪያ ሁሉ ላይ ልብ እንዲልለት የተፈለገው ለልማታችንም ሆነ ለጥፋታችን «ራስነታችን ነው» በማለት ልከኛውን አቅም መፍጠር ነው።

በቀደሙት ተረቶች፣ ምሳሌዊ ንግግሮች፣ ቅኔዎች እና ፍቺዎች ሁሉ ውስጥ በስፋት «ወንድነት» እንዴት እንደተገለፀ ልብ ብለናል፤ በዚህ ርዕስ ስርም እርሱን አሳዳጊ ጭብጥን አነሳለሁ።

መፅሐፍት ይነበባሉ፣ ይተረካሉ፣ ማስተማሪያ ሆነውም ይቀርባሉ። የተረት መፅሐፍት በኢትዮጵያ እየተዘጋጁ እየተሰራጩም ነው፤ እነዚህ ደግሞ ይጠቅማሉ፤ ወጥ የሆኑ ሀገራዊ ተረቶችም ሆኑ የተተረጎሙ የውጭ ዓለም መፅሐፍት እነማንን በበጎ አንስተው እነማንን አንኳሰሱ? እነማንን ዋንኛ ገፀ ባህሪ አድርገው እነማንን ንዑሳንና መንገደኞች አደረጉ? ወንድ በሰውም መልክ ሆነ በእንስሳ ገፀ ባህሪነት የተጫወታቸው ድርሻዎች፡- ሴት በሰውነት ወይም በእንስሳ የባህርይ ትንታኔ ላይ ምን ያህል ተገልፀዋል? እነዚህ ጥያቄዎች በጥናት ተደግፈው ወደ ልከኛ ማጠቃለያ መዝለቅ ይኖርባቸዋል። በዚህም አሉታዊ አስተዋፅኦን ባደረጉት ላይ ብቻ ጥቂት እላለሁ

***

በክርስትና ቀዳሚ ሀገር ነኝ ብላ በድፍረት የምትናገረው ሀገራችን ኢትዮጵያ ናት፤ ከታሪክ አገላለፅ አኳያም ይህ እውነት ነው፤ እንዳለችው ክርስትናን ቀድማ በመቀበል እንዲሁም የብሉይ





ሥርዓትንና ትምህርትን ከዚህም ቀድማ ማመኗም ሀሰት አይደለም እወቁልኝ እስካለች ድረስ የቅዱሳን መፅሐፍት ባለቤት ሆና መገኘት ሰውን በትክክል ለመረዳትም ሆነ እግዚአብሔር በሰው ላይ ያለውን ዓላማ ለመገንዘብ አቅምን በፈጠረላት ነበር። በቀዳሚው ምዕራፎች እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳል እንደፈጠረው፤ እኩል አድርጎ እንዳመጣቸው ይህም በሰው ልጅ ታሪክም ውስጥ እውነት ሆኖ እንዲዘልቅ ፈቃዱ መሆኑን አመላክቻለሁ፤ ይኸው ጭብጥ በተዛባበት፣ በተሸነፈበት ስፍራ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድ እና ሴት በእግዚአብሔር ፈቃድ እና ዓላማ አኳያ የተለወጠ ምንም ነገር እንደሌለ በመግለፅ እና በማስተማር ወደ እርሱ ይመለሱ ዘንድ መከሯል። አስመክሯል። ልኩንም አስተዋውቋል።

ይህ እውነት ኢትዮጵያን አሸንፏት ሊገዛት አልቻለም፤ ሰዎች እኩል አይደሉም፤ ወንድና ሴት በምንም አይቀራረቡም፤ ባል መሆን እና ሚስት መሆን የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው፤

የክብር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ **«ፍቅር እስከ መቃብር»** በሀገራችን ተነባቢና ተወዳጅ ስራ ነው፤ ዛሬም ይመረጣል፤ ይወደዳል፤ በዚያ ስራ ውስጥ ሀዲስ፡- ህብረተሰቡ ለወንዶች የሚሰጠውን ተገቢ ያልሆነ ስፍራ በየምዕራፎቻቸው በአግባቡ አኑረዋል፤ በትይዩም ሴት የመወሰን፣ የመምረጥ መብት እንደሌላት በማብራራት ለእሷነቷ ወሳኟ ሌላ አካል መሆኑን አፅንኦት ሰጥተው ፅፈዋል። ሀዲስ ይህን ከትውልድ ወደ ትውልድ «ልክ» እና «እውነት ነው» ተብሎ የሚታመንበትን ስነ ቃላዊ አስተሳሰብን ነው የተፈታተኑት፤ ፊት አውራሪ መሸሻም ሆኑ ወይዘሮ ጥሩዓይነት በሴት ልጃቸው ላይ የወሰዱት አቋም ለዚህ ዝጅግት መንደርደሪያ ነው፤ ፊታውራሪ «ወንድ» ከመሆን ባሻገር «የወንድ መለኪያ» እንዳላቸው አምነዋል፤ ሴቲቱም በሴት ልጃቸው ላይ ተመሳሳይ አቋም ወስደዋል። በዚህም ከቅዱሳት መጽሐፍት ሀያልነት እና አስተማሪነት በበለጠ ትውፊት ቀዳሚውን ስፍራን በመያዝ ራሱ በቁሙ «እምነት» መሆኑን ያረጋግጣል፤ ይህ ዛሬም አለ፤ ወደ ፊት ሊኖርም ይችላል፤ ለዚህም ጥቂት እናንብብ፡- የገፅ 85-86ን ንባቡ በማየት ብቻ ከአጠቃላይ የ«ወንድ» ተባዕታዊ አገዛዝ ጋር ምን ግንኙነት አለው? የሚል ቢኖር በትዕግስት መላልሶ ልብ ማለት ወደ ልኩ ያደርሳል፡-

> *«...ፊት አውራሪ መሸሻና ምሽታቸው ወይዘሮ ጥሩ አይነት በዘር ያከለናል ይመስለናል የማይሉት ሰው ልጃቸውን ሊጋብቻ ሲጠይቅ እንኩዋንስ ሊሰጡ መጠየቃቸውን እንደ ብርቱ ውርደት እየቆጠሩት አጅግ ያዝኑ ነበር።*
>
> *«ወዮው ጉዴ! ጆሮ አልሰማም አይልምኮ እናንተ» ይላሉ ፊታውራሪ መሸሻ ከውጭ ሲገቡ*
>
> *«ዛሬ ደግሞ ምን ሰሙ ጌታዬ?» ይላሉ ባለቤታቸው ወይዘሮ ጥሩአይነት*

*«ቀኛዝማች እገሌ ሰብለወንጌልን ለልጁ ለመነኝ»*

*«ቀኛዝማች እገሌ የማንልጅ ነው?»*

*«አባቱን እንኩዋን እኔ እሱም አያውቀው»*

*«ትልቅ ድፍረት!» ይላሉ ወይዘሮ ጥሩአይነት*

*«ግራዝማች እገሌ ልጅህን ስጠኝ አለኝኮ ጥሩ»*

*«የማን ልጅ ነው ጌታዬ!»*

*«አባቱ ሰው አይደለም ገበሬ ነው»*

*«ይሀን ሳልሰማ በሞትሁ»*

*«ፊት አውራሪ እገሌ ልጁን ለልጁ ለመነኝ»*

*«የማን ልጅ ነው?»*

*«አባቱ መጫኛ ነካሽ ነጋዴ ነበር»*

*«ምነው ከምታሰድበን ባልተወለደች»*

*«ባላምባራስ እገሌ ልጅህን ስጠኝ ብሎ አማላጅ ላከብኝኮ ሀ...ሀ...ሀ ወይ ጊዜ!»*

*«የማን ልጅ ነው?»*

*«አባቱ ብዙ ላም የነበረው ባለጌ ባላገር ነበር፣ እሱ ሲሞት ላሙን ሁሉ አውርሶት ሞተ አሁን አጉዋቱን በፋጋ እየጠጣ ሆዱ ሲነፋ ጊዜ ከሰው እኩል የሆነ መስሎት ይሄዋ የኛን ልጅ ይለምን ጀመር!»*

*«ይበለን ኸረ ይበለን ሲያንሰን ነው ሲያንሰን ነው ለቀን ሰው ወዳለበት እንዳንሄድ እንደታሰርን ሁሉ ይሀን ሀገር መልቀቅ አቅቶን የባላገር መጫዎቻ ሆን» ይላሉ ወይዘሮ ጥሩዐይነት ዕንባ እየተናነቃቸው*

*«አይ ያንቺ ነገር ሰው ወዳለበት የምትይ ዛሬ የሰው ምርት አልቆ ግርዱ በቀረበት*





*ዘመን ምን ሰው አለ? የትም ብትሄጂ ቢበዛ አባት እንጂ አያት ያለው ሰው ይገኝ መሰለሽ?»*

*«እንዴት?»...*

*ለዚህ የጥሩዐይነት ጥያቄ ፊትአውራሪ የሚሰጡት ምላሽ ጠባብነትን ያጎላ፣ ፈጣሪ ከእርሳቸው ጋር በመቆም ሌላውን ሰው የጠላ፣ ዛሬ ያሉ ሰዎች ተቃይጠው ተካልሰው ማንነታቸውን ያጡ በአዳጉሎቹ ፊትአውራሪ፣ ቀኛዝማች እንደተባሉ በመናገር፣ የእሳቸውን ግን የእሌኒን የገላውዲዮስን፣ የሱስንዮስን ልጅ ለገበሬ ለነጋዴ አልሰጥም በማለት ሲቆጡ ነው የሚነበብ፤ በማጠቃለያ ውሳኔያቸውም «እርስዎስ ልስጥ ቢሉ እኔን መቃብር ሳይጫነኝ ልጂ አጥንተ ሰባራ አታገባም» እንዲያውም አላቻዋ አግብታ ዘር ከምታበላሽ የሚያከላት የሚመስላት አጥታ ሳታገባ ቀረች ብትባል ክብሯን ይጨምረዋል እንጂ አይቀንሰውም» የሚል ነው*

በዚህ የሀዲስ አለማየሁ ቃለ ምልልስ ውስጥ ኢትዮጵያ የክርስቲያን ሀገር በመሆን ክርስቲያናዊ ስነ ምግባር የሰፈነባት ሳትሆን ስነ ቃል መሪ እና እምነት በመሆን ልዩነቱን ማሳየቱን ነው ያረጋገጠው። አቅም ያለው ክርስትና የባልና ሚስት ግንኙነት በአንድ አቋም የፀና ያስመስል እንጂ እንደ ጥሩዐይነት በየንግግሩ ጣልቃ «ጌታዬ» እያስባለ ከፊትአውራሪ «እመቤቴ» ማለትን የከለከለ ነው። ውዝግቡ በሴት ልጃቸው ቢሆንም ጎልቶ የወጣው «የማን ልጅ ነው» የሚለው የአባት ጥያቄ ማንነት ነው፤ በዚህም ሰው በእግዚአብሔር መለኪያ ሳይሆን በተቀባበሉት እና ባመኑት ሰፍረውታል፤ ሌላው የተሰፈረለትን እንዲያምንም አስገድዷል።

በዚህ ውስጥ ግን ተገዳዳሪውን ጫና ከምንም ሳይቆጥሩ ልከኛው መስመር ይያዝ ዘንድ እነ ፊትአውራሪን «አባቱን አላዋቂው፣ ገበሬው፣ መጫኛ ነካሹ፣ ወተታሙም» ደፍረው ጠይቀዋል፤ በዚህም የትግል ቀጣይነት እስከ መቼ እንደሚቀጥል ያስነብባል፤ በርከክቡ ሂደትም ቀስ በቀስ ለውጥ እያደገ ይመጣል፤ ገለፃው ግን «ልኩ ይኸው ነው» በሚል የተተነተነ ነው፤ የተፈጠሩ እጓጓል ድርሰቶች ገዢ ሆነው ሲገኙ ፍቅር እስከመቃብር ግን መፍትሄን በድርሰት ሂደት ውስጥ አኑሯል፤ ያም ትምክተኛ የሆኑትን ፊትአውራሪንና ጥሩ አይነትን ማስወገድ፣ በምትኩ ሰብለ ወንጌልን ከበዛብህ ጋር በማስተሳሰር በሰው እኩልነትና በእግዚአብሔር አምሳል በመፈጠሩ አቅም ላይ መጠቅለል ፅኑ አቋማቸው ሆኖ ተደምድሟል። እነሀ ሁሉ አካሄዶች ግን ፊትአውራሪን ወይም መሰሎቻቸውን ለመርገም እና እንደ ኋላ ቀር ለመቁጠር አይደለም፤ ይልቅስ ወንድ ተኮር አሉታዊ አስተሳሰቦች በተለያዩ መንገዶች እንዲባነንባቸው ካልተደረጉ ጉዳቱ ብዙ መሆኑን ያረጋግጣል ከልብ ወለዱ መነሻ